## መመሪያ ቁጥር 3 /2017

## የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ

### መግቢያ

የፍርድ ቤቶች የቅጣት አወሳሰን ትክክለኛነት ፣አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ (Manual) እንዲያወጣ ፣ በ1996 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ የተደነገገ በመሆኑ፤

የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የማውጣት ስራ በየጊዜው መረጃ መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ጥናት እና ምርምር ማድረግ፣ የመመሪያውን ትግበራ መከታተል እና ይህንኑ መሰረት በማድረግ መመሪያውን ማሻሻል የሚጠይቅ መሆኑን በማስታወስ፤

በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት የሚወሰን የወንጀል ቅጣት ፣ የዳኞችን የመወሰን ነፃነት እና የፍርድ ቤቶችን ተቋማዊ ነፃነት ባከበረ ሁኔታ፣ እንዲሁም ተጠያቂነት እና የህዝብ አመኔታን ባተረፈ መልኩ ሊተገበር የሚገባ መሆኑን በመገንዘብ፤

ከጥቅምት 1/ 2006 ዓ.ም ጀምሮ ተግባር ላይ በቆየው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ስራ ላይ በቆየባቸው ዓመታት ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት ማሻሻያ ማድረግ በማስፈለጉ፣ እንዲሁም በወታደራዊ ወንጀሎች፣ በተሻሻሉ እና አዲስ በወጡ ሕጎች ውስጥ ለሚገኙ ደረጃ ላልወጣላቸው ወንጀሎች የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 88(4) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. ስያሜ

ይህ መመሪያ "የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 3 /2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፡፡

1. ‹ፍርድ ቤት› ማለት የወንጀል ጉዳዮችን ለመዳኘት በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል ማለት ነው፡፡
2. ‹የወንጀል ደረጃ› ማለት በአንድ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ውስጥ የሚያርፉ የወንጀል ድርጊቶች በአፈፃፀማቸው ሁኔታ፣ በሚያደርሱት ጉዳት እና/ወይም በሚያስገኙት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መሰረት የሚኖራቸው ክብደት ነው፡፡
3. ‹የወንጀል ደረጃ መግለጫ› በወንጀሎች ላይ እንደ ክብደታቸው ተመጣጣኝ ቅጣት ለመወሰን የሚያስችሉ እንደ የወንጀል ድርጊት አፈፃፀም ሁኔታ፣ በወንጀሉ የደረሰ ጉዳት እና/ወይም በወንጀሉ የተገኘ ተገቢ ያልሆነ ጥቅምን የተመለከቱ መመዘኛዎች (መስፈርቶች) ማለት ነው፡፡
4. ‹የቅጣት እርከን› ማለት ነፃነትን ፣ ህይወትን የሚያሳጡ ቅጣቶች እና የገንዘብ መቀጮ ሠንጠረዥ ውስጥ የሚገኝ፣ እንደአግባብነቱ መነሻ እና መድረሻ ያለው ቅጣት የሚወሰንበት ረድፍ ማለት ነው፡፡
5. ‹ፍቅድ ስልጣን› ማለት ፍርድ ቤቶች የወንጀል አፈጻጸም ልዩ ሁኔታ ከግምት በማስገባት ቅጣቱን ለመጣል የሚችሉበት በአንድ የቅጣት እርከን መነሻና መድረሻ መካከል ያለው የቅጣት መጠን ማለት ነው፡፡
6. ‹መነሻ ቅጣት› ማለት በአንድ ወንጀል ላይ የሚወሰን ቅጣትን በተመለከተ፣ ቅጣቱን የሚያከብዱና የሚያቀሉ ጠቅላላ እና ልዩ ምክንያቶች ታሳቢ ከመደረጋቸው በፊት፣ ፍርድ

ቤቱ ይህን መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ በለየው የቅጣት እርከን መሰረት በማድረግ የሚጣል ቅጣት ነው፡፡

3. **የመመሪያው ዓላማና ግብ**

1. **ዓላማ**

የመመሪያው ዓላማ የዳኝነት አካሉ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ውጤታማና ተገማችነት ያለው ቅጣት የሚሰጥበትን ስርዓት መመስረት ነው፡፡

2. **ግብ**

መመሪያው የሚከተሉት ግቦች ይኖሩታል፡-

ሀ. በተቀራራቢና ተመሳሳይ የወንጀል ጉዳዮች መካከል ተቀራራቢነት ያለው ቅጣት እንዲወሰን ማድረግ፣

ለ. እንደ ወንጀሉ ክብደትና አደገኛነት የቅጣትን ተመጣጣኝነት ማረጋገጥ፡፡

4. **የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን**

1. ግልፅ የሆነ ሌላ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር፣ ይህ መመሪያ የወንጀል ጉዳዮችን በመዳኘት ቅጣት ለመወሰን በሕግ ስልጣን በተሰጣቸው ፍርድ ቤቶች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. ግልፅ የሆነ ሌላ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ይህ መመሪያ በደንብ መተላለፍ እንዲሁም አካለመጠን ያላደረሱ ወጣት ወንጀል አድራጊዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

5. **መሰረታዊ የአተገባበር መርሆዎች**

1. በእያንዳንዱ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ወንጀሉን የሚያቋቁመው ፍሬነገር አንድና ተመሳሳይ ቢሆንም የወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀም ሁኔታ፣ በወንጀሉ የደረሰ ጉዳት እና/ወይም በወንጀሉ የተገኘ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መሰረት በማድረግ እንደ ወንጀሉ ክብደትና አደገኛነት ደረጃ በማውጣት ቅጣት ይወሰናል፡፡

2. ፍርድ ቤቶች ቅጣት ሲወስኑ፣ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶችን መሰረት አድርገው ቅጣቱን ከማክበዳቸው ወይም ከማቅለላቸው በፊት፤ ከተጣሰው የወንጀል ድንጋጌ አንጻር

የወንጀሉን ባህሪ መሰረት በማድረግ በቅድሚያ ወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2) እና በዚህ መመሪያ መሰረት የወንጀሉን ደረጃ በመለየት፣ ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት በተያያዙት የቅጣት እርከን ሰንጠረዦች በመጠቀም መነሻ ቅጣቱን ይወስናሉ፡፡ በመቀጠልም ቅጣቱን የሚያከብዱ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣቱን ያከብዳሉ፣ በመጨረሻም ቅጣቱን የሚያቃልሉ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣቱን ያቀላሉ፡፡

3. በዚህ መመሪያ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር፣ በወንጀል ሕግ በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት እንደሚያስቀጡ በተደነገጉ ወንጀሎች ላይ ፣ ፍርድ ቤቱ ከቀላል እስራት ወይም ከጽኑ እስራት መካከል አንዱን አማራጭ በቅድሚያ በመያዝ ደረጃ እና እርከኑን በማውጣት ቅጣቱን ያሰላል፡፡

4. የቅጣት ማክበጃዎችና ማቅለያዎች ወጥነት ባለው መልኩ ቅጣቱን የሚያከብዱ ወይም የሚያቀሉ ይሆናሉ፡፡ ሆኖም በወንጀል ሕጉ ስለ ልዩ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ናቸው፡፡

5. ፍርድ ቤቶች መነሻ ቅጣቱን ለማስቀመጥ፣ እንዲሁም የቅጣት ማክበጃዎችና ማቅለያዎችን መሰረት በማድረግ ቅጣቱን ለማክበድ ወይም ለማቅለል ሲወስኑ፣ እንደ ወንጀሉ ዓይነት ሊታዩ የሚገቡ ልዩ ሁኔታዎችን ታሳቢ በማድረግ በየቅጣት እርከኑ ባለው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ አግባብነት ያለውን ቅጣት ይወስናሉ፡፡

6. በዚህ መመሪያ የወንጀል ደረጃ ያልወጣላቸው የወንጀል ድንጋጌዎችን በመጣስ የሚፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶች ላይ የሚወሰነው ቅጣት፣ በዚህ መመሪያ የወንጀል ደረጃ ለወጣላቸው የወንጀል ሕግ ድንጋጌዎች ላይ ቅጣት ለመጣል የተቀመጡትን አጠቃላይ ድንጋጌዎች፣ መስፈርቶችና አሰራሮችን እንደ ሁኔታው በመጠቀም ይሆናል፡፡

7. ይህ መመሪያ በወንጀል ሕግ ስለ ቅጣት አወሳሰን ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ይተረጎማል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ነፃነትን እና ህይወትን የሚያሳጡ ቅጣቶች እና የገንዘብ መቀጮ ሠንጠረዥ

### 6. ነፃነትንና ሕይወትን የሚያሳጡ ቅጣቶች እርከን ሠንጠረዥ

1. ነጻነትንና ሕይወትን የሚያሳጡ ቅጣቶች እርከን ሠንጠረዥ ከቀላል እስራት እስከ ሞት ቅጣት ድረስ ያለውን ያካተተ ነው፡፡

2. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል በወንጀል ሕጉ በተመለከተው መሰረት ከዝቅተኛው ቅጣት (1 ቀን የግዴታ ስራ) እስከ ከፍተኛው ቅጣት (ሞት) ድረስ የሚደርስ በአጠቃላይ 45 የቅጣት እርከኖች ያሉት ሠንጠረዥ (አባሪ -1) ተዘጋጅቷል፡፡

3. የቅጣት እርከኖች ሠንጠረዥ ሲዘጋጅ ለእያንዳንዱ የቅጣት እርከን መነሻና መድረሻ ያለው ሲሆን፣ ከዚህ በታች በተገለፁት ንዑሳን ድንጋጌዎች መሰረት የተዘጋጀ ነው፡፡

   ሀ. እርከን-1 የግዴታ ስራን ወይም ተግሳፅ ፣ ማስጠንቀቂያ ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መንገድ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ከ ከእርከን 2 እስከ እርከን 15 ድረስ ደግም በመነሻውና በመድረሻው መካከል የስድስት ወር ፍቅድ ስልጣን እንዲኖር ተደርጓል፡፡

   ለ. ከቅጣት እርከን 16 እስከ እርከን 35 ድረስ በመነሻውና በመድረሻው መካከል ያለው ፍቅድ ስልጣን የመነሻውን አስራ አምስት በመቶ (15%) እንዲሆን ተደርጓል፡፡

   ሐ. ከ ቅጣት እርከን 36 እስከ እርከን 41 ድረስ ላሉት የቅጣት እርከኖች የ2 ዓመት ፍቅድ ስልጣን፣ ለ እርከን 42 እና እርከን 43 እንደ ቅደም ተከተላቸው የ 3 ዓመት እና የ 4 ዓመት ፍቅድ ስልጣን እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡

   መ. የእያንዳንዱ የቅጣት እርከን መነሻ ሲቀመጥ፣ ከ አንድ የቅጣት እርከን ከፍ ብሎ የሚገኘውን የቅጣት እርከን አማካይ ለቀጣዩ እርከን እንደመነሻ በመውሰድ ፍቅድ ስልጣኑ ተወስኗል፡፡ አማካኙ ሲሰላ ለስሌት እንዲቀል ሽርፍራፊ ጊዜያትን እንደነገሩ ሁኔታ ወደሚቀርበው ጊዜ በማጠጋጋት የእርከን መነሻው ተወስኗል፡፡

   ሠ. የወንጀል ሕጉ ቀላል እስራት ወደ የግዴታ ስራ ሊቀየር እንደሚችል ስለሚያስቀምጥ፣ ለዚህ መመሪያ አላማ (አባራ-1 ስር) የአንድ ቀን እስራት ከአንድ ቀን (8 ሰዓት) የግዴታ ስራ ጋር ተመጣጣኝ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ስለሆነም የእስራት ቅጣቱ በማቅለያ ምክንያት

የሚቀነስ ከሆነ ተቀንሶ በተደረሰበት የእስራት ጊዜ ልክ የግዴታ ስራ እንዲሰራ ለመወሰን በሚያስችል መልኩ የቅጣት እርከኑ ተዘጋጅቷል፡፡

ረ. ከላይ በንዑስ አንቀጽ "ሠ" የተደነገገው ቢኖርም፣ በዚህ መመሪያ የቀላል እስራት ወደ ግዴታ ስራ የሚቀየረው በወንጀል ህግ አንቀጽ 103(1) መሰረት በልዩ ክፍል እስከ 6 ወር ቀላል እስራት እንደሚያስቀጡ በተደነገጉ ወንጀሎች እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 179 (ረ) ማቅለያ በሚያዝላቸው ወንጀሎች ብቻ ላይ ነው፡፡

ሸ. በቅጣት ማቅለያ ጊዜ የእስራት ቅጣት ወደ መቀጮ እንደሚቀየር የወንጀል ሕግ አንቀጽ 179 (ረ) የሚደነግግ በመሆኑ ወደ መቀጮ ሲቀየር ስንት ሊሆን እንደሚችል በሚያሳይ መልኩ የቅጣት እርከኑ ተዘጋጅቷል፡፡

ቀ. በ ወንጀል ሕግ አንቀፅ 89 በተደነገገው መሰረት ከሶስት ወር የማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከ አንድ ሽህ ብር የማይበልጥ መቀጮ በሚያስቀጡ ወንጀሎች ላይ ማስጠንቀቂያ እና ተግሳፅ ለመወሰን በሚያስችል መልኩ የቅጣት እርከን ተዘጋጅቷል፡፡

7. **የገንዘብ መቀጮ ሠንጠረዥ**

1. በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90(2) የተደነገጉትን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ የሚተገበር የገንዘብ መቀጮ ጣሪያዎችን የሚያሳይ የገንዘብ መቀጮ እርከን ሠንጠረዥ በአባሪ-2 ተዘጋጅቷል፡፡

2. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 90(2) መሰረት የገንዘብ መቀጮን ለመወሰን የወንጀል አድራጊው የገቢ መጠን፣ ሀብቱ ወዘተ ከግምት ገብተው ስለሚወሰን በወንጀል ህጉ ከተቀመጠው ጠቅላላ የመቀጮ ወለል ሌላ መነሻ ቅጣት አልተቀመጠም፡፡

3. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 92 በተደነገገው መሰረት ወንጀሉ በአፍቅሮ ንዋይ የተፈጸመ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች በመቀጮ ቅጣት እርከን የተቀመጠውን ጣሪያ በአስር እጥፍ በማሳድግ በወንጀል ሕግ ከተመለከተው ጣሪያ ሳይበልጥ የመቀጮውን መጠን ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

4. በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል እና በሌሎች የወንጀል ሕግ ይዘት ባላቸው አዋጆች የተደነገገው የመቀጮ ጣሪያ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 90(1) ከተደነገገው ጣሪያ በላይ ከሆነ፣ በልዩ ድንጋጌዎች ላይ የተቀመጠውን ጣሪያ መሰረት በማድረግ መቀጮው ይሰላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የወንጀል መነሻ ቅጣት ስለሚወሰንበት ሁኔታ

### ንዑስ ክፍል- አንድ

### እንደ ወንጀሉ ክብደት ደረጃ የወጣላቸው የወንጀል ዓይነቶች ድንጋጌዎች እና የወንጀል ደረጃዎች

### ርዕስ አንድ

### በመንግስት ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

**8. የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመነካት የሚደረግ ወንጀል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 241)**

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 241 የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት በሚደረግ ወንጀል እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 257 በመገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ ማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

2. በወንጀል ህጉ አንቀጽ 241 ስር ቅጣትን ለመወሰን የወንጀሉን ማቋቋሚያ ነጥቦች፣ ጥፋተኛው የቡድን አባል መሆን አለመሆን፣ በወንጀሉ የደረሰውን ጉዳት፣ የጥፋተኛው ስልጣን ደረጃ፣ እንዲሁም በወንጀሉ የተገኘ ጥቅም የሚሉ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. ለዚህ ድንጋጌ ዓላማ ሲባል፡-

   ሀ. "ቀላል ጉዳት"፡- ማለት በንብረት ላይ እስከ ብር 200,000.00 ጉዳት ያደረሰ ወይም በሰው ላይ ቀላል የአካል ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ ነው

   ለ፡-"መካከለኛ ጉዳት";- ማለት በንብረት ላይ ከብር 200,001.00 እስከ 500,000.00 ጉዳት ያደረሰ ወይም በሰው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ያስከተለ ነው፡፡

ሐ. ”ከባድ ጉዳት” ማለት በንብረት ላይ የብር 500,001.00 እና ከዚያ በላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም ድርጊቱ ሞት ያስከተለ እንደሆነ ነው፡፡

4. የወንጀል ድርጊቱ በገንዘብ ወይም በንብረት ላይ ያስከተለው ጉዳት መጠን እና በሰው አካል ወይም ህይወት ላይ ያስከተለው የጉዳት መጠን የሚገኝበት ደረጃ የተለያየ በሚሆንበት ጊዜ ፍ/ቤቱ ቅጣቱን የሚወስነው ከሁለቱ ደረጃ የበለጠ ወይም ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስከትለውን የጉዳት መጠን መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

5. በወንጀል ህጉ አንቀጽ 241 ስር ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ ከአስር አመት እስከ ሃያ አመት ለመድረስ በሚችል ጽኑ እስራት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ሊቀጣ እንደሚችል በድንጋጌው የተመለከተ ሲሆን፣ በተጨማሪነት የወንጀል ህግ አንቀጽ 259 መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ እስከ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) ሊደርስ የሚችል መቀጮ ሊያስከትል የሚችል ወንጀል በመሆኑ ከደረጃ ሰባት አንስቶ ላሉት የወንጀሉ ደረጃዎች ነጻነትን ከሚያሳጡ የቅጣቶች እርከን ጎን ለጎን የገንዘብ መቀጮ እርከኖች እንዲታከሉ ተደርጓል፡፡

6. ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 241 ስር የሞት ቅጣትን በሚወሰንበት ጊዜ ከወንጀል ህግ አንቀጽ 258 መስፈርቶች በተጨማሪ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 117 ድንጋጌዎችን ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡፡

## 9. መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር (የወንጀል ህግ አንቀጽ 257)

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ህግ አንቀጽ 257 በመገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ ማሰናዳት ተግባር ወንጀል ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

2. በወንጀል ህግ አንቀጽ 257 ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ቅጣት ለመወሰን ከንዑስ ፊደል ‹‹ሀ›› እስከ ‹‹ሠ›› ስር ያሉት ድንጋጌዎች የያዟቸው የማቋቋሚያ ነጥቦች ክብደት ፣ ወንጀሉ ሊያስከትል ይችል የነበረው አደጋ ከባድነት፣ የጥፋተኛው ስልጣን ደረጃ፣ እንዲሁም በወንጀሉ የተገኘ ጥቅም የሚሉት መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ስምንት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. ለወንጀል ህግ አንቀጽ 257 በወንጀል ድንጋጌው ስር ከንዑስ ፊደል ‹‹ሀ›› እስከ ‹‹ሠ›› በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች እና በአንቀጽ 259 ላይ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ስምንት ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

4. የወንጀል ደረጃ 6 እና ደረጃ 8 ወንጀሉ ሊያስከትል ይችል የነበረውን አደጋ ከፍተኛነት መሰረት ያደረጉ ሲሆን በሁለቱም ደረጃዎች የአደጋውን ክብደት ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ እያየ ምክንያቱን በግልጽ በማስፈር ሊወስን ይችላል፡፡

5. ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው በደረጃ ሰባት የተመለከቱትን የስልጣንና የጥቅም መስፈርቶች መሟላታቸውን እንደነገሩ ሁኔታ እያየ ምክንያቱን በግልጽ በማስፈር የሚወሰን ይሆናል፡፡

6. በወንጀል ህጉ አንቀጽ 257 ስር ጥፋተኛ የተባለ ተከሳሽ በቀላል እስራት፣ ወይም ይህ አድራጎት ሊያስከትል ይችል የነበረው አደጋ በተለይ በጣም ከፍ ያለ እንደሆነ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ሊቀጣ እንደሚችል በድንጋጌው የተመለከተ ሲሆን፣ በተጨማሪነት የአንቀጽ 259 መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ እስከ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) ሊደረስ የሚችል መቀጮ ሊያስከትል የሚችል ወንጀል በመሆኑ ከደረጃ 4 አንስቶ ላሉት የወንጀል ደረጃዎች ነጻነትን ከሚያሳጡ የቅጣቶች እርከን ጎን ለጎን የገንዘብ መቀጮ እርከኖች እንዲታከሉ ተደርጓል፡፡

10. **የአገሪቱን የፖለቲካና የግዛት አንድነት በመንካት የሚደረግ ወንጀል (የወንጀል ህግ አንቀጽ 241)**

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 241 | 1 | የተደራጀ የቡድን አባል ሳይሆን በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የፈጸመና ጉዳቱ ቀላል ከሆነ፡፡ | 33 | |
| 241 | 2 | የተደራጀ የቡድን አባል ሆኖ በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የፈጸመና ጉዳቱ ቀላል ከሆነ፡፡ | 34 | |
| 241 | 3 | የተደራጀ ቡድን አባል ሳይሆን በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ከተፈጸመና ጉዳቱ መካከለኛ ከሆነ፡፡ | 35 | |
| 241 | 4 | የተደራጀ ቡድን አባል ሆኖ ድርጊቱ በድንጋጌው አግባብ ከተፈጸመና የደረሰው ጉዳት መካከለኛ ከሆነ፡፡ | 36 | |
| 241 | 5 | የተደራጀ ቡድን አባል ሳይሆን ድርጊቱ በድንጋጌው አግባብ ከተፈጸመና ጉዳቱ ከባድ ከሆነ፡፡ | 37 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 241 | 6 | የተደራጀ ቡድን አባል ሆኖ ድርጊቱ በድንጋጌው አግባብ በተፈጸመና ጉዳቱ ከባድ ከሆነ፡፡ | 41 | |
| 241 እና 259 | 7 | በድንጋጌው የተመለከቱት ተግባራት የተፈጸሙት ተሿሚ ወይም መሪ በሆነ ሰው ወይም ጥቅም ለማግኘት ሆኖ ጉዳቱ ቀላል ከሆነ፡፡ | 42 | 7 |
| 241 እና 259 | 8 | በድንጋጌው የተመለከቱት ተግባራት የተፈጸሙት ተሿሚ ወይም መሪ በሆነ ሰው ወይም ጥቅም ለማግኘት ሆኖ ጉዳቱ መካከለኛ ከሆነ፡፡ | 43 | 10 |
| 241 እና 259 | 9 | በድንጋጌው የተመለከቱት ተግባራት የተፈጸሙት ተሿሚ ወይም መሪ በሆነ ሰው ሆኖ ጉዳቱ ከባድ ከሆነ፡፡ | 44 | 11 |
| 241 እና 258 | 10 | በድንጋጌው ከተመለከቱት ተግባራት አንዱ ከተፈጸመና በአንቀጽ 258 ስር ከተዘረዘሩት ፍሬ ነገሮች አንዱ ከተሟላ፡፡ | 45 | 12 |

## 11. መገፋፋትና ግዙፍ ያልሆነ የማሰናዳት ተግባር (የወንጀል ህግ አንቀጽ 257)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ |
|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | መነሻ<br>እርከን |
| 257 | 1 | አጥፊው ድርጊቱን በንግግር፣ በስዕል ወይም በጽሁፍ አማካይነት በግልጽ የቀሰቀሰ እንደሆነ፡፡ | 2 | |
| 257 | 2 | አጥፊው ሽፍቶችን በአገር ውስጥ ወይም ከአገር ውጭም ቢሆን እንዲቋቋሙ ያደመ፣ ዕቅድ ያወጣ ወይም የገፋፋ እንደሆነ፡፡ | 5 | |
| 257 | 3 | እንዲዚህ በመሳሰሉ ሽፍቶች ቡድን የገባ፣በእቅዱም የተባበረ ወይም ትዕዛዙን የተከተለ እንደሆነ፡፡ | 8 | |
| 257 | 4 | ከዉጭ አገር መንግስታት፣ የፖለቲካ ወይም ሌላ ድርጅት ወይም ከእነዚሁ ወኪሎች ጋር ግንኙነት ያደረገ ወይም በምስጢር ግንኙነት የተባበረ እንደሆነ፡፡ | 11 | |
| 257 | 5 | የህዝብን ሞራል ዝቅ ለማድረግ እና እምነቱን ወይም የመቋቋም ኃይሉን ለማፍረስ በማቀድ በተቀናጀ ዘዴ ትክክለኛ ያልሆነ፣ ጥላቻ የተሞላበት ወይም ያለውን አቋም የሚያፈርስ መረጃ በንግግር፣ በጽሁፍ ወይም በስዕል የበተነ ወይም ያስታወቀ እንደሆነ፡፡ | 15 | |
| 257 | 6 | ከላይ ከተፈጸሙት ድርጊቶች መካከል አንዱ በጣም ከፍ ያለ አደጋ ሊያስከትል ይችል የነበረ እንደሆነ፡፡ | 19 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 257 እና 259 | 7 | በድንጋጌው የተመለከቱት ድርጊቶች የተፈጸሙት ተሿሚ ወይም መሪ በሆነ ሰው ወይም ጥቅም ለማግኘት ከሆነ፡፡ | 22 | 8 |
| 257 እና 259 | 8 | በደረጃ 7 የተመለከቱት ፍሬ ነገሮች እንዳሉ ሆነው ድርጊቱ ከፍ ያለ አደጋ ሊያስከትል ይችል የነበረ ከሆነ፡፡ | 25 | 11 |

## ርዕስ ሁለት

## ወታደራዊ ወንጀሎች

**12. ጠቅላላ**

1. በዚህ ርዕስ ስር የተመለከቱት ድንጋጌዎች ወታደራዊ ወንጀሎችን የሚመለከቱ ሲሆን በመከላከያ ሰራዊት አዋጅ ቁጥር 1286/2015 አንቀጽ 39 መሰረት የተቋቋሙ ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች የቅጣት አወሳሰን ወጥነት እና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሲባል የተደነገጉ ናቸው፡፡

2. ወታደራዊ ወንጀሎች ተለይተው በወንጀል ህጉ መደንገጋቸው እና በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች እንዲታዩ የተደረገበት መሰረታዊ ምክንያት የመከላከያ ሰራዊቱን እንደተቋም ለማጠናከር እና ተቋማዊ ተልዕኮውን እንዲወጣ ለማስቻል በመሆኑ፤ ወታደራዊ ፍርድ ቤቶች የመከላከያ ሰራዊቱን የተልዕኮ አፈፃፀም ውጤታማነት መረጋገጥ ልዩ ፍላጎት (best interest of the service) ግምት ውስጥ በማስገባት ውሳኔ መስጠት የሚጠበቅባቸው በመሆኑ፤ እንዲሁም ወታደራዊ ደንብ እና ሥርዓት በማክበር፣ በፍትህ አስተዳደር እና በተቋሙ ውጤታማነት መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት መኖሩን መሰረት በማድረግ ወታደራዊ ወንጀሎችን በተመለከተ ራሱን በቻለ ርዕስ ስር የቅጣት አወሳሰን መመሪያ (Manual) እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

3. ለዚህ የመመሪያው ክፍል አላማ ሲባል፡-

   ሀ. "ቀላል/ዝቅተኛ ጉዳት/ጥቅም" ማለት በንብረት ላይ እስከ ብር 200,000.00 ወይም በሰው ላይ ቀላል የአካል ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ ነው፡፡

   ለ."መካከለኛ ጉዳት/ጥቅም" ማለት በንብረት ላይ ከብር 200,001.00 እስከ 500,000.00 ወይም በሰው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ ነው፡፡

   ሐ."ከባድ/ከፍተኛ ጉዳት/ጥቅም" ማለት በንብረት ላይ ከብር 500,001.00 እስከ 1,000,000.00 ወይም በሰው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች የአካል ጉዳት (መቁሰል) ወይም የሰው ሞት (መሰዋት) ያስከተለ እንደሆነ ነው፡፡

መ. “በጣም ከባድ/ከፍተኛ ጉዳት/ጥቅም” ማለት በንብረት ላይ ከብር 1,000,000.00 በላይ ጉዳት ያደረሰ ወይም ከአምስት ሰው በላይ ላይ የአካል ጉዳት (መቁሰል) ያስከተለ ወይም ከአንድ ሰው በላይ ሞት (መሰዋት) ያስከተለ እንደሆነ ነው፡፡

4. ለዚህ የመመሪያው ክፍል አላማ ሲባል

ሀ. “አዲስ ወታደር” ማለት በመከላከያ ሰራዊት አዋጅ ቁጥር 1286/2015 አንቀጽ 2(5) ስር የተመለከተው “መሰረታዊ ወታደር”፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 720/2005 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ15(1)(ሀ) እና በፌዴራል ማረሚያ ቤት አዋጅ ቁጥር 1174/2012 አንቀጽ 22(1)(ሀ) የተመለከተው የ“ኮንስታብል” ማዕረግ ያለው ፖሊስ እንዲሁም በክልልና ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽንና ማረሚያ ቤት ማቋቋሚያ ህጎች በተመሳሳይ የተመከተው የ“ኮንስታብል” ማዕረግ ያለው ፖሊስ ነው፡፡

ለ. ወታደራዊ ኃላፊነቶችን በተመለከተ “ከጓድ አመራር እስከ መቶ መሪ”፣ “የሻምበል አመራር እና ተመጣጣኝ ኃላፊነት”፣ “የሻለቃ አመራር እና ተመጣጣኝ ኃላፊነት”፣ “የክ/ጦር አመራር እና ተመጣጣኝ ኃላፊነት”፣ “የኮር አመራር እና ተመጣጣኝ ኃላፊነት”፣ “የኮር አመራር በላይ እና ተመጣጣኝ ኃላፊነት” ወ.ዘ.ተ … የሚሉት ሀረጎች በመከላከያ ሰራዊት አዋጅ ቁጥር 1286/2015 እና በመከላከያ ሰራዊት አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 460/2012 እንዲሁም በሚንስቴሩ በሚወጡ መመሪያዎች የተመለከተውን ይከተላሉ፡፡

ሐ. ባለ ሌላ ማዕረግ የሰራዊት አባላት (ባ/ማ) ለዚህ መመሪያ “ከጓድ አመራር እስከ መቶ መሪ” ወይም ተመጣጣኝ የስታፍ አመራር እንደሆኑ ይወሰዳል፡፡

መ. የፖሊስ እና የማረሚያ ቤት ፖሊስ ኃላፊነቶችን በተመለከተ በሌላ ሁኔታ ካልተረጋገጠ በቀር ለዚህ መመሪያ ሲባል፡-

- “ከረዳት ሳጅን እስከ ሳጅን” ያሉት “ከጓድ መሪ እስከ መቶ መሪ” እና ተመጣጣኝ ኃላፊነት” እንዳላቸው፤
- “ከረዳት ኢንስፔክተር እስከ ምክትል ኢንስፔክተር” ያሉት “የሻምበል አመራር እና ተመጣጣኝ ኃላፊነት” እንዳላቸው፤

- "ከኢንስፔክተር እስከ ዋና ኢንስፔክተር" ያሉት "የሻለቃ አመራር እና ተመጣጣኝ ኃላፊነት" እንዳላቸው፤
- "ከምክትል ኮማንደር እስከ ኮማንደር" ያሉት "የክ/ጦር አመራር እና ተመጣጣኝ ኃላፊነት" እንዳላቸው፤
- "ከረዳት ኮሚሽነር እስከ ምክትል ኮሚሽነር" ያሉት "የኮር አመራር እና ተመጣጣኝ ኃላፊነት" እንዳላቸው፤
- "ኮሚሽነር" እና በላይ የሆኑት "የኮር አመራር በላይ እና ተመጣጣኝ ኃላፊነት" እንዳላቸው ይወሰዳል፡፡

5. በወንጀል ህግ አንቀጽ 33 እንዲሁም በሌላ የህግ አግባብ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ወታደራዊ ወንጀሉ ሊፈፀም የሚችለው በማንኛውም የሰራዊት አባል ስለመሆኑ በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል በተደነገገበት ሁሉ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል "የሰራዊት አባል" ማለት በመከላከያ ሰራዊት አዋጅ ቁጥር 1286/2015 አንቀጽ 2(4) የተሰጠውን ትርጉም፣ በኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 720/2005 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ አንቀጽ 2(1) ለ"ፖሊስ አባል" የተሰጠውን ትርጉም፣ በፌዴራል ማረሚያ ቤት አዋጅ ቁጥር 1174/2012 አንቀጽ 2(3) ለ"ማረሚያ ቤት ፖሊስ" የተሰጠውን ትርጉም እንዲሁም በክልልና ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽንና ማረሚያ ቤት ማቋቋሚያ ህጎች የተመከተውን ተመሳሳይ ትርጉም ይይዛል፡፡

6. በዚህ መመሪያ መሰረት ሲታይ ጉዳዩ በተለያዩ የወንጀል ደረጃዎች ሥር የሚያርፍ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን የሚወስነው የበለጠ ወይም ከፍ ያለ ቅጣት የሚያስከትለውን መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

7. ወታደራዊ ግዴታን በመጣስ መኮንኖችና አዛዥ መኮንኖች የሚፈጽሟቸውን ወንጀሎች በተመለከተ አርዓያነት እንዲኖረው ባጠፋው ጥፋት መጠን በወንጀል ህጉ ከተደነገጉት ከፍተኛ የቅጣት ጣሪያዎች ሳይታለፍ በከባድ ቅጣት እንደሚቀጣ በወንጀል ህጉ የተደነገገ (የወ/ህ/ቁ 320) ሲሆን መኮንንነቱ ወይም አዛዥ መኮንንነቱ የወንጀሉን ደረጃ ለመወሰን ከዋለ የወንጀሉን ቅጣት ለማክበድ ሲል ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ሁኔታ ዳግመኛ ምክንያት ሊያደርገው አይችልም (የወ/ህ/ቁ 84(2))፡፡

8. በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ክስ ቀርቦ ሁለት ዓመት እና ከዚያ በታች የእስራት ቅጣት የሚወሰንበት፣ የሚታረሙበት እንዲሁም በሰራዊት አባልነት ማገልገል መቀጠላቸውን

የተመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች በአዋጁ እና በመከላከያ ሰራዊት ደንብ የተመለከተ በመሆኑ የቅጣት አወሳሰን መመሪያው ከዚህ ጋር በሚጣጣም መልኩ የሚተገበር ይሆናል፡፡

9. ወታደራዊ ወንጀሎችን የተመለከቱት የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች በፖሊስ አባላት ላይ ተፈፃሚ በሚሆኑበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ የፖሊስን ልዩ ተግባርና አቋም ከግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት መሆኑ በህጉ የተደነገገ በመሆኑ (የወ/ህ/ቁ 341) በፖሊስ አባላት ላይ በዚህ መመሪያ (Manual) መሰረት ፍርድ ቤቱ ቅጣት ሲወሰን ይህን ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡፡

**13. ከፍ ያለ ክዳት (የወንጀል ህግ አንቀፅ 248)**

1. በወንጀል ህግ አንቀፅ 248 መሠረት ከፍ ያለ ክዳት ወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ በሚባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወስነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡

2. በወንጀል ህጉ አንቀጽ 248 ስር ቅጣትን ለመወሰን የወንጀሉን ማቋቋሚያ ነጥቦች፣ ጥፋተኛው ሲቪል ወይም የሰራዊት አባል መሆኑን፣ የጥፋተኛው የስልጣን ደረጃ/ሃላፊነትና ማዕረግ፣ በሠራዊቱ አባላት፣ በጦር ክፍሉ ወይም በአገሪቱ ላይ የደረሰ ጉዳት፣ እንዲሁም ጥቅም ለማግኘት የተፈፀመ መሆኑን የተመለከቱ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው ዘጠኝ የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. ለዚህ ድንጋጌ አላማ ሲባል ሲቪል ባለስልጣናትን በተመለከተ "ከፍተኛ ሥልጣን"፣ "መካከለኛ ሥልጣን"፣ እና "ዝቅተኛ ስልጣን" ተብለው የተጠቀሱት በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ስር ለተለዩት የወንጀል አይነቶች በተዘጋጀው የዚህ መመሪያው ክፍል ውስጥ የተሰጣቸውን ትርጉም ይከተላሉ፡፡

4. ፍርድ ቤቱ በወንጀል ህግ አንቀጽ 248 ስር የሞት ቅጣትን ለመወሰን በወ/ህ/ቁ 258 እና 117 ስር የተደነገገውን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

5. የወንጀል ህግ አንቀፅ 248 ከወንጀል ህግ አንቀጽ 259 ጋር ሊጣመር የሚችልበትን ሁኔታ በፅኑ እስራት በሚያስቀጣ ወቅት ወይም ጥፋተኛው የተሾመ ወይም የመሪነት ስልጣን ያለው ከሆነ ወይም የግል ጥቅም ለማግኘት ከሆነ ከፅኑ እስራቱ በተጨማሪ በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 248 | 1 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የፈፀመ ሆኖ ለውትድርና አዲስ የሆነ የጦር መሳሪያ ያልያዘ ፤ ተከሳሹ ሲቪል ሆኖ ስልጣን የሌለው ከሆነ፡፡ | 23 | |
| 248 | 2 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የተፈፀመ ሆኖ ጥፋተኛው ከጓድ አመራር እስከ መቶ መሪ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ሃላፊነት ከሆነ፤ የነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያ የያዘ ከሆነ፤ በቡድን ሁለት እና ከሁለት በላይ ሆነው የፈፀሙት ከሆነ፤ ሲቪል ሆኖ ዝቅተኛ ስልጣን ያለው ከሆነ፡፡ | 26 | |
| 248 | 3 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የፈፀመ ሆኖ ጥፋተኛው ከሻምበል አመራር ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊነት ያለው ከሆነ፤ በቡድን ሁለት እና ከሁለት በላይ ሆነው የፈፀሙት መሳሪያ ይዘው ከሆነ፤ የደረሰው ጉዳት ቀላል ከሆነ፤ ሲቪል ሆኖ መካከለኛ ስልጣን ያለው ከሆነ፤ የደረሰው ጉዳት ቀላል ከሆነ፡፡ | 28 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 248 | 4 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የፈፀመው የሻለቃ አመራር እና ተመጣጣኝ ኃላፊነት ያለው ከሆነ፣ የወገን ሚስጥር አሳልፎ ለጠላት የሰጠ፣ የደረሰው ጉዳት መካከለኛ ከሆነ፣ በቡድን የተፈፀመ ሆኖ  የደረሰ ጉዳት ቀላል እንደሆነ፣ ሲቪል ሆኖ ከፍተኛ ስልጣን ያለው ከሆነ፡፡ | 30 | |
| 248 | 5 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የፈፀመው የክ/ጦር አመራር እና ተመጣጣኝ ኃላፊነት ያለው  ከሆነ፣ የወገን ሚስጥር አሳልፎ ለጠላት የሰጠ በዚህም በወገን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰ፣ ከባድ መሳሪያ እስከሞርተር እና እና ሚስጥራዊ የግንኙነት ኮድ አሳልፎ የሰጠ፣ በቡድን የተፈፀመ ሆኖ  የደረሰ ጉዳት መካከለኛ ከሆነ፡፡ | 33 | 4 |
| 248 | 6 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የፈፀመው የኮር አመራር እና ተመጣጣኝ ኃላፊነት ያለው ከሆነ፣ በሥራው ያገኘውን ሚስጥር አሳልፎ የሰጠ በዚህም በወገን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰ፣ ከባድ መሳሪያ/ሚስጥራዊ የግንኙነት ሬዲዮ አሳልፎ የሰጠ፣ በቡድን የተፈፀመ ሆኖ የደረሰ ጉዳት ከባድ ከሆነ፡፡ | 36 | 6 |
| 248 | 7 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የፈፀመው የኮር አመራር በላይ እና ተመጣጣኝ | 37 | 8 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ኃላፊነት ያለው ከሆነ፤ የወገንን እና የሃገርን ሚስጥር አሳልፎ የሰጠ በዚህም በሀገር ላይ በጣም ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰ፤ ጥብቅ ሚስጥራዊ የግንኙነት መስመሮች ሬድዮኖችን ለጠላት የሰጠ፤ በህቡዕ በመደራጀት የጠላትን ሴራ ለማስፈፀም ሲሰራ የነበረ ከሆነ፤ የጠላትን ፍላጎት ተቀብሎ ሌሎችን በማሳመን በወገን ውስጥ ሴል ፈጥሮ ሲንቀሳቀስ የነበረ ከሆነ፡፡ | | |
| 248 | 8 | በድንጋጌው አግባብ ወንጀሉ የተፈፀመው ጥቅም ለማግኘት ሆኖ ድርጊቱን የፈፀመው የኮር አመራር በላይ ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊነት ያለው ከሆነና የደረሰ ጉዳት ከፍተኛ ከሆነ፡፡ | 40 | 10 |
| 248 | 9 | በድንጋጌው አግባብ ወንጀሉ የተፈፀመው ጥቅም ለማግኘት ሆኖ ድርጊቱን የፈፀመው ከኮር አመራር በላይ ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊነት ያለው ከሆነና የደረሰ ጉዳት በጣም ከፍተኛ ከሆነ፡፡ | 44 | 12 |

### 14. ኲብለላ (የወንጀል ህግ አንቀፅ 288)

1. በወንጀል ህግ አንቀፅ 288 መሠረት የኲብለላ ወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ በተባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡

2. የኩብለላ ወንጀል የሰራዊቱን ግዳጅ አፈፃፀም የሚያውክ ከባድ ጥፋት በመሆኑ በተለይ በጦር ሜዳ ግዳጅ ወቅት፣ አንድ ክፍል በኦፐሬሽኖች ላይ አስፈላጊ የሰው ሃይል እጥረት እንዲከሰትና አላስፈላጊ መስዋትነትን ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ ቅጣቱ ይህንም መሰረት በማድረግ እየከበደ የሚሄድ ይሆናል፡፡

3. በወንጀል ህጉ አንቀፅ 288 ቅጣት ለመወሰን የጥፋተኛው ሃላፊነት/ማዕረግ፣ የወንጀል ድርጊቱ አፈፃፀም፣ የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመበት ወቅት በተለይም የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦር ክተት በታወጀበት፣ በጦርነት ጊዜ ወይም በጦር ሜዳ ግዳጅ ወቅት መሆኑን፣ እንዲሁም በሠራዊቱ አባላት፣ በጦር ክፍሉ ወይም በአገሪቱ ላይ የደረሰ ጉዳት መሰረት በማድረግ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው 13 (አስራ ሶስት) የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

4. ፍርድ ቤቱ በወንጀል ህግ አንቀጽ 288(2) ስር የሞት ቅጣትን ሲወስን በወ/ህ/ቁ 117 ስር የተደነገገውን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 288/1 | 1 | በንዑስ ድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የፈፀመ ሆኖ ለውትድርና አዲስ የሆነ የጦር መሳሪያ/ተተኳሽ ያልያዘ ከሆነ፡፡ | 10 |
| 288/1 | 2 | በንዑስ ድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የፈፀመ ሆኖ ጥፋተኛው ከጓድ አመራር እስከ መቶ መሪ ከሆነ፣ የነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያ ወይም ተተኳሽ የያዘ ከሆነ፣ በቡድን ሁለት እና | 13 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ከሁለት በላይ ሆነው የፈፀሙት ከሆነ፤ የደረሰው ጉዳት ቀላል ከሆነ ፡፡ | |
| 288/1 | 3 | በንዑስ ድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የፈፀመ ሆኖ ጥፋተኛው ከሻምበል አመራር ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊነት ያለው ከሆነ፤ የቡድን ጦር መሳሪያ/ተተኳሽ ይዞ ከሆነ፤ ከጥበቃ ቦታ ላይ የኮበለለ ከሆነ፤ በቡድን ሁለት እና ከሁለት በላይ ሆነው የፈፀሙት መሳሪያ ይዘው ከሆነ፤ የደረሰው ጉዳት መካከለኛ ከሆነ፡፡ | 15 |
| 288/1 | 4 | በንዑስ ድንጋጌው አግባብ ድርጊቱን የፈፀመው የሻለቃ አመራር ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊነት ወይም ከዚህ በላይ ኃላፊነት ያለው ከሆነ፤ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ከሆነ፤ ከጥበቃ ቦታ ላይ የኮበለለ ከሆነ፤ በቡድን ሁለት እና ከሁለት በላይ ሆነው የፈፀሙት የቡድን ጦር መሳሪያ ይዘው ከሆነ፤ በቡድን የተፈፀመ ሆኖ ቀላል ወይም ከዚያም በላይ ጉዳት አስከትሎ ከሆነ፡፡ | 18 |
| 288/2 | 5 | በደረጃ 1 የተመለከተው የተፈፀመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦር ክተት በታወጀበት ጊዜ ከሆነ፡፡ | 23 |
| 288/2 | 6 | በደረጃ 2 የተመለከተው የተፈፀመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦር ክተት በታወጀበት ጊዜ ከሆነ፡፡ | 26 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 288/2 | 7 | በደረጃ 3 የተመለከተው የተፈፀመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦር ክተት በታወጀበት ጊዜ ከሆነ፡፡ | 28 |
| 288/2 | 8 | በደረጃ 4 የተመለከተው የተፈፀመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦር ክተት በታወጀበት ጊዜ ከሆነ፡፡ | 30 |
| 288/2 | 9 | በደረጃ 1 የተመለከተው የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ ወይም በጦር ሜዳ ግዳጅ ወቅት ከሆነ፡፡ | 33 |
| 288/2 | 10 | በደረጃ 2 የተመለከተው የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ ወይም በጦር ሜዳ ግዳጅ ወቅት ከሆነ፡፡ | 36 |
| 288/2 | 11 | በደረጃ 3 የተመለከተው የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ ወይም በጦር ሜዳ ግዳጅ ወቅት ከሆነ፡፡ | 37 |
| 288/2 | 12 | በደረጃ 4 የተመለከተው የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ ወይም በጦር ሜዳ ግዳጅ ወቅት ከሆነ፡፡ | 41 |
| 288/2 | 13 | በደረጃ 3 ወይም ደረጃ 4 የተመለከተው የተፈፀመው በጦር ሜዳ ግዳጅ ወቅት ሆኖ ሠራዊቱ በውጊያ ላይ እያለ ከሆነ፡፡ | 44 |

## 15. በበላይ አለቃ ወይም በማዕርግ እኩያ በሆነ አባል ላይ የሚፈፀም ስድብ ፣ ዛቻና የእጅ እልፊት - (የወ/ህ/ አንቀጽ 297)

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ህግ አንቀጽ 297 መሠረት ተከሰው ጥፋተኛ በተባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡

2. የሰራዊቱ ውጤታማነት የሚመሰረተው ለበላይ አዛዥ በሚኖር ህጋዊ ታዛዥነት ላይ በመሆኑ፤ በበላይ አለቃም ሆነ በማዕረግ እኩያ ላይ የሚፈፀም ስድብ፣ ዛቻ፣ እጅ እልፊት ወታደራዊ የአዛዥ/ታዛዥ ተዋረዱን የሚያፋልስ እና የሰራዊቱን ውጤታማነት የሚጎዳ በመሆኑ፤ እንዲሁም ድርጊቱ በሠራዊቱ ውስጥ ያለውን ሞራል እና ስነምግባር በእጅጉ የሚጎዳና በትእዛዝ ሰንሰለት ላይ እምነት ማጣት የሚፈጥር በመሆኑ የሚጣለው ቅጣት ይህን ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡

3. በወንጀል ህጉ አንቀፅ 297 ቅጣት ለመወሰን የአንቀጹን ማቋቋሚያዎች እንዲሁም የጥፋተኛውን ሃላፊነት ደረጃ፤ ድርጊቱ በማዕርግ እኩያ ወይም በበላይ አለቃ ላይ የተፈፀመ መሆኑን፤ የግል ተበዳይ በሚመራቸው አባላት ፊት የተፈፀመ መሆኑን፤ የእጅ እልፊት ( የወንጀል ህግ አንቀፅ 560 (1) - የአካል ጉዳትን ወይም የጤንነት ጉድለትን ሳያደርስ) መፈፀሙን፤ ድርጊቱ የተፈፀመው በሃይል ተግባር ወይም በጦር መሳሪያ፣ አደገኛ በሆነ ነገር ወይም መሳሪያ አማካኝነት መሆኑን፤ እንዲሁም ወንጀሉ የተፈፀመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ መሆኑን መሰረት በማድረግ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው 16 (አስራ ስድስት) የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 297/1 | 1 | በማዕረግ እኩያ የሆነውን አባል የሰደበ ፣ የዛተበት፣ ያወከው እንደሆነና ጥፋተኛው አዲስ ወታደር ከሆነ፡፡ | 6 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | |
| 297/1 | 2 | የበላይ አለቃውን የሰደበ ፣ የዛተበት፣ ያወከው እንደሆነ፤<br>በማዕረግ እኩያ ላይ የተፈፀመ ሆኖ ጥፋተኛው ከጓድ እስከ ሻምበል አመራር ደረጃ ወይም ተመጣጣኝ ሃላፊነት ያለ ከሆነ፤<br>የግል ተበዳይ በሚመራቸው አባላት ፊት የተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 8 |
| 297/1 | 3 | በማዕረግ እኩያው ላይ የእጅ እልፊት የፈፀመ፤<br>የማዕረግ እኩያውን የሰደበ፣ የዛተበት፣ ያወከው ሆኖ ጥፋተኛው የሬጅመንት አመራር ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊነት ያለው ከሆነ ፡፡ | 10 |
| 297/1 | 4 | የበላይ አለቃው ላይ የእጅ እልፊት የፈፀመ፤<br>በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተውን የፈፀመው ጥፋተኛ የክ/ጦር አመራር ወይም ተመጣጣኝ ሃላፊነት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ፡፡ | 12 |
| 297/2 | 5 | በደረጃ 1 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 10 |
| 297/2 | 6 | በደረጃ 2 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 13 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 297/2 | 7 | በደረጃ 3 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 15 |
| 297/2 | 8 | በደረጃ 4 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 18 |
| 297/3 | 9 | በደረጃ 1 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው ጊዜ ከሆነ፡፡ | 10 |
| 297/3 | 10 | በደረጃ 2 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው ጊዜ ከሆነ፡፡ | 13 |
| 297/3 | 11 | በደረጃ 3 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው ጊዜ ከሆነ፡፡ | 15 |
| 297/3 | 12 | በደረጃ 4 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው ጊዜ ከሆነ፡፡ | 18 |
| 297/3 | 13 | በደረጃ 5 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው ጊዜ ከሆነ፡፡ | 13 |
| 297/3 | 14 | በደረጃ 6 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው ጊዜ ከሆነ፡፡ | 17 |
| 297/3 | 15 | በደረጃ 7 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው ጊዜ ከሆነ፡፡ | 21 |
| 297/3 | 16 | በደረጃ 8 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው ጊዜ ከሆነ፡፡ | 25 |

16. **ለበላይ አለመታዘዝ - (የወንጀል ህግ አንቀፅ 298)**

1. በወንጀል ህግ አንቀፅ 298 መሠረት ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወስነው ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡

2. የሰራዊቱ ውጤታማነት የሚመሰረተው ተዋረዱን ጠብቆ በሚፈፀም ትዕዛዝ በመሆኑ፣ ለበላይ አለመታዘዝ የትዕዛዝ ሰንሰለቱን የሚያዳክምና ውጤታማነትን በዕጅጉ የሚጎዳ በመሆኑ፣ በተለይም ድርጊቱ የተፈፀመው በግዳጅ ወቅት ሲሆን በውጤታማነት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ የከፋ በመሆኑ ይህን ታሳቢ በማድረግ ቅጣቱ እየከበደ እንዲሄድ ተደርጓል፡፡

3. በወንጀል ህጉ አንቀጽ 298 ቅጣት ለመወሰን የአንቀጹን ማቋቋሚያዎች እንዲሁም ትዕዛዝ አለመፈፀም፣ ለመፈፀም አምቢተኛ መሆን፣ የነበረው ሃላፊነት እና ማዕረግ፣ ትዕዛዝ ባለመፈፀሙ/እምቢተኝነቱ የደረሰ ጉዳት ቀላል፣ መካከለኛ፣ ከባድ መሆኑን መሰረት በማድረግ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው 9 (ዘጠኝ) የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

4. በወንጀል ህጉ አንቀጽ 298(3) እንደተመለከተው ወንጀሉ "በተለይ ከባድ" (exceptional gravity) ነው በማለት ፍርድ ቤቱ ሲወስን ጥፋተኛው ከነበረው ሃሳብ፣ ከኃላፊነቱ ደረጃ፣ ከደረሰው ጉዳት ክብደት፣ ወንጀሉ ከተፈፀመበት ጊዜ፣ እምቢተኛነቱ ቁርጠኛ ከመሆኑና ከድርጊቱ አፈፃፀም አንጻር ሁሉ ሲታይ ጥፋተኛው የፈፀመው ለበላይ አለመታዘዝ ወንጀል "በተለይ ከባድ" መሆኑን የተቀበለበትን ምክንያት በውሳኔው ማስፈር ይኖርበታል፡፡

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 298/1 | 1 | ጥፋተኛው አዲስ ወታደር ከሆነ፡፡ | 10 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 298/1 | 2 | ጥፋተኛው ከጓድ እስከ ሻምበል አመራር ደረጃ ወይም ተመጣጣኝ ሃላፊነት ያለ ከሆነ፤<br><br>የደረሰው ጉዳት መካከለኛ ወይም ከዚህ በታች ከሆነ፡፡ | 13 |
| 298/1 | 3 | ጥፋተኛው የሬጅመንት አመራር ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊነት ያለው ከሆነ፤<br><br>በሌላ ሰው ሊፈጸም የማይችል ትዕዛዝ ከሆነ፤<br><br>በወንጀል ድርጊቱ የደረሰው ጉዳት ከባድ ከሆነ፡፡ | 16 |
| 298/1 | 4 | ጥፋተኛው ክ/ጦር አመራር ወይም ተመጣጣኝ የስታፍ አመራር ወይም ከዚህ በላይ ኃላፊነት ያለው ከሆነ፤<br><br>የወንጀል ድርጊቱ ያስከተለው ጉዳት በጣም ከፍተኛ ከሆነ፡፡ | 19 |
| 298/2 | 5 | በደረጃ 1 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው ጊዜ እና ሁኔታ ከሆነ፤ | 14 |
| 298/2 | 6 | በደረጃ 2 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው ጊዜ እና ሁኔታ ከሆነ፤ | 18 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 298/2 | 7 | በደረጃ 3 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው ጊዜ እና ሁኔታ ከሆነ፡፡ | 25 |
| 298/2 | 8 | በደረጃ 4 የተመለከተው የተፈፀመው በአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (2) በተመለከተው ጊዜ እና ሁኔታ ከሆነ፡፡ | 31 |
| 298/3 | 9 | ወንጀሉ "በተለይ ከባድ" ሆኖ እምቢተኝነቱም የተፈፀመው በጠላት ፊት ከሆነ፡፡ | 44 |

17. **በዕቃዎች ያለአግባብ መገልገል ወይም ማባከን- (የወንጀል ህግ አንቀፅ 306)**

1. በወንጀል ህግ አንቀፅ 306 መሠረት ተከሰው ጥፋተኛ በተባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ ባለት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡

2. በወንጀል ህጉ አንቀፅ 306 ቅጣት ለመወሰን የአንቀጹን ማቋቋሚያዎች እንዲሁም ጥፋተኛው የነበረው ሃላፊነት እና ማዕረግ፣ የንብረቱ አይነት፣ ጥፋተኛው ያገኘው/ሊያገኝ የታሰበው ጥቅም፣ ንብረቱ ተመላሽ መደረጉን፣ እንዲሁም ድርጊቱ የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ መሆኑን ሁሉ መሰረት በማድረግ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው 15 (አስራ አምስት) የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. በተፈፀመው ወንጀል የተገኘው የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ለመገመት የማይቻል በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ምክንያቱን በማስቀመጥ ደረጃውን ይወስናል፡፡

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | 306 | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን ለቀላል እስራት | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን ለፅኑ እስራት |
|---|---|---|---|---|
| 306/1 | 1 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተውን የፈፀመ እንደሆነና ወይም አዲስ ወታደር ከሆነ ወይም የንብረቱ ዓይነት ቀላል ከሆነ ወይም<br><br>ያገኘው/ሊያገኝ የታሰበው ጥቅም ከብር 1000.00 እስከ 2500.00 ከሆነ ወይም ንብረቱ ወደተቋሙ ተመላሽ የተደረገ ከሆነ ወይም ከ48 ሰዓት ላላነሰ ትጥቁን ይዞ ከተማ ከሄደ ወይም የጦር መሳሪያ ይዞ የተከለከለ ቦታ ካደረ፡፡ | 6 | 10 |
| 306/1 | 2 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተውን የፈፀመ እንደሆነና ወንጀሉ የተፈፀመው ለሰራዊቱ በሚያገለግል ንብረት ከሆነ ወይም ያገኘው/ሊያገኝ የታሰበው ጥቅም ከብር 2501.00 እስከ 5000.00 ከሆነ ወይም<br><br>የጦር መሳሪያ ይዞ ከ50 ኪ/ሜ በላይ ተጉዞ የተያዘ ከሆነ፡፡ | 8 | 14 |
| 306/1 | 3 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተውን የፈፀመ እንደሆነና<br><br>ያገኘው/ሊያገኝ የታሰበው ጥቅም ከብር 5001.00 በላይ ከሆነ ወይም ጥፋተኛው ከጓድ እስከ ሻምበል አመራር ወይም ተመጣጣኝ የሃላፊነት ደረጃ ያለ ከሆነ፡፡ | 10 | 18 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 306/1 | 4 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተውን የፈፀመ እንደሆነና<br><br>ወንጀሉ የተፈፀመው ለውጊያ አገልግሎት በሚሰጡ ንብረቶች ላይ ከሆነ ወይም በቡድን ወይም በመደራጀት የተፈፀመ ከሆነ ወይም ጥፋተኛው የሬጅመንት አመራር ወይም ተመጣጣኝ የሃላፊነት ደረጃ ወይም ከዚህ በላይ ኃላፊነት ያለው ከሆነ ወይም በኃላፊነት በግምጃ የተረከበው ከሆነ፡፡ | 12 | 22 |
| 306/2 | 5 | አዲስ ወታደር ከሆነ ወይም የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመበት የንብረት አይነት በመጠን ወይም በቁጥር ወይም በዋጋ ዝቅተኛ ከሆነ ወይም ንብረቱ ለመንግስት ተመላሽ ከተደረገ ወይም የሥራ ባልደረባው በአደራ በሰጠው የነፍስ ወከፍ መሳሪያ/ተተኳሽ ላይ የተፈፀመ ከሆነ፡፡ | | 10 |
| 306/2 | 6 | የታጠቀውን የነፍስ ወከፍ መሳሪያ ከነሙሉ ትጥቁ የሸጠ ወይም<br><br>የተሸጠው መሳሪያ ከተያዘ ወይም ጥፋተኛው ከጓድ እስከ ሻምበል አመራር ወይም ተመጣጣኝ የሃላፊነት ደረጃ ያለ ከሆነ፡፡ | | 17 |
| 306/2 | 7 | ድርጊቱ የተፈፀመው በሰላም ጊዜ ከሆነ ወይም<br><br>ጥፋተኛው የሬጅመንት አመራር ወይም ተመጣጣኝ ወይም ከዚህ በላይ ኃላፊነት ያለው ከሆነ፡፡ | | 24 |
| 306/2 | 8 | ወንጀሉ የተፈፀመበት ንብረት ለጠላት ከተላለፈ ወይም ለማስተላለፍ ከተሞከረ ወይም የወንጀል ድርጊት የተፈፀመበት ንብረት ለውጊያ | | 32 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አገልግሎት ጥቅም የሚውል ከሆነ ወይም በኃላፊነት በግምጃ የተረከበው ከሆነ፡፡ | | |
| 306/3 | 9 | ወንጀል የተፈፀመበት መሳሪያ ወይም ዕቃ ለአገር ደህንነት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ፡፡ | | 16 |
| 306/3 | 10 | ወንጀል የተፈፀመበት መሳሪያ ወይም ዕቃ ለአገር ደህንነት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ እና የተገኘው/ሊገኝ የታሰበው ጥቅም ወይም ጉዳት መካከለኛ ወይም በታች ከሆነ ፡፡ | | 22 |
| 306/3 | 11 | ወንጀል የተፈፀመበት መሳሪያ ወይም ዕቃ ለአገር ደህንነት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ እና የተገኘው/ሊገኝ የታሰበው ጥቅም ወይም ጉዳት ከባድ ከሆነ፡፡ | | 30 |
| 306/3 | 12 | ወንጀል የተፈፀመበት መሳሪያ ወይም ዕቃ ለአገር ደህንነት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ እና በኃላፊነት በግምጃ የተረከበው ከሆነ፡፡ | | 41 |
| 306/4 | 13 | ከደረጃ 1 እስከ 4 የተመለከተው የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ፡፡ | | 23 |
| 306/4 | 14 | ከደረጃ 5 እስከ 8 የተመለከተው የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ፡፡ | | 33 |
| 306/4 | 15 | ከደረጃ 9 እስከ 12 የተመለከተው የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ፡፡ | | 42 |

## 18. የማይገባ ጥቅምን ማግኘት ወይም ያለአግባብ ማጥፋት - (የወንጀል ህግ አንቀፅ 307)

1. በወንጀል ህግ አንቀጽ 307 መሠረት ተከሰው ጥፋተኛ በተባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወስነው ከዚህ ቀጥሎ ባለት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡

2. ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ በወንጀል ህግ አንቀጽ 307 ስር የተመለከተው የማይገባ ጥቅምን ማግኘት ወይም ያላግባብ የማጥፋት ወንጀል አድራጎት እንደ እምነት ማጉደል፣ የተንኮል ሥራ አመራር፣ ጉቦ፣ በመንግስት ሥራ ላይ ማስገደድ ወይም የመሳሰሉት ሆኖ በእነዚሁ ወንጀሎች የማያስቀጣ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. ወንጀሉ በማንም ሰው ሊፈፀም እንደሚችል በህጉ የተደነገገ በመሆኑ የወታደር ስንቅን፣ ገንዘብን፣ ዕቃን፣ ነዳጅን፣ ወይም ማናቸውም ሌላ ንብረት የመጠበቅ፣ የመቆጣጠር፣ ሥራውን የመምራት፣ የመግዛት ወይም ማከፋፈል "ሀላፊነት የተሰጠው ሰው" ተካቶ የወንጀል ደረጃ ተዘጋጅቷል፡፡

4. በወንጀል ህጉ አንቀፅ 307 ቅጣት ለመወሰን የአንቀጹን ማቋቋሚያዎች እንዲሁም የተከሳሽን ወታደራዊ ኃላፊነት/ማዕረግ ወይም ኃላፊነት የተሰጠው ሰው መሆኑን፤ አድራጎቱ ያስከተለው ጉዳት/የተገኘው ጥቅም ቀላል፣ መካከለኛ፣ ከፍተኛ፣ በጣም ከፍተኛ መሆኑን፤ እንዲሁም ድርጊቱ የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ መሆኑን መሰረት በማድረግ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው 14 (አስራ አራት) የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

5. በተፈፀመው ወንጀል የተገኘው የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ለመገመት የማይቻል በሆነ ጊዜ ወይም የንብረቱን የተለየ አስፈላጊነት እንዲሁም የጥፋተኛውን ልዩ ኃላፊነት መሰረት በማድረግ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ምክንያቱን በማስቀመጥ ደረጃውን ሊወስን ይችላል፡፡

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን ለቀላል እስራት | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን ለፅኑ እስራት |
|---|---|---|---|---|
| 307/1 | 1 | አዲስ ወታደር እና ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፡፡ | 5 | 9 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 307/1 | 2 | ከንድ እስከ ሻምበል አመራር ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው እና ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፤ ወይም<br>አዲስ ወታደር እና መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፡፡ | 6 | 12 |
| 307/1 | 3 | የሬጅመንት አመራር ወይም ተመጣጣኝ የሃላፊነት ደረጃ እና ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፤ ወይም<br>ከንድ እስከ ሻምበል አመራር ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው እና መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፤ ወይም<br>አዲስ ወታደር እና ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፡፡ | 7 | 15 |
| 307/1 | 4 | ክፍለ ጦር አመራር ወይም ተመጣጣኝ ሃላፊነት ወይም ከዚያ በላይ እና ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፤ ወይም<br>የሬጅመንት አመራር ወይም ተመጣጣኝ የሃላፊነት ደረጃ እና መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፤ ወይም<br>ከንድ እስከ ሻምበል አመራር ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው እና ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፤ ወይም<br>አዲስ ወታደር እና በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፡፡ | 8 | 18 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 307/1 | 5 | ክፍለ ጦር አመራር ወይም ተመጣጣኝ ሃላፊነት ወይም ከዚያ በላይ እና መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፤ ወይም የሬጅመንት አመራር ወይም ተመጣጣኝ የሃላፊነት ደረጃ እና ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፤ ወይም ከጓድ እስከ ሻምበል አመራር ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊነት የተሰጠው ሰው እና በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፡፡ | 9 | 21 |
| 307/1 | 6 | ክፍለ ጦር አመራር ወይም ተመጣጣኝ የሃላፊነት ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ እና ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፤ ወይም የሬጅመንት አመራር ወይም ተመጣጣኝ ሃላፊነት እና በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፡፡ | 10 | 24 |
| 307/1 | 7 | ክፍለ ጦር አመራር ወይም ተመጣጣኝ ሃላፊነት ወይም ከዚያ በላይ እና በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፡፡ | 11 | 26 |
| 307/2 | 8 | በደረጃ 1 የተመለከተው የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ፡፡ | | 12 |
| 307/2 | 9 | በደረጃ 2 የተመለከተው የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ፡፡ | | 15 |
| 307/2 | 10 | በደረጃ 3 የተመለከተው የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ፡፡ | | 19 |
| 307/2 | 11 | በደረጃ 4 የተመለከተው የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ፡፡ | | 23 |
| 307/2 | 12 | በደረጃ 5 የተመለከተው የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ፡፡ | | 26 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 307/2 | 13 | በደረጃ 6 የተመለከተው የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ፡፡ | | 30 |
| 307/2 | 14 | በደረጃ 7 የተመለከተው የተፈፀመው በጦርነት ጊዜ ከሆነ፡፡ | | 34 |

**19. አስፈላጊ የሆነውን የደህንነት ጥንቃቄ ያለማድረግ - (የወንጀል ህግ አንቀፅ 309)**

1. በወንጀል ህግ አንቀፅ 309 መሠረት ተከሰው ጥፋተኛ በተባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ ባለት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡

2. በወንጀል ህጉ አንቀፅ 309 ቅጣት ለመወሰን የአንቀጹን ማቋቋሚያዎች እንዲሁም የተከሳሹን አዲስነት እና ኃላፊነት/ማዕረግ፣ ግድፈቱ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት (የታወቀ/ያልታወቀ) የተፈፀመ መሆኑን፣ እንዲሁም የአደጋ ምልክት በተሰጠበት፣ የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ የተፈፀመ መሆኑን መሰረት በማድረግ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው 12 (አስራ ሁለት) የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን ለቀላል እስራት | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን ለፅኑ እስራት |
|---|---|---|---|---|
| 309/1 | 1 | ጥፋተኛው አዲስ ወታደር ከሆነ፡፡ | 6 | 10 |
| 309/1 | 2 | ጥፋተኛው ከጓድ እስከ ሻምበል አመራር ደረጃ ወይም ተመጣጣኝ ሃላፊነት ያለ ከሆነ ወይም<br>የደረሰው ጉዳት መካከለኛ ወይም ከዚህ በታች ከሆነ ወይም | 8 | 13 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ጉዳት የደረሰበት ንብረት ለግዳጅ ማስፈፀሚያ የሚውል ንብረት ከሆነ፡፡ | | |
| 309/1 | 3 | ጥፋተኛው የሬጅመንት አመራር ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊነት ያለው ከሆነ ወይም በወንጀል ድርጊቱ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ከሆነ ወይም<br>ጥፋተኛው ንብረቱን የመቆጣጠር ሙሉ ኃላፊነት ያለው ከሆነ፡፡ | 10 | 15 |
| 309/1 | 4 | ጥፋተኛው ክ/ጦር አመራር ወይም ተመጣጣኝ ሃላፊነት ያለው ወይም ከዚህ በላይ ኃላፊነት ያለው ከሆነ ወይም<br>የወንጀል ድርጊቱ ያስከተለው ጉዳት በጣም ከፍተኛ ከሆነ ወይም<br>የደረሰው ጉዳት ግዙፍ ወይም ለጦርነት አስፈላጊ በሆኑ ንብረቶች ከሆነ፡፡ | 12 | 18 |
| 309/3/ሀ | 5 | በደረጃ 1 ወይም 2 የተመለከተው የተፈፀመው የአደጋ ምልክት በተሰጠበት ወይም የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ ከሆነ፡፡ | | 19 |
| 309/3/ሀ | 6 | በደረጃ 3 ወይም 4 የተመለከተው የተፈፀመው የአደጋ ምልክት በተሰጠበት ወይም የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ ከሆነ፡፡ | | 25 |
| 309/3/ለ | 7 | በድንጋጌው የተመለከተው የተፈፀመው የአደጋ ምልክት በተሰጠበት ወይም የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ ከሆነ፡፡ | 9 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 309/3/ለ | 8 | በድንጋጌው የተመለከተው የተፈፀመው የአደጋ ምልክት በተሰጠበት ወይም የጦርነት ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ ከሆነ፡፡ | 12 | |

20. **ፈሪነት - (የወንጀል ህግ አንቀፅ 312)**

1. በወንጀል ህግ አንቀፅ 312 መሠረት ተከሰው ጥፋተኛ በተባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው በዚህ ድንጋጌ መሠረት ነው፡፡

2. በወንጀል ህጉ አንቀፅ 312 ቅጣት ለመወሰን የአንቀጹን ማቋቋሚያዎች፣ እንዲሁም የተከሳሽን ወታደራዊ ኃላፊነት/ማዕረግ ፣ አድራጎቱ ያስከተለው ጉዳት/የተገኘው ጥቅም ቀላል፣ መካከለኛ፣ ከፍተኛ፣ በጣም ከፍተኛ መሆኑን፣ ድርጊቱ በጥፋተኛው ብቻ መፈፀሙን፣ ሌሎችን አባላት አስተባብሮ በጋራ የፈፀሙት መሆኑንና በማስተባበሩ/በማነሳሳቱ የነበረውን ሚና ሁሉ መሰረት በማድረግ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው 13 (አስራ ሶስት) የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 312/ሀ | 1 | ወንጀል ፈፃሚው አዲስ ወታደር ወይም የውጊያ ልምድ የሌለው ከሆነ፣<br>እምቢተኛ የሆነው በራሱ ብቻ ከሆነ፡፡ | 23 |
| 312/ሀ | 2 | የጓድ አመራር ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊነት ያለው ከሆነ፣ | 25 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | አዲስ ወታደር ሆኖ የቲሙን አባላት አስተባብሮ ሁለትና በላይ ሆነው በጋራ የፈፀሙት ሲሆን፤<br>የደረሰው ጉዳት መካከለኛ እና በታች ሲሆን፡፡ | |
| 312/ሀ | 3 | በመቶ መሪ ወይም ተመጣጣኝ ኃላፊነት ያለው ከሆነ፤<br>በቡድን ወይም እንደክፍል ሆነው አባላቱን በማነሳሳት ወይም በማስተባበር ወይም ሁኔታውን በማመቻቸት በጋራ የፈፀሙት ሲሆን፤እንደ ክፍል እምቢተኛ ሲሆን፤<br>የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ሲሆን፡፡ | 33 |
| 312/ሀ | 4 | ሻምበል አመራር ወይም ከዚህ በላይ እንዲሁም ተመጣጣኝ ኃላፊነት ያለው ሲሆን፤<br>ጥፋተኛው በጋራ እምቢተኛ እንዲሆኑ በማነሳሳት፣ በማስተባበር ወይም ሁኔታውን በማመቻቸት በግሉ የጎላ አስተዋጽኦ ሲኖረው፤<br>የደረሰው ጉዳት በጣም ከፍተኛ ሲሆን፡፡ | 38 |
| 312/ለ | 5 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው የተፈፀመው በደረጃ 1 በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 23 |
| 312/ለ | 6 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው የተፈፀመው በደረጃ 2 በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 25 |
| 312/ለ | 7 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው የተፈፀመው በደረጃ 3 በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 33 |
| 312/ለ | 8 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው የተፈፀመው በደረጃ 4 በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 38 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 312/ሐ | 9 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው የተፈፀመው በደረጃ 1 በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 23 |
| 312/ሐ | 10 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው የተፈፀመው በደረጃ 2 በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 25 |
| 312/ሐ | 11 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው የተፈፀመው በደረጃ 3 በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 33 |
| 312/ሐ | 12 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው የተፈፀመው በደረጃ 4 በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 38 |
| 312/ሐ | 13 | በድንጋጌው የተገለፁት ሁለት ወይም በላይ ማቋቋሚያዎች የተፈፀሙና በተለይ ጥፋተኛው ቀዳሚ አነሳሽ ሆኖ ውጤቱ በሠራዊቱ ላይ ከፍተኛ የሞራል ጫና ያስከተለ እና በጣም ከፍተኛ ጉዳት ደርሶ ከሆነ፡፡ | 44 |

**21. ለጠላት እጅን መስጠት - (የወንጀል ህግ አንቀፅ 313)**

1. በወንጀል ህግ አንቀፅ 313 መሠረት ተከሰው ጥፋተኛ በተባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው በዚህ ድንጋጌ መሠረት ነው፡፡

2. በወንጀል ህጉ አንቀፅ 313 ቅጣት ለመወሰን የአንቀጹን ማቋቋሚያዎች እንዲሁም የነበረው ሃላፊነት እና ማዕረግ፤ በሠራዊቱ ላይ የደረሰ ጉዳት መካከለኛ/ጉዳት፤ በጋራ/ብቻውን ዕጅ መስጠቱን ሁሉ መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ንዑስ አንቀፁ ሁለት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 313(ሀ) | 1 | ጥፋተኛው መቶ መሪ ወይም ተመጣጣኝ ደረጃ ላይ ያለ፤ የጓድ አመራር ወይም ተመጣጣኝ ደረጃ ላይ ያለ ወይም አዲስ ወታደር ከሆነ፤ የመቶዋን አባላት አስተባብሮ ወይም የቲሙን አባላት አስተባብሮ በጋራ ዕጅ የሰጡ ወይም የቡድን መሳሪያ አብሮ ዕጅ እንዲተላለፍ ከተደረገ፤ በራሱ ብቻውን ዕጅ የሰጠ/የነፍስ ወከፍ መሳሪያ ከያዘ፤ ወይም ሌላው በንዑስ ድንጋጌው የተመለከተውን ከተፈፀመ፤ የደረሰው ጉዳት በአሃድ፣ በክፍልና በሃገር ላይ ከፍተኛ ወይም በታች ከሆነ፡፡ | 44 |
| 313(ሀ) | 2 | ሻምበል አመራር እና በላይ ወይም ተመጣጣኝ ደረጃ ላይ ያለ ከሆነ፤ የደረሰው ጉዳት በአሃድ፣ በክፍልና በሃገር ላይ በጣም ከፍተኛ ከሆነ፤ እንደክፍል እጅ እንዲሰጡ ከተደረገ፤ ወይም ሌላው በንዑስ ድንጋጌው የተመለከተውን ከተፈፀመ፤ ከባድ መሳሪያ በጠላት እጅ እንዲወድቅ ከተደረገ፡፡ | 45 |
| 313(ለ) | 3 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው የተፈፀመው በደረጃ 1 በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 44 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 313(ለ) | 4 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው የተፈፀመው በደረጃ 2 በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 45 |
| 313(ሐ) | 5 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው የተፈፀመው በደረጃ 1 በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 44 |
| 313(ሐ) | 6 | በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው የተፈፀመው በደረጃ 2 በተመለከተው አግባብ ከሆነ፡፡ | 45 |

## 22. የቆሰለ ወይም የተሰዋ አባልን ትቶ መሄድ- (የወንጀል ህግ አንቀፅ 316)

1. በወንጀል ህግ አንቀፅ 316 መሠረት ተከሰው ጥፋተኛ በተባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው በዚህ ድንጋጌ መሠረት ነው፡፡

2. በወንጀል ህጉ አንቀፅ 316 ደረጃ ለመወሰን የአንቀጹን ማቋቋሚያዎች እንዲሁም የጥፋተኛው ኃላፊነት ደረጃ፤ በጠላት እጅ የወደቀ/የሞተ ቁስለኛ ብዛት፤ ሳይወጣ የቀረው አመራር ወይም የአመራር አስከሬን መሆኑ፤ የሃኪሙ የአገልግሎት ዘመን (ልምድ)፤ ወንጀሉ በሀገር ጥቅም ወይም በሰራዊቱ ሞራል ያስከተለው ጉዳት ከፍተኛነት ሁሉ መሰረት ተደርጎ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው 12 የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 316/1 | 1 | ጥፋተኛው አዲስ ወታደር ከሆነ፡፡ | 10 |
| 316/1 | 2 | ጥፋተኛው የጓድ  አመራር ወይም ተመጣጣኝ ደረጃ ያለ ከሆነ፤ | 15 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ሁለት ሆነው የፈፀሙት ከሆነ፡፡ | |
| 316/1 | 3 | ጥፋተኛው የመቶ መሪ ወይም ተመጣጣኝ ደረጃ ያለ ከሆነ፤<br>በቡድን ከሁለት በላይ ሆነው ከሆነ፤<br>ሳይወጣ የቀረው መካከለኛ አመራር ወይም የመካለኛ አመራር አስከሬን ከሆነ፡፡ | 20 |
| 316/1 | 4 | ሻምበል አመራር፣ ሻለቃ አመራር ወይም በላይ እና ተመጣጣኝ ደረጃ ያለ ከሆነ፤<br>ሳይወጣ የቀረው ከፍተኛ አመራር ወይም የከፍተኛ አመራር አስከሬን ከሆነ፡፡ | 27 |
| 316/2 | 5 | የወታደር ሃኪሙ ከ10 ዓመት በታች የሠራዊት የአገልግሎት ዘመን ያለው ከሆነ፤<br>በአንድ ቁስለኛ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰ፡፡ | 10 |
| 316/2 | 6 | የወታደር ሃኪሙ ከ10 ዓመት በላይ የሠራዊት የአገልግሎት ዘመን ያለው ከሆነ፤<br>አንድ ቁስለኛ ከሞተ፡፡ | 15 |
| 316/2 | 7 | በንዑስ ድንጋጌው አግባብ ባለመፈፀሙ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰው በሁለት ወይም በላይ ቁስለኞች ላይ ከሆነ ፡፡ | 20 |
| 316/2 | 8 | በንዑስ ድንጋጌው አግባብ ባለመፈፀሙ ሁለት ወይም በላይ ቁስለኛ ከሞተ፡፡ | 27 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 316/3 | 9 | ወንጀሉ በሀገር ጥቅም ወይም በሰራዊቱ ሞራል ላይ ከፍተኛ ጉዳትን ያስከተለ እና በደረጃ 1 ወይም 2 በተመለከተው አግባብ ተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 44 |
| 316/3 | 10 | ወንጀሉ በሀገር ጥቅም ወይም በሰራዊቱ ሞራል ላይ ከፍተኛ ጉዳትን ያስከተለ እና በደረጃ 3 ወይም 4 በተመለከተው አግባብ ተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 45 |
| 316/3 | 11 | ወንጀሉ በሀገር ጥቅም ወይም በሰራዊቱ ሞራል ላይ ከፍተኛ ጉዳትን ያስከተለ እና በደረጃ 5 ወይም 6 በተመለከተው አግባብ ተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 44 |
| 316/3 | 12 | ወንጀሉ በሀገር ጥቅም ወይም በሰራዊቱ ሞራል ላይ ከፍተኛ ጉዳትን ያስከተለ እና በደረጃ 7 ወይም 8 በተመለከተው አግባብ ተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 45 |

## ርዕስ ሶስት

## በታወቁ ገንዘቦች፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች፣ ማህተሞች፣ ቴምብሮች ወይም መሳሪያዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

### የሐሰት ገንዘብ፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች መስራት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 356-362)

**23. ጠቅላላ**

1. በዚህ *መመሪያ* በወንጀል ህግ አንቀጽ 356-362 የሐሰት ገንዘብ፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች ጋር በተያያዘ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

2. የወንጀል ህግ አንቀጽ 362 ተግባራዊ የሚሆነው ከወንጀል ህግ አንቀጽ 356-361 የሚገኙትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የሚፈጸም ወንጀል የገንዘቡ ግምት አንስተኛ ግምት የሚሰጠው ሆኖ ወንጀሉ ቀላል በሚሆንበት ጊዜ በመሆኑ ለዚህ ርዕስ አፈጻጸም እስከ ብር 2,000.00 / ሁለት ሺህ ብር/ ግምት ያላቸው ወንጀሎች አንስተኛ ግምት ያላቸው ተደርገው ተወስደዋል፡፡

3. በወንጀል ህግ አንቀጽ 356-362 መሰረት ቅጣት ለመወሰን በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበው የገንዘቡ ወይም ንብረቱ ጥቅም ግምትን መሰረት በማድረግ የጥቅሙን መጨመር ታሳቢ ባደረገ መልኩ እንዲሁም ወንጀሉ በቀላል ሁኔታ ከተደረገ ተፈጻሚነት ካለው የወንጀል ህግ አንቀጽ 362 ጋር መጣመር ለሚገባቸው ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ለእያንዳንዳቸው አራት፣ ለወንጀል ህግ አንቀጽ 356 አስራ ሁለት፣ ለወንጀል ህግ አንቀጽ 357 አስራ ሁለት ፣ ለወንጀል ህግ አንቀጽ 358 አስራ ሁለት፣ ለወንጀል ህግ አንቀጽ 359 አስራ ሁለት፣ ለወንጀል ህግ አንቀጽ 361/1/ሀ ስድስት፣ ለወንጀል ህግ አንቀጽ 361/1/ለ ስድስት ፣ ለወንጀል ህግ አንቀጽ 361/2/ሀ ስድስት እና ለወንጀል ህግ አንቀጽ 361/2/ለ ስድሰት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

4. የወንጀል ህግ አንቀጽ 361/2/ሀ የሚደነግገው ቅጣት የወንጀል ህግ አንቀጽ 362 ስር እንደተመለከተው ቀላል እስራት በመሆኑ እና የወንጀል ህግ አንቀጽ 361/2/ለ

የሚደነግገው ቅጣት የገንዘብ መቀጮ በመሆኑ ሁለቱን ድንጋጌዎች ከወንጀል ህግ አንቀጽ 362 ጋር ማጣመር ሳያስፈልግ ራሳቸውን ችለው የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡

**24. መስራት (የወንጀል ህግ አንቀጽ 356 እና 362)**

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ (በ ኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 356 እና 362 | 1 | እስከ 500.00 | 4 |
| 356 እና 362 | 2 | ከ 501.00 - 1,000.00 | 6 |
| 356 እና 362 | 3 | ከ 1,001.00 - 1,500.00 | 8 |
| 356 እና 362 | 4 | ከ 1,501.00 - 2,000.00 | 10 |

25. መስራት (የወንጀል ህግ አንቀጽ 356)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ (በ ኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 356 | 1 | ከ 2,001.00 - 10,000.00 | 22 |
| 356 | 2 | ከ 10,001.00 - 25,000.00 | 24 |
| 356 | 3 | ከ 25,001.00 - 50,000.00 | 26 |
| 356 | 4 | ከ 50,001.00 - 75,000.00 | 28 |
| 356 | 5 | ከ 75,001.00 - 100,000.00 | 30 |
| 356 | 6 | ከ 100,001.00 - 150,000.00 | 32 |
| 356 | 7 | ከ 150,001.00 - 200,000.00 | 34 |
| 356 | 8 | ከ 200,001.00 - 250,000.00 | 36 |
| 356 | 9 | ከ 250,001.00 - 300,000.00 | 38 |
| 356 | 10 | ከ 300,001.00 - 400,000.00 | 40 |
| 356 | 11 | ከ 400,001.00 - 500,000.00 | 42 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 356 | 12 | ከ 500,000.00 በላይ | 43 |

26. ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ (የወንጀል ህግ አንቀጽ 357 እና 362)

| የወንጀል ግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ (በ ኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 357 እና 362 | 1 | እስከ 500.00 | 4 |
| 357 እና 362 | 2 | ከ 501.00 - 1,000.00 | 6 |
| 357 እና 362 | 3 | ከ 1,001.00 - 1,500.00 | 8 |
| 357 እና 362 | 4 | ከ 1,501.00 - 2,000.00 | 10 |

27. ወደ ሐሰተኛነት መለወጥ (የወንጀል ህግ አንቀጽ 357)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ (በ ኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 357 | 1 | ከ 2,001.00 - 10,000.00 | 13 |
| 357 | 2 | ከ 10,001.00 - 25,000.00 | 15 |
| 357 | 3 | ከ 25,001.00 - 50,000.00 | 17 |
| 357 | 4 | ከ 50,001.00 - 75,000.00 | 19 |
| 357 | 5 | ከ 75,001.00 - 100,000.00 | 21 |
| 357 | 6 | ከ 100,001.00 - 150,000.00 | 23 |
| 357 | 7 | ከ 150,001.00 - 200,000.00 | 25 |
| 357 | 8 | ከ 200,001.00 - 250,000.00 | 27 |
| 357 | 9 | ከ 250,001.00 - 300,000.00 | 29 |
| 357 | 10 | ከ 300,001.00 - 400,000.00 | 31 |
| 357 | 11 | ከ 400,001.00 - 500,000.00 | 33 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 357 | 12 | ከ 500,000.00 በላይ | 35 |

28. ዋጋዉን ዝቅ ማድረግ (የወንጀል ህግ አንቀጽ 358 እና 362)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ (በ ኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 358 እና 362 | 1 | እስከ 500.00 | 4 |
| 358 እና 362 | 2 | ከ 501.00 - 1,000.00 | 6 |
| 358 እና 362 | 3 | ከ 1,001.00 - 1,500.00 | 8 |
| 358 እና 362 | 4 | ከ 1,501.00 - 2,000.00 | 10 |

29. ዋጋዉን ዝቅ ማድረግ (የወንጀል ህግ አንቀጽ 358)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ (በ ኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 358 | 1 | ከ 2,001.00 - 10,000.00 | 8 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 358 | 2 | ከ 10,001.00 - 25,000.00 | 10 |
| 358 | 3 | ከ 25,001.00 - 50,000.00 | 12 |
| 358 | 4 | ከ 50,001.00 - 75,000.00 | 14 |
| 358 | 5 | ከ 75,001.00 - 100,000.00 | 16 |
| 358 | 6 | ከ 100,001.00 - 150,000.00 | 18 |
| 358 | 7 | ከ 150,001.00 - 200,000.00 | 20 |
| 358 | 8 | ከ 200,001.00 - 250,000.00 | 22 |
| 358 | 9 | ከ 250,001.00 - 300,000.00 | 24 |
| 358 | 10 | ከ 300,001.00 - 400,000.00 | 26 |
| 358 | 11 | ከ 400,001.00 - 500,000.00 | 28 |
| 358 | 12 | ከ 500,000.00 በላይ | 30 |

30. ወደ ሀገር ማስገባት፣ ከሀገር ማስወጣት፣ መያዝ፣ ማስቀመጥ እና ማቅረብ (የወንጀል ህግ አንቀጽ 359 እና 362)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ (በ ኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 359 እና 362 | 1 | እስከ 500.00 | 4 |
| 359 እና 362 | 2 | ከ 501.00 - 1,000.00 | 6 |
| 359 እና 362 | 3 | ከ 1,001.00 - 1,500.00 | 8 |
| 359 እና 362 | 4 | ከ 1,501.00 - 2,000.00 | 10 |

31. ወደ ሀገር ማስገባት፣ ከሀገር ማስወጣት፣ መያዝ፣ ማስቀመጥ እና ማቅረብ (የወንጀል ህግ አንቀጽ 359)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ (በ ኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|

| | | | |
|---|---|---|---|
| 359 | 1 | ከ 2,001.00 - 10,000.00 | 13 |
| 359 | 2 | ከ 10,001.00 - 25,000.00 | 15 |
| 359 | 3 | ከ 25,001.00 - 50,000.00 | 17 |
| 359 | 4 | ከ 50,001.00 - 75,000.00 | 19 |
| 359 | 5 | ከ 75,001.00 - 100,000.00 | 21 |
| 359 | 6 | ከ 100,001.00 - 150,000.00 | 23 |
| 359 | 7 | ከ 150,001.00 - 200,000.00 | 25 |
| 359 | 8 | ከ 200,001.00 - 250,000.00 | 27 |
| 359 | 9 | ከ 250,001.00 - 300,000.00 | 29 |
| 359 | 10 | ከ 300,001.00 - 400,000.00 | 31 |
| 359 | 11 | ከ 400,001.00 - 500,000.00 | 33 |
| 359 | 12 | ከ 500,000.00 በላይ | 35 |

32. ማዘዋወር (የወንጀል ህግ አንቀጽ 361/1/ሀ እና 362)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ (በ ኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 361(1)ሀ እና 362 | 1 | እስከ 500.00 | 4 |
| 361(1)(ሀ) እና 362 | 2 | ከ 501.00 - 1,000.00 | 6 |
| 361(1)(ሀ) እና 362 | 3 | ከ 1,001.00 - 1,500.00 | 8 |
| 361(1)(ሀ) እና 362 | 4 | ከ 1,501.00 - 2,000.00 | 10 |

33. ማዘዋወር (የወንጀል ህግ አንቀጽ 361/1/ሀ)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ (በ ኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 361(1)(ሀ) | 1 | ከ 2,001.00 - 50,000.00 | 12 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 361(1)(ሀ) | 2 | ከ 50,001.00 - 100,000.00 | 16 |
| 361(1)(ሀ) | 3 | ከ 100,001.00 - 200,000.00 | 20 |
| 361(1)(ሀ) | 4 | ከ 200,001.00 - 300,000.00 | 24 |
| 361(1)(ሀ) | 5 | ከ 300,001.00 - 500,000.00 | 28 |
| 361(1)(ሀ) | 6 | ከ 500,000.00 በላይ | 31 |

34. **ማዘዋወር (የወንጀል ህግ አንቀጽ 361/1/ለ እና 362)**

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ (በ ኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 361(1)(ለ) እና 362 | 1 | እስከ 500.00 | 4 |
| 361(1)(ለ) እና 362 | 2 | ከ 501.00 - 1,000.00 | 6 |
| 361(1)(ለ) እና 362 | 3 | ከ 1,001.00 - 1,500.00 | 8 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 361(1)(ለ) እና 362 | 4 | ከ 1,501.00 - 2,000.00 | 10 |

35. ማዘዋወር (የወንጀል ህግ አንቀጽ 361/1/ለ)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ (በ ኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 361(1)(ለ) | 1 | እስከ 50,000.00 | 11 | 1 |
| 361(1)(ለ) | 2 | ከ 50,001.00 - 100,000.00 | 13 | 2 |
| 361(1)(ለ) | 3 | ከ 100,001.00 - 200,000.00 | 15 | 3 |
| 361(1)(ለ) | 4 | ከ 200,001.00 - 300,000.00 | 17 | 4 |
| 361(1)(ለ) | 5 | ከ 300,001.00 - 500,000.00 | 19 | 5 |
| 361(1)(ለ) | 6 | ከ 500,001.00 በላይ | 21 | 5 |

36. ማዘዋወር (የወንጀል ህግ አንቀጽ 361/2/ሀ)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ (በ ኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 361(2)(ሀ) | 1 | እስከ 50,000.00 | 4 |
| 361(2)(ሀ) | 2 | ከ 50,001.00 - 100,000.00 | 6 |
| 361(2)(ሀ) | 3 | ከ 100,001.00 - 200,000.00 | 8 |
| 361(2)(ሀ) | 4 | ከ 200,001.00 - 300,000.00 | 10 |
| 361(2)(ሀ) | 5 | ከ 300,001.00 - 500,000.00 | 12 |
| 361(2)(ሀ) | 6 | ከ 500,001.00 በላይ | 14 |

37. ማዘዋወር (የወንጀል ህግ አንቀጽ 361/2/ለ)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ (በ ኢትዮጵያ ብር) | የገንዘብ መቀጮ ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 361(2)(ለ) | 1 | እስከ 50,000.00 | 1 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 361(2)(ለ) | 2 | ከ 50,001.00 - 100,000.00 | 2 |
| 361(2)(ለ) | 3 | ከ 100,001.00 - 200,000.00 | 3 |
| 361(2)(ለ) | 4 | ከ 200,001.00 - 300,000.00 | 4 |
| 361(2)(ለ) | 5 | ከ 300,001.00 - 500,000.00 | 5 |
| 361(2)(ለ) | 6 | ከ 500,001.00 በላይ | 5 |

## ርዕስ አራት

## በሰው እና በእንስሳት ጤና ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮችን በማምረት እና በማሰራጨት የሚደረጉ ወንጀሎች

## መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒቶችን ወይም እፆችን ማምረት፣ መስራት፣ ማዘዋወር፣ ወይም መጠቀም፡፡

**38. ጠቅላላ**

1. መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒቶችን ወይም እፆችን ማምረት፣ መስራት፣ ማዘዋወር፣ ወይም መጠቀም ወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ በሚባሉ ሰዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው በሚከተሉት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

2. በወንጀል ህግ አንቀጽ 525(1) ድንጋጌዎች ለክስ ምክንያት የሆነውን መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒትን ወይም እፅን ዓይነት፣ አደገኝነት እና ብዛት(መጠን) መሠረት በማድረግ እና በ አንቀጽ 525(2) ከ “ሀ” እስከ “ሠ” ስር ከተዘረዘሩ ማክበጃ ምክንያቶች ጋር በማያያዝ 10 ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል።

3. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(3) የተደነገገው ቅጣት ከ ወንጀል ህግ አንቀጽ 525(1) ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ፣ ለሁለቱም የወንጀል ድንጋጌዎች ከ ደረጃ 1 እስከ 4 ተመሳሳይ ደረጃ ወጥቶላቸዋል፡፡

4. በዚህ መመሪያ በወጣው ደረጃ የተካተቱት መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት ወይም እፅ ዓይነቶች ሄሮይን ፣ኮኬይን እና ካናቢስ ብቻ ናቸው፡፡

5. በዚህ መመሪያ ደረጃ ከወጣላቸው ውጭ ሌሎች መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒቶች በሚያጋጥሙበት ጊዜ፣ ለክስ ምክንያት የሆነውን እፅ(መድሃኒት) አደገኝነት መሰረት በማድረግ ደረጃ ከወጣላቸው ውስጥ ይበልጥ የሚቀርበውን ደረጃ በመያዝ ቅጣት ይወሰናል፡፡

6. በዚህ መመሪያ ለ ወንጀል ሕግ አንቀጽ ለ 525(1) እና 525(2) እና 525(3) የተመለከቱ የወንጀል ደረጃዎች አተገባበር፣

ሀ. "በጣም ከፍተኛ ደረጃ" ፡- ማለት ለ ወንጀሉ ምክንያት የሆነው መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት ወይም እፆ፤

- መጠኑ 2 ኪሎ ግራም እና ከዚያ በላይ ሄሮይን ከሆነ ወይም፣
- መጠኑ 2 ኪሎ ግራም እና ከዚያ በላይ ኮኬይን ከሆነ ወይም፣
- መጠኑ ከ 50 ኪሎ ግራም በላይ ካናቢስ ከሆነ

ለ. "ከፍተኛ ደረጃ"፡- ማለት ለ ወንጀሉ ምክንያት የሆነው መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት ወይም እፆ፤

- መጠኑ ከ 250 ግራም እስከ 1.99 ኪሎ ግራም ሄሮይን ከሆነ ወይም፣
- መጠኑ ከ 250 ግራም እስከ 1.99 ኪሎግራም ኮኬይን ከሆነ ወይም፣
- መጠኑ ከ 25 ኪሎግራም እስከ 49 ኪሎግራም ካናቢስ ከሆነ ወይም፣

ሐ. "መካከለኛ ደረጃ"፡- ማለት ለ ወንጀሉ ምክንያት የሆነው መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት ወይም እፆ፤

- መጠኑ ከ 50 ግራም እስከ 249 ግራም ሄሮይን ከሆነ ወይም፣
- መጠኑ ከ 99 ግራም እስከ 249 ግራም ኮኬይን ከሆነ ወይም፣
- መጠኑ ከ 1 ኪሎ ግራም እስከ 24 ኪሎ ግራም ካናቢስ ከሆነ ወይም፣

መ. "ዝቅተኛ ደረጃ"፡- ማለት ለ ወንጀሉ ምክንያት የሆነው መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት ወይም እፆ፤

- መጠኑ ከ 50 ግራም በታች ሄሮይን ከሆነ ወይም፣
- መጠኑ ከ 50 ግራም በታች ሄሮይን ከሆነ ወይም፣
- መጠኑ ከ 1 ኪሎግራም በታች ካናቢስ ከሆነ

7. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(1)፣(2) እና (3) አተገባበር  የክስ ምክንያት የሆነው መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት በዚህ መመሪያ “በጣም ከፍተኛ” ደረጃን ለመወሰን ከተመለከተው  ዝቅተኛ መመዘኛ ጋር ሲነፃፀር  ሰፊ ልዩነት ያለው መጠን የሚጋጥም ከሆነ፣ ፍ/ቤቱ በመመሪያው ከተቀመጠው መነሻ የቅጣት እርከን ላይ ለወንጀሉ ክብደት ተገቢ ሆኖ እስካገኘው  እርከን ድረስ ከፍ በማድረግ መነሻ ቅጣት ይወስናል ፡፡

8. ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(4) (ሀ) እና (ለ) ለክስ ምክንያት የሆነውን መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒትን ወይም እፅን ዓይነት፣ አደገኝነት ሁኔታ እና ለግል ጥቅም የሚውል መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት  መጠን ስንት እንደሆነ የሚወስን ዝቅተኛ መመዘኛ (threshold ) እና ወንጀሉ የተፈፀመበትን ቦታ  መሰረት በማድረግ  ስምንት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

9. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(4) (ሀ) እና (ለ) በተመለከተ፣በመመሪያው ከተቀመጠው ለግል ጥቅም የሚውል መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት ከተቀመጠው መጠን ስንት እንደሆነ ለመወሰን ከተቀመጠው ዝቅተኛ መመዘኛ ጋር ሲነፃፀር ሰፊ ልዩነት ያለው መጠን የሚጋጥም ከሆነ፣ ፍ/ቤቱ በመመሪያው ከተቀመጠው መነሻ የቅጣት እርከን ላይ እስከ ሶስት እርከን ከፍ በማድረግ መነሻ ቅጣት ሊወስን ይችላል፡፡

10. በአንድ የወንጀል ክስ በመመሪያው ደረጃ ከወጣላቸው መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት ዓይነቶች ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ በሚገኙበት ጊዜ ፤ ፍ/ቤቱ ይበልጥ አደገኛ ለሆነው  የአደንዛዥ እፅ(መድሃኒት) ዓይነት የተዘጋጀውን  እርከን ላይ ለሌላኛው አደገኛ እፅ (መድሃኒት)   ተገቢ ሆኖ እስካገኘው  እርከን ድረስ  በማድረግ መነሻ ቅጣት ይወስናል፡፡

11. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(5) የወንጀል ፈጻሚዉን ሁኔታ መሰረት በማድረግ 3 ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

39. የወንጀል ሕግ አንቀጽ፣ 525(1) ፣ 525(2) እና 525(3)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀል ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 525(1) ፣ 525(3) | 1 | ማንም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው በ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(1) ከ "ሀ" እስከ "መ" ባሉት ንኡሳን ድንጋጌዎች የተከለከሉትን ተግባራት አንዱን ፈፅሞ ለ ወንጀሉ ምክንያት የሆነው መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት ወይም እፆ ዝቅተኛ ደረጃ ከሆነ፡ | 23 | 3 |
| 525(1) ፣ 525(3) | 2 | በ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(1) ከ "ሀ" እስከ "መ" ባሉት ንኡሳን ድንጋጌዎች የተከለከሉትን ተግባራት አንዱ ተፈፅሞ፤ ለ ወንጀሉ ምክንያት የሆነው መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት ወይም እፆ መካከለኛ ደረጃ ከሆነ፡፡ | 26 | 6 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 525(1) ፤ 525(3) | 3 | በ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(1) ከ “ሀ” እስከ “መ” ባሉት ንኡሳን ድንጋጌዎች የተከለከሉትን ተግባራት አንዱ ተፈፅሞ፤ ለ ወንጀሉ ምክንያት የሆነው መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት ወይም እፆ ከፍተኛ ደረጃ ከሆነ፡፡ | 29 | 8 |
| | 4 | በ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(1) ከ “ሀ” እስከ “መ” ባሉት ንኡሳን ድንጋጌዎች የተከለከሉትን ተግባራት አንዱ ተፈፅሞ ፤ ለ ወንጀሉ ምክንያት የሆነው መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት ወይም እፆ በጣም ከፍተኛ ደረጃ ከሆነ:: | 31 | 9 |
| 525(1) እና 525(2) | 5 | ወንጀሉ በደረጃ-1 እንደተመለከተው ሆኖ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(2) “ሀ” እስከ “ሠ” ከተዘረዘሩት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱን የሚያሟላ ከሆነ: | 34 | 10 |
| 525(1) እና 525(2) | 6 | ወንጀሉ በደረጃ-2 እንደተመለከተው ሆኖ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(2) ከ “ሀ” እስከ “ሠ” ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱን የሚያሟላ ከሆነ፡፡ | 36 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወይም<br><br>ድርጊቱ በደረጃ-1 እንደተመለከተው ሆኖ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(2) ከ “ሀ” እስከ “ሠ” ከተዘረዘሩት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱን የሚያሟላ ከሆነ፡፡ | | |
| | 7 | ወንጀሉ በደረጃ-3 እንደተመለከተው ሆኖ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(2) “ሀ” እስከ “ሠ” ከተዘረዘሩት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱን የሚያሟላ ከሆነ፡፡<br><br>ወይም<br><br>ወንጀሉ በደረጃ-2 እንደተመለከተው ሆኖ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(2) ከ “ሀ” እስከ “ሠ” ከተዘረዘሩት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱን የሚያሟላ ከሆነ፡፡<br><br>ወይም<br><br>ወንጀሉ በደረጃ-1 እንደተመለከተው ሆኖ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(2) ከ “ሀ እስከ “ሠ” ከተዘረዘሩት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ከሶስት በላይ የሚያሟላ ከሆነ፡፡ | 38 | 11 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 8 | ወንጀሉ በደረጃ-4 እንደተመለከተው ሆኖ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(2) "ሀ" እስከ "ሠ" ከተዘረዘሩት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱን የሚያሟላ ከሆነ፡፡<br><br>ወይም<br><br>ወንጀሉ በደረጃ-3 እንደተመለከተው ሆኖ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(2) ከ "ሀ" እስከ "ሠ" ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱን የሚያሟላ ከሆነ ፡፡<br><br>ወይም<br><br>ወንጀሉ በደረጃ-2 እንደተመለከተው ሆኖ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(2) ከ "ሀ" እስከ "ሠ" ከተዘረዘሩት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ከሶስት በላይ የሚያሟላ ከሆነ፡፡ | 40 | 12 |
| | 9 | ወንጀሉ በደረጃ - 4 እንደተመለከተው ሆኖ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(2) "ሀ" እስከ "ሠ" ከተዘረዘሩት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱን የሚያሟላ ከሆነ፡፡<br><br>ወይም<br><br>ወንጀሉ በደረጃ-3 እንደተመለከተው ሆኖ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(2) ከ "ሀ" እስከ | 41 | 13 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | “ሠ” ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ከሶስት በላይ የሚያሟላ ከሆነ፡፡ | | |
| | 10 | ወንጀሉ በደረጃ-4 እንደተመለከተው ሆኖ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(2) “ሀ” እስከ “ሠ” ከተዘረዘሩት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ከሶስት በላይ የሚያሟላ ከሆነ፡፡ | 42 | 14 |

40. **የወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(4)(ሀ)፣(ለ)**

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀል ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 525(4)(ሀ)፣(ለ) | 1 | ማንኛውም ሰው ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው በግል እንዲጠቀምበት በማሰብ በድንጋጌው የተከለከሉትን ተግባራት ፈፅሞ፣ለወንጀል ክስ ምክንያት የሆነው መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት መጠኑ 14.99 ግራም እና ከዚያ በታች ካናቢስ ከሆነ፡፡ | 10 | 1 |
| 525(4)(ሀ)፣(ለ) | 2 | ወንጀሉ በደረጃ-1 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ለወንጀል ክስ ምክንያት የሆነው መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት | 12 | 2 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | መጠኑ 15.00 ግራም እና ከዚያ በላይ ካናቢስ ከሆነ:: | | |
| 525(4)(ሀ)፣ (ለ) | 3 | ወንጀሉ በደረጃ 1 እንደተመለከተው ሆኖ፣ የተፈፀመው በማረሚያ ቤት፣ በትምህርት ቤት፣ ማህበራዊ አገልግሎት ተቋም ቅጥር ግቢ ውስጥ ፣ ህፃናት ወይም ወጣት ተማሪዎች ለ ትምህርት፣ለስፖርት ወይም ለሌሎች ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች በሚጠቀሙበት ቦታ እንደሆነ፡፡ | 14 | 3 |
| 525(4)(ሀ)፣ (ለ) | 4 | ወንጀሉ በደረጃ 2 እንደተመለከተው ሆኖ፣ የተፈፀመው በማረሚያ ቤት፣ በትምህርት ቤት፣ ማህበራዊ አገልግሎት ተቋም ቅጥር ግቢ ውስጥ ፣ ህፃናት ወይም ወጣት ተማሪዎች ለ ትምህርት፣ለስፖርት ወይም ለሌሎች ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች በሚጠቀሙበት ቦታ እንደሆነ፡፡ | 16 | 4 |
| 525(4)(ሀ)፣ (ለ) | 5 | ማንኛውም ሰው ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው በግል እንዲጠቀምበት በማሰብ በድንጋጌው የተከለከሉትን ተግባራት ፈፅሞ፣ለወንጀል ክስ ምክንያት የሆነው መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት መጠኑ 49.99 ሚሊግራም እና ከዚያ በታች ሄሮይን ወይም ኮኬይን ከሆነ፡፡ | 18 | 5 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 525(4) )(ሀ)፣ (ለ) | 6 | ወንጀሉ በደረጃ-5 እንደተመለከተው ሆኖ፣ለወንጀል ክስ ምክንያት የሆነው መርዛማ ወይም የናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒት መጠኑ 50.00 ሚሊግራም እና ከዚያ በላይ ሄሮይን ወይም ኮኬይን ከሆነ፡፡ | 21 | 6 |
| 525(4) )(ሀ)፣ (ለ) | 7 | ወንጀሉ በደረጃ 5 እንደተመለከተው ሆኖ፣ የተፈፀመው በማረሚያ ቤት፣ በትምህርት ቤት፣ ማህበራዊ አገልግሎት ተቋም ቅጥር ግቢ ውስጥ ፣ ህፃናት ወይም ወጣት ተማሪዎች ለ ትምህርት፣ለስፖርት ወይም ለሌሎች ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች በሚጠቀሙበት ቦታ ከሆነ፡፡ | 23 | 7 |
| 525(4) )(ሀ)፣ (ለ) | 8 | ወንጀሉ በደረጃ 6 እንደተመለከተው ሆኖ፣ የተፈፀመው በማረሚያ ቤት፣ በትምህርት ቤት፣ ማህበራዊ አገልግሎት ተቋም ቅጥር ግቢ ውስጥ ፣ ህፃናት ወይም ወጣት ተማሪዎች ለ ትምህርት፣ለስፖርት ወይም ለሌሎች ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች በሚጠቀሙበት ቦታ ከሆነ፡፡ | 25 | 8 |

## 41. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(5)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀል ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| የወንጀል ሕግ | 1 | ማንኛውም ሰው ናርኮቲክ ወይም ሳይኮትራፒክ ነገሮችን ለህገ ወጥ ዓላማ | 10 | 1 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አንቀጽ 525(5) | | ለማዋል በማሰብ የህክምና ባለሙያን በማጭበርበር የመድኃኒት ማዘዣ እንዲሰጠው ያደረገ ከሆነ፡፡ | | |
| የወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(5) | 2 | ከላይ በደረጃ 1 የተመለከተውን በህጋዊም ሆነ በህገ ወጥ መንገድ ያገኘውን ማዘዣ ላልተፈቀደለት ሶስተኛ ወገን ያስተላለፈ ከሆነ፡፡ | 14 | 3 |
| የወንጀል ሕግ አንቀጽ 525(5) | 3 | ከላይ በደረጃ 1 የተመለከተውን ነገሮች ማዛዣ አስቦ በህገ ወጥ መንገድ የጻፈ ህክምና ባለሙያ ከሆነ፡፡ | 18 | 5 |

## ርዕስ አምስት

## በሰው ሕይወት፣ አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

### ምዕራፍ አንድ

### በሰው ሕይወት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

42. **በሰው ሕይወት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (የወንጀል ህግ አንቀጽ 539-543)**

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ህግ አንቀጽ 539-543 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

2. በወንጀል ህጉ አንቀጽ 539 ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ቅጣቱን ለመወሰን በእያንዳንዱ ድንጋጌ ስር ያሉትን የወንጀሉን ማቋቋሚያ ነጥቦች፣ የነጥቦቹን ተደራርቦ መገኘትና የወንጀሉ ድርጊት አፈጻጸም ከባድ ወይም በጣም ከባድ መሆኑን መሰረት በማድረግ ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ በዚህ መሰረት የወንጀል ህግ አንቀጽ 539/1 ከፊደል “ሀ” እስከ “ሐ” ለተመለከቱት ንዑስ ድንጋጌዎች ለእያንዳንዳቸው ሁለት ደረጃዎች የተዘጋጁ ሲሆን፣ ለአንቀፁ ንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ ቅጣቱ አማራጭ የሌለው በመሆኑ አንድ ደረጃ ብቻ እንዲኖረው ተደርጓል፡፡

3. በወንጀል ህግ አንቀጽ 539 (1)(ለ) እና (ሐ) ስር ለተመለከቱት ድንጋጌዎች ደረጃዎችን ለመለየት ፍርድ ቤቱ  አስቀድሞ የወንጀሉ አፈጻጸም ከባድ ወይም በጣም ከባድ መሆን ያለመሆኑን ሊወስን ይገባል፡፡

4. የወንጀል አፈጻጸሙ በጣም ከባድ ወይም ከዚያ በመለስ ስለመሆኑ  ለመለየትና ቅጣት ለመወሰን፣ ከድንጋጌው በተጨማሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 117/1 መስፈርቶችን ታሳቢ በማድረግ መሆን ይኖርበታል፡፡

5. ለወንጀል ህግ አንቀጽ 540 ድንጋጌ በወንጀል ህግ አንቀጽ 539 የተመለከተውን ያህል ከባድ እንዲሁም በአንቀጽ 541 የተመለከተውን ያህል ቀላል አለመሆኑን በመግለጽ ህግ አውጭው ያስቀመጠውን ድንጋጌ መሰረት በማደረግ የወጡ መስፈርቶችን፣ ማለትም የወንጀል ድርጊት መፈፀም መንስኤ የሆነው ሰው ማንነት ፣ ወንጀሉን ለመፈፀም

የተጠቀመው ገዳይ መሳሪያ ወይም ዘዴ መኖር/አለመኖር ፣ ሟች ጥፋተኛ ከተባለው ሰው ጋር የሩቅ ዝምድና ወይም ማህበራዊ ቅርርብ ያለው መሆን/አለመሆኑን ፣ መሰረት በማድረግ ስምንት የወንጀል ደረጃዎች እንዲኖሩት ተደርጓል፡፡

6. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ስር ቅጣት ሲወሰን፣ ድርጊቱ በወንጀል ህግ አንቀጽ 539 እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 541 ከሚሸፈኑ ድርጊቶች ውጭ በመሆኑ በወንጀል ህግ አንቀጽ 82/1/መ ስር ያለው የተበዳይ ለድርጊቱ መንስኤ መሆን በጠቅላላ ቅጣት ማቅለያነት የሚያዝ አይሆንም፡፡

7. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 በተመለከተ፣ በሟች እና ጥፋተኛ በተባለው ሰው መካከል የሩቅ ዝምድና መኖር/አለመኖር፣ በፍ/ቤቱ የየአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት በማድረግ የሚወሰን ይሆናል፡፡

8. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 541 (ሀ) ድንጋጌ የአስገዳጅ ሁኔታ መጠን መተላለፍን ለማሳየት የሚችሉ መስፈርቶችን በመጠቀም የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ሆኖም ደረጃዎቹን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የዋሉ መስፈርቶች በድጋሚ ማቅለያ ሆነው ቅጣት ማቅለያ ተደርገው ሊወሰዱ አይችሉም፡፡

9. ለወንጀል ህግ አንቀጽ 541 በድንጋጌው “ለ” ስር ያሉትን ፍሬ ነገሮች መሰረት በማድረግ ሦስት ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ ሆኖም ደረጃዎቹን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የዋሉ መስፈርቶች በድጋሚ ማቅለያ ሆነው ቅጣትን እንዳያቀሉ ፍ/ቤቱ ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

10. ለወንጀል ህግ አንቀጽ 543 በድንጋጌው ውስጥ የተመለከቱትን ፍሬ ነገሮች፣ የቸልተኝነት ሁኔታ እና የሟች አስተዋፅኦ መኖር/አለመኖር መሰረት በማድረግ ለወንጀል ህግ አንቀጽ 543/1 ስድስት፣ ለወንጀል ህግ አንቀጽ 543/2 አራት እና ለወንጀል ህግ አንቀጽ 543/3 አስራ ሦስት ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

11. በፍርድ ቤት በወ/ህ/አ. 543 መሰረት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሲሰጥ የተከሳሽን የቸልተኝነት ሁኔታ በወንጀል ህግ አንቀጽ 59 ስር የተቀመጡትን መስፈርቶች በመጠቀም ቸልተኝነቱ የታወቀ (የወ/ህ/አ.59/1/ሀ) ወይም ያልታወቀ (የወ/ህ/አ.59/1/ለ) መሆኑን መወሰን አለበት፡፡

43. ከባድ የሰው ግድያ (የወንጀል ህግ አንቀጽ 539/1/ሀ)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 539/1/ሀ | 1 | አስቀድሞ በማሰብ የተፈጸመ ሆኖ አፈጻጸሙ ከባድ ከሆነ ወይም በአፈጻጸሙ በወንጀል ህግ አንቀጽ 84/1 ስር የተመለከቱት ፊደሎች ካስቀመጧቸው የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መካከል አንድ ወይም ሁለት ምክንያቶች የተገኙ ከሆነ ወይም በወንጀል ህግ አንቀጽ 86 መሰረት ሊያዝ የሚገባ አንድ ወይም ሁለት ሌላ ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች የተገኘ ከሆነ፡፡ | 44 |
| 539/1/ሀ | 2 | አስቀድሞ በማሰብ የተፈጸመ ሆኖ በወንጀል ህግ አንቀጽ 84 ወይም 86 መሰረት ሊያዙ የሚችሉ ከሁለት በላይ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ከተገኙ ወይም የወንጀሉ አፈጻጸም በጣም ከባድ ከሆነ፡፡ | 45 |

44. ከባድ የሰው ግድያ (የወንጀል ህግ አንቀጽ 539/1/ለ)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 539/1/ለ | 1 | ሰውን ለመግደል ወይም የውንብድና ወንጀልን ለመፈጸም የተደራጀ ወንበዴ ቡድን አባል በመሆን ድርጊቱን መፈጸምና የድርጊቱ አፈጻጸም ከባድ ሆኖ መገኘት፡፡ | 44 |
| 539/1/ለ | 2 | ሰውን ለመግደል ወይም የውንብድና ወንጀልን ለመፈጸም የተደራጀ ወንበዴ ቡድን አባል በመሆን ድርጊቱን መፈጸምና የድርጊቱ አፈጻጸም በጣም ከባድ ሆኖ መገኘት፡፡ | 45 |

45. ከባድ የሰው ግድያ (የወንጀል ህግ አንቀጽ 539/1/ሐ)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 539/1/ሐ | 1 | ሌላ ወንጀል ለመፈጸም እንዲመቸው ወይም የተፈጸመ ወንጀል እንዳይገለጽ ለማድረግ የተፈጸመ መሆኑና አፈጻጸሙ ከባድ ሆኖ መገኘት፡፡ | 44 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 539/1/ሐ | 2 | ሌላ ወንጀል ለመፈጸም እንዲመቸው ወይም የተፈጸመ ወንጀል እንዳይገለጽ ለማድረግ የተፈጸመ መሆኑና አፈጻጸሙ እጅግ በጣም ከባድ ሆኖ መገኘት፡፡ | 45 |

46. ከባድ የሰው ግድያ (የወንጀል ህግ አንቀጽ 539/2)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 539/2 | 1 | ወንጀለኛው የእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ተፈርዶበት ቅጣቱን በመፈጸም ላይ ሳለ በአንቀጽ 539(1) በተመለተከው ሁኔታ ድርጊቱን ከፈጸመ፡፡ | 45 |

47. ተራ የሆነ የሰው ግድያ (የወንጀል ህግ አንቀጽ 540)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 540 | 1 | ለወንጀል ድርጊቱ መፈፀም መንስኤው ሟች ከሆነ እና አጥፊው ምንም ዓይነት ገዳይ መሳሪያ (ዘዴ) ያልተጠቀመ ከሆነ፡፡ | 25 |
| 540 | 2 | በደረጃ 1 የተገለፀው መመዘኛ እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ ሟች የጥፋተኛው | 28 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | የቅርብ ዘመድ ባይሆንም የሩቅ ዝምድና ወይም ማህበራዊ ቅርርብ የነበረው ሰው ከሆነ፡፡ | |
| 540 | 3 | ለወንጀል ድርጊቱ መፈፀም መንስኤው ሟች ከሆነ እና አጥፊው ገዳይ መሳሪያ (ዘዴ) ከተጠቀመ፡፡ | 31 |
| 540 | 4 | በደረጃ 3 የተመለከተው መመዘኛ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሟች የጥፋተኛው የቅርብ ዘመድ ባይሆንም የሩቅ ዝምድና ወይም ማህበራዊ ቅርርብ የነበረው ሰው ከሆነ፡፡ | 34 |
| 540 | 5 | ለወንጀል ድርጊቱ መፈፀም መንስኤው አጥፊው ከሆነ እና ምንም ዓይነት ገዳይ መሳሪያ (ዘዴ) ያልተጠቀመ ከሆነ፡፡ | 37 |
| 540 | 6 | በደረጃ 5 የተመለከተው መመዘኛ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሟች የጥፋተኛው ቅርብ ዘመድ ባይሆንም የሩቅ ዝምድና ወይም ማህበራዊ ቅርርብ የነበረው ሰው ከሆነ፡፡ | 38 |
| 540 | 7 | ለወንጀል ድርጊቱ መፈፀም መንስኤው አጥፊው ከሆነ እና ገዳይ መሳሪያ (ዘዴ) ከተጠቀመ፡፡ | 39 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 540 | 8 | በደረጃ 7 የተመለከተው መመዘኛ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ሟች የጥፋተኛው የቅርብ ዘመድ ባይሆንም የሩቅ ዝምድና ወይም ማህበራዊ ቅርርብ የነበረው ሰው ከሆነ፡፡ | 40 |

48. ቀላል የሆነ የሰው ግድያ(የአስገዳጅ ሁኔታን ወሰን በመተላለፍ ሲፈፀም) (የወንጀል ህግ አንቀጽ 541/ሀ)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 541/ሀ | 1 | ምትን ያስከተለውን ድርጊት ከመፈፀም በአደጋ ላይ ያለውን መብት መስዋእት ማድረግ ተገቢ የነበረ እንደሆነ ወይም ሰው መግደሉ ካስፈላጊው መጠን በላይ ከሆነ፡፡ | 10 |
| 541/ሀ | 2 | በደረጃ -1 የተቀመጠው የተመጣጣኝነት መመዘኛ እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጊት ፈፃሚው የተገኘበት የአስገዳጅ ወይም አደጋ ሁኔታ በራሱ ጥፋት የመጣ እንደሆነ፡፡ | 14 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 541/ሀ | 3 | በደረጃ -1 የተቀመጠው የተመጣጣኝነት መመዘኛ እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጊት ፈፃሚው የሰውን ሕይወት ወይም ደህንነት የመጠበቅ ልዩ የሙያ ግዴታ ያለበት ሰው እንደሆነ፡፡ | 18 |
| 541/ሀ | 4 | በደረጃ -1 የተቀመጠው የተመጣጣኝነት መመዘኛ እንደተጠበቀ ሆኖ፤<br>1. ድርጊት ፈፃሚው የተገኘበት የአስገዳጅ ወይም አደጋ ሁኔታ በራሱ ጥፋት የመጣ እንደሆነ እና<br>2. ድርጊት ፈፃሚው የሰውን ሕይወት ወይም ደህንነት የመጠበቅ ልዩ የሙያ ግዴታ ያለበት ሰው እንደሆነ፡፡ | 21 |

## 49. ቀላል የሆነ የሰው ግድያ (የወንጀል ህግ አንቀጽ 541/ለ)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 541/ለ | 1 | በድንጋጌው ስር በተመለከተው አግባብ ድርጊቱን የፈጸመው ያለምንም ገዳይ መሳሪያ (ዘዴ) ከሆነ፡፡ | 11 |
| 541/ለ | 2 | በድንጋጌው ስር በተመለከተው አግባብ ድርጊቱን የፈጸመው ገዳይ መሳሪያዎች (ዘዴ) በመጠቀም ከሆነ፡፡ | 18 |
| 541/ለ | 3 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈፅሞ አፈፃፀሙ የድርጊቱን አፈፃፀም ከባድነት በሚያሳዩ ሁኔታዎች ከሆነ፡፡ | 21 |

50. በቸልተኝነት ሰው መግደል (የወንጀል ህግ አንቀጽ 543/1)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 543/1 | 1 | የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመው ያለምንም መሳሪያ እና ባልታወቀ ቸልተኝነት ከሆነ፡፡ | 5 | 2 |
| 543/1 | 2 | የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመው ያለምንም መሳሪያ እና በታወቀ ቸልተኝነት ከሆነ፡፡ | 6 | 2 |
| 543/1 | 3 | የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመው አደገኛ ባልሆነ መሳሪያ እና ባልታወቀ ቸልተኝነት ከሆነ፡፡ | 7 | 4 |
| 543/1 | 4 | የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመው አደገኛ ባልሆነ መሳሪያ እና በታወቀ ቸልተኝነት ከሆነ፡፡ | 8 | 3 |
| 543/1 | 5 | ድርጊቱ የተፈጸመው በአደገኛ መሳሪያ እና ባልታወቀ ቸልተኝነት ከሆነ፡፡ | 9 | 4 |
| 543/1 | 6 | ድርጊቱ የተፈጸመው በአደገኛ መሳሪያ እና በታወቀ ቸልተኝነት ከሆነ፡፡ | 10 | 4 |

51. በቸልተኝነት ሰው መግደል (የወንጀል ህግ አንቀጽ 543/2)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 543/2 | 1 | አጥፊው የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለው ሆኖ ድርጊቱም የሟች አስተዋጽኦ ካለው እና ባልታወቀ ቸልተኝነት የተፈጸመ ከሆነ፡፡ | 7 | 3 |
| 543/2 | 2 | አጥፊው የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለው ሆኖ ድርጊቱም የሟች አስተዋጽኦ ከሌለበት እና ባልታወቀ ቸልተኝነት ድርጊቱ የተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 8 | 4 |
| 543/2 | 3 | አጥፊው የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለው ሆኖ ድርጊቱም የሟች አስተዋጽኦ ካለበት እና በታወቀ ቸልተኝነት ድርጊቱ የተፈጸመ ከሆነ፡፡ | 14 | 4 |
| 543/2 | 4 | የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት ሆኖ ድርጊቱም የሟች አስተዋጽኦ ከሌለበት እና ድርጊቱ በታወቀ ቸልተኝነት የተፈጸመ ከሆነ፡፡ | 16 | 4 |

52. በቸልተኝነት ሰው መግደል (የወንጀል ህግ አንቀጽ 543/3)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 543/3 | 1 | በድንጋጌው ከተመለከቱት ውስጥ አንዱ ፍሬነገር (ማቋቋሚያ) የተሟላ ሆኖ፣ ባልታወቀ ቸልተኝነት፣ የሟች አስተዋጽኦ ባለበት የተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 23 | 3 |
| | 2 | በድንጋጌው ከተመለከቱት ውስጥ አንዱ ፍሬነገር (ማቋቋሚያ) የተሟላ ሆኖ፣ ባልታወቀ ቸልተኝነት፣ የሟች አስተዋጽኦ በሌለበት የተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 24 | 3 |
| | 3 | በድንጋጌው ከተመለከቱት ውስጥ ሁለት ፍሬ ነገሮች (ማቋቋሚያዎች) ተሟልተው፣ ባልታወቀ ቸልተኝነት፣ የሟች አስተዋጽኦ ባለበት የተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 25 | 3 |
| | 4 | በድንጋጌው ከተመለከቱት ውስጥ ሁለት ፍሬ ነገሮች (ማቋቋሚያዎች) ተሟልተው፣ ባልታወቀ ቸልተኝነት የሟች አስተዋጽኦ በሌለበት የተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 26 | 3 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 5 | በድንጋጌው ከተመለከቱት ፍሬ ነገሮች (ማቋቋሚያዎች) ውስጥ ሶስት ወይም ከዚያ በላይ ተሟልተው፣ ባልታወቀ ቸልተኝነት የሚች አስተዋጽኦ ባለበት የተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 27 | 3 |
| | 6 | በድንጋጌው ከተመለከቱት ፍሬ ነገሮች (ማቋቋሚያዎች) ውስጥ ሶስት ወይም ከዚያ በላይ ተሟልተው፣ ባልታወቀ ቸልተኝነት የሚች አስተዋጽኦ በሌለበት የፈፀመ ከሆነ፡፡ | 28 | 3 |
| | 7 | ድርጊቱ በድንጋጌዉ ላይ ከተመለከቱት ፍሬ ነገሮች (ማቋቋሚያዎች) ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ፣ በታወቀ ቸልተኝነት የሚች አስተዋጽኦ ባለበት የተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 29 | 3 |
| | 8 | ድርጊቱ በድንጋጌዉ ላይ ከተመለከቱት ፍሬ ነገሮች (ማቋቋሚያዎች) ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ፣ በታወቀ ቸልተኝነት የሚች አስተዋጽኦ በሌለበት የተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 30 | 4 |
| | 9 | በድንጋጌዉ ላይ ከተመለከቱት ፍሬ ነገሮች (ማቋቋሚያዎች) ዉስጥ ሁለቱን የሚያሟላ ሆኖ፣ ድርጊቱም የተፈጸመዉ በታወቀ ቸልተኝነት የሚች አስተዋጽኦ ባለበት ከሆነ፡፡ | 32 | 4 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 10 | በድንጋጌዉ ላይ ከተመለከቱት ፍሬ ነገሮች (ማቋቋሚያዎች) ዉስጥ ሁለቱን የሚያሟላ ሆኖ ድርጊቱ የተፈጸመዉ በታወቀ ችልተኝነት የሚች አስተዋጽኦ በሌለበት የተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 33 | 4 |
| | 11 | በድንጋጌዉ ላይ ከተመለከቱት ፍሬ ነገሮች (ማቋቋሚያዎች) ዉስጥ ሁለቱን የሚያሟላ ሆኖ ድርጊቱ የተፈጸመዉ በታወቀ ችልተኝነት የሚች አስተዋጽኦ ባለበት ከሆነ፡፡ | 34 | 4 |
| | 12 | በድንጋጌው ከተመለከቱት ፍሬ ነገሮች (ማቋቋሚያዎች) ውስጥ ሶስት ወይም ከዚያ በላይ ተሟልተው በታወቀ ቸልተኝነት የሚች አስተዋጽኦ ባለበት የተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 35 | 4 |
| | 13 | በድንጋጌው ከተመለከቱት ፍሬ ነገሮች (ማቋቋሚያዎች) ውስጥ ሶስት ወይም ከዚያ በላይ ተሟልተው በታወቀ ቸልተኝነት የሚች አስተዋጽኦ በሌለበት የተፈፀመ ከሆነ፡፡ | 36 | 4 |

## ምዕራፍ ሁለት

## በሰው አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

53. በሰው አካልና ጤንነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (555-560)

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ህግ አንቀጽ 555 — 560 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋጋጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

2. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 ደረጃ የወጣው የፅኑ እስራት አማራጩን በመያዝ ነው፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ በቀላል እስራትን ተመራጭ የሚደረግ ከሆነ ፣ወንጀሉን ደረጃ እንዳልወጣለት በመቁጠር አግባብነት ባላቸው የመመሪያው ድንጋጌዎች መሰረት ቅጣት ይወሰናል፡፡

3. በወንጀል ህግ አንቀጽ 555 ‹ታሳቦ የሚፈጸም ከባድ የአካል ጉዳት› 558 ‹ከጥፋተኛው ሀሳብ በላይ የደረሰ ጉዳት› እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 559 ንዑስ አንቀጽ 2 ‹በቸልተኝነት የሚፈጸሙ የአካል ጉዳዮች› በወንጀሉ ምክንያት የሚደርሰው የጉዳት ዓይነት እና መጠን ተመሳሳይ በመሆኑ እነዚህን እንደ መስፈርትነት በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ፣ ለወንጀል ህግ አንቀጽ 555 ስድስት ፣ለወንጀል ህግ አንቀጽ 558 ስድስት፣ እና ለወንጀል ህግ አንቀጽ 559/2 ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

4. በወንጀል ህግ አንቀጽ 556/2 ቀላል የአካል ጉዳት ወንጀልን በተመለከተ በድንጋጌው የተመለከቱትን ማክበጃዎች ማለትም ‹ወንጀሉን ለመፈጸም የተጠቀመበት መሳሪያ መኖር› ፣ ‹የሙያ ግዴታን በመተላለፍ የተጣሰ መሆኑ›፣ ‹ጉዳት ከደረሰበት ሰው ተጋላጭነት› እንደ ደረጃ ማውጫ መስፈርት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነኝህ መስፈርቶች ለዚህ መመሪያ ሲባል የቅጣት ማክበጃ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከቱት የቅጣት ማክበጃዎች ዓይነት ላይ በመመስረት እና ከአንድ በላይ ተደራርበው በሚገኙበት ጊዜ የወንጀል ደረጃውን ከፍ እንዲል በማድረግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ፣ ለወንጀል ህግ አንቀጽ 556/2 ሶስት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

6. የወንጀል ህግ አንቀጽ 557 ተፈጻሚ የሚሆነው አስቦ ከባድ የአካል ጉዳት (የወንጀል ህግ አንቀጽ 555) ወይም ቀላል የአካል ጉዳት (የወንጀል ህግ አንቀጽ 556) የማድረስ ወንጀል ሲፈጸም የቅጣት ማቅለያ  ምክንያቶች ተሟልተው ሲገኙ ብቻ በመሆኑ እና የወንጀል ህግ አንቀጽ 556/1 ከወንጀል ህግ አንቀጽ 557 ያነሰ ቅጣትን ስለሚደነግግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ፣ ለወንጀል ህግ አንቀጽ 555 እና  557 ሰባት እና ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/2 እና 557 አራት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል ፡፡

7. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/1፣ 559/1 እና አንቀጽ 560 የያዙት ፍቅድ ሥልጣን ጠባብ በመሆኑ ለእያንዳንዳቸው አንድ የወንጀል ደረጃ ተዘጋጅቶዋል፡

## 54. ታስቦ የሚፈጸም ከባድ የአካል ጉዳት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ  መግለጫ | የጽኑ እስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 555 | 1 | በሰዉ አካል ላይ   ከባድ ጉዳት ያደረሰ ሆኖ፣ ጉዳቱ የዳነ ወይም ሊድን የሚችል ከሆነ፡፡ | 10 |
| | 2 | በሰዉ አካል ላይ  የማይድን ከባድ ጉዳት ያደረሰ ሆኖ፣ የጉዳቱ መጠን  ከዚህ በታች ባሉ የወንጀል ደረጃዎች የተገለፁትን ያህል ከባድ ካልሆነ፡፡ | 16 |
| | 3 | ከሰዉ አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑት ብልቶች ፣ ህዋሳት ውስጥ በአንዱ ላይ  ከፊል  ጉዳት ያደረሰ  እንደሆነ፡፡ | 25 |
| | 4 | በሰዉ አካል ፣ አስፈላጊ ብልቶች ወይም  ህዋሳት ውስጥ በሁለቱ ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ከፊል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፡፡ | 28 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 5 | ከሁለት በላይ በሆኑ የሰዉ አካል፣ አስፈላጊ ብልቶች ወይም ህዋሳት ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ከፊል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፡፡ | 31 |
| | 6 | በሰውነት ወይም በአእምሮ ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ሙሉ ጉዳት ከሆነ ወይም የደረሰው ጉዳት የሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጂውን መልክ ያበላሸ ከሆነ፡፡ | 34 |
| | 7 | የደረሰው ጉዳት ተጎጂው በህይወት ለመኖር የሚያሰጋዉ ከሆነ ወይም ሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ የአካል ክፍሎች ፣ አስፈላጊ ብልቶች ወይም ህዋሳት ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ሙሉ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፡፡ | 35 |

55. ታስቦ የሚፈጸም ከባድ የአካል ጉዳት የቅጣት ማቅለያ ሁኔታዎች (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 555 እና 557)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የቀላል እስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 555 እና 557(1) | 1 | በሰዉ አካል ላይ ከባድ ጉዳት ያደረሰ ሆኖ፣ ጉዳቱ የዳነ ወይም ሊድን የሚችል ከሆነ፡፡ | 2 | 1 |
| | 2 | በሰዉ አካል ላይ የማይድን ከባድ ጉዳት ያደረሰ ሆኖ፣ የጉዳቱ መጠን ከዚህ በታች ባሉ | 2 | 1 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የወንጀል ደረጃዎች የተገለፁትን ያህል ከባድ ካልሆነ፡፡ | | |
| | 3 | ከሰዉ አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑት ብልቶች ፣ ህዋሳት ውስጥ በአንዱ ላይ ከፊል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፡፡ | 4 | 1 |
| | 4 | በሰዉ አካል ፣ አስፈላጊ ብልቶች ወይም ህዋሳት ውስጥ በሁለቱ ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ከፊል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፡፡ | 6 | 2 |
| | 5 | ከሁለት በላይ በሆኑ የሰዉ አካል፣ አስፈላጊ ብልቶች ወይም ህዋሳት ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ከፊል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፡፡ | 8 | 2 |
| | 6 | በሰውነት ወይም በአእምሮ ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ሙሉ ጉዳት ከሆነ ወይም የደረሰው ጉዳት የሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጂውን መልክ ያበላሸ ከሆነ፡፡ | 10 | 3 |
| | 7 | የደረሰው ጉዳት ተጎጂው በህይወት ለመኖር የሚያሰጋዉ ከሆነ፣ ወይም ሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ የአካል ክፍሎች ፣ አስፈላጊ ብልቶች ወይም ህዋሳት ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ሙሉ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ፡፡ | 11 | 3 |
| | 8 | የወንጀል ሕግ አንቀጽ 557(1)(ሐ)ስር የተመለከተው ተጎጅ በእድሜው ፣ በአእምሮው | 16 | 3 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወይም በሌላ ምክንያት ጉዳት እንዲደርስበት ያቀረበው ጥያቄ ወይም በሽታው የሚያስከትለውን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ለመረዳት የማይችል ከሆነ፡፡ | | |

## 56. ታስቦ የሚፈጸም ቀላል የአካል ጉዳት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 556/1)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 556/1 | 1 | በሰው አካል ወይም ጤና ላይ አስቦ ቀላል ጉዳት ያደረሰ ከሆነ፡፡ | 2 | 6 |

## 57. ታስቦ የሚፈጸም ቀላል የአካል ጉዳት (የወንጀል ህግ አንቀጥ 556/2)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 556/2 | 1 | በድንጋጌው ከተዘረዘሩት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱን ያሟላ ከሆነ፡፡ | 5 |
| 556/2 | 2 | በድንጋጌው ከተዘረዘሩት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱን የሚያሟላ ከሆነ፡፡ | 8 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 556/2 | 3 | በድንጋጌው ከተዘረዘሩት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሶስቱን የሚያሟላ ከሆነ፡፡ | 13 |

## 58. ታስቦ የሚፈጸም ቀላል የአካል ጉዳት የቅጣት ማቅለያ ሁኔታዎች (የወንጀል ህግ አንቀጽ 556/2 እና 557)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 556(2) እና 557/1 | 1 | በ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2) ከተዘረዘሩት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱን ያሟላ ከሆነ፡፡ | 2 | 1 |
| 556(2)እና 557/1 | 2 | በ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2) ከተዘረዘሩት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱን የሚያሟላ ከሆነ፡፡ | 4 | 2 |
| 556(2)እና 557/1 | 3 | ከሆነ በድንጋጌው በ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 556(2) ከተዘረዘሩት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሶስቱን የሚያሟላ ከሆነ፡፡ | 6 | 2 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 556(2)እና 557/2 | 4 | በወንጀል ህግ አንቀጽ 557/1/ሐ የተመለከተው ተጎጂ በእድሜው ወይም በአእምሮው ወይም በሌላ ማናቸውም ሁኔታ ጉዳት እንዲደርስበት ያቀረበውን ጥያቄ ወይም እሽታውን የሚያስከትለውን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ለመረዳት የማይችል ከሆነ፡፡ | 10 | 2 |

## 59. ከጥፋተኛው ሀሳብ በላይ የደረሰ ጉዳት (የወንጀል ህግ አንቀጽ 558)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 558 | 1 | የሰውን አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች ወይም ህዋሳቶች አንዱን ያጎደለ ወይም እንዳያገለገሉ ያደረገ ወይም ማናቸውንም ሌላ ከባድ የሆነ ጉዳትን በሌላ ሰው ላይ ያደረሰ ከሆነ፡፡ | 5 |
| 558 | 2 | በሰው አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች ወይም ህዋሳቶች ከአንድ በላይ ያጎደለ ወይም እንዳያገለግሉ ያደረገ፡፡ | 6 |
| 558 | 3 | በሰውነት ወይም በአእምሮ ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያተርፍ ወይም ከባድ ጉዳት የሚያደርስ በሽታን የሚያስከትል ጉዳት ከሆነ፡፡ | 7 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 558 | 4 | የደረሰው ጉዳት በሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሁኔታ የተጎጂው መልክ ያበላሸ ከሆነ፡፡ | 8 |
| 558 | 5 | የደረሰው ጉዳት ለተጎጂው ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ፡፡ | 9 |
| 558 | 6 | ከላይ ደረጃ 1-5 ከተጠቀሱት መስፈርቶች ከአንድ በላይ ተደራርበው የተገኙ ከሆነ፡፡ | 11 |

60. በቸልተኝነት የሚፈጸሙ የአካል ጉዳቶች (የወንጀል ህግ አንቀጽ 559/1)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 559/1 | 1 | በቸልተኝነት በሌላ ሰው አካል ወይም ጤና ላይ ቀላል ጉዳት ያደረሰ ከሆነ | 4 | 4 |

61. በቸልተኝነት የሚፈጸሙ የአካል ጉዳቶች (የወንጀል ህግ አንቀጽ 559/2)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 559/2 | 1 | ቀላል የአካል ወይም የጤና ጉዳት አድራሹ የሌላ ሰውን አካል ወይም ጤንነት የመጠበቅ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት እንደ ህክምና ባለሙያ ወይም አሽከርካሪ ያለ ሰው ከሆነ፡፡ | 7 | 1 |
| 559/2 | 2 | በሰው አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች ወይም ህዋሳቶች አንዱን ያጎደለ ወይም እንዳያገለግሉ ያደረገ ከሆነ፡፡ | 8 | 2 |
| 559/2 | 3 | በሰው አካል ወይም አስፈላጊ ከሆኑ ብልቶች ወይም ህዋሳቶች ከአንድ በላይ ያጎደለ ወይም እንዳያገለግሉ ያደረገ ከሆነ፡፡ | 9 | 3 |
| 559/2 | 4 | በሰውነት ወይም በአእምሮ ላይ ለዘወትር ጠንቅ የሚያደርስ ወይም ከባድ ጉዳት የሚያደርስ በሽታን የሚያስከትል ከሆነ፡፡ | 10 | 4 |
| 559/2 | 5 | የደረሰው ጉዳት የሚያሰቅቅና ጉልህ ሆኖ በሚታይ ሆኔታ የተጎጂውን መልክ ያበላሸ ከሆነ፡፡ | 11 | 5 |
| 559/2 | 6 | የደረሰው ጉዳት ለተጎጂው ህይወት የሚያሰጋ ከሆነ፡፡ | 12 | 6 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 559/2 | 7 | ከላይ ከደረጃ 1-5 የተጠቀሱት መስፈርቶች ከአንድ በላይ ተደራርበው የተገኙ ከሆነ፡፡ | 13 | 7 |

## 62. የእጅ እልፊት (የወንጀል ህግ አንቀጽ 560/1)

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 560/1 | 1 | የአካል ጉዳትን ወይም የጤና ጉድለትን ሳያደርስ በሌላ ሰው ላይ የእጅ እልፊት ወይም የመጋፋት ድርጊት የፈጸመ ከሆነ፡፡ | 2 | 1 |

## ርዕስ ስድስት

## በመልካም ፀባይ እና በቤተዘመድ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

## በግብረ ሥጋ ነፃነትና ንፅህና ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620-628)

**63. ጠቅላላ**

1. በወንጀል ሕግ አንቀፅ 620-628 ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በግብረ ሥጋ ነጻነትና ንፅህና ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ክስ ቀርቦባቸው ጥፋተኛነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ተከሳሾች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡

2. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/1 ስር ለተመለከተው የአስገድዶ መድፈር ወንጀል፣ የወንጀሉ የአፈፃፀም ዘዴ እና ሁኔታ፣የወንጀል ፈፃሚው ከተበዳይ ጋር ባለው ቅርበት ፣በወንጀሉ ምክንያት የደረሰ ጉዳት እና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 628 ስር የተመለከቱትን የማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስራ ሁለት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. የወንጀል ሕግ አንቀፅ 620/2 ለወንጀል ሕግ አንቀፅ 620/1 ማክበጃ ምክንያቶችን በድንጋጌ ከፊደል ሀ-መ ዘርዝሮ ብቻ የያዘ በመሆኑ ፣ በአንቀፅ 620/2 እና በወንጀል ህግ አንቀፅ 628 ስር ከተመለከቱት ተጨማሪ የማከበጃ ምክንያቶች ጋር በማጣመር ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

4. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/3 ማከበጃ ምክንያቶች ተሟልተው ከተገኙ የሚጣለውን የቅጣት ዓይነት ሕጉ እራሱ ወስኖ ስላስቀመጠው አንድ የወንጀል ደረጃ ብቻ ተዘጋጅቷል፡፡

5. በወንጀል ሕግ አንቀፅ 621 ስር ለተደነገገው ሴቶች በወንዶች ላይ ለሚፈፀሙት አስገድዶ መድፈር የወንጀሉን አፈፃፀም ሁኔታ፣ በተበዳይ ላይ የደረሰው ጉዳት በወንጀል ህግ አንቀጽ 628 ስር የተመለከቱትን የማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ስምንት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅቷል፡፡

6. በወንጀል ሕግ አንቀፅ 622 ስር ለተመለከተው በንጽህና ክብር ላይ የሚፈጽሙ የሀይል ድርጊት የወንጀሉን አፈፃፀም እና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ ከፍተኛ አስራ ሁለት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ ወንጀሉ በቀላል እስራት ወይም በፅኑ እስራት በአማራጭ የሚያስቀጣ በመሆኑ፣ እስከ ደረጃ-3 ድረስ በሁለቱም የእስራት አማራጮች የቅጣት እርከኖች ተለይተዋል፡፡

7. በወንጀል ሕግ አንቀፅ 623 ስር ለተመለከተው አእምሯቸውን በሳቱ ወይም የአእምሮ ደካማ በሆኑ ወይም ለመቃወም በማይችሉ ሰዎች ላይ የሚፈጸም የክብረ ንፅህና ድፍረት በደል የወንጀሉን ዓይነት እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስራ አንድ የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ ወንጀሉ በቀላል እስራት ወይም በፅኑ እስራት በአማራጭ የሚያስቀጣ በመሆኑ፣ እስከ ደረጃ-3 ድረስ በሁለቱም የእስራት አማራጮች የቅጣት እርከኖች ተለይተዋል፡፡

8. በወንጀል ሕግ አንቀፅ 624 ስር ለተመለከተው ሆስፒታል ውስጥ በተኙ በተጋዙ ወይም በታሰሩ ሰዎች ላይ የሚፈፀም የክብረ ንፅህና ድፍረት በደል የወንጀሉን ዓይነት እና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ወንጀሉ በቀላል እስራት ወይም በፅኑ እስራት በአማራጭ የሚያስቀጣ በመሆኑ፣ በሁለቱም የእስራት አማራጮች ባገናዘበ መልኩ የቅጣት እርከኖች ተለይተዋል፡፡

9. በወንጀል ሕግ አንቀፅ 625 ስር ለተመለከተው አንድ ሴት ያለባትን ከፍ ያለ ችግር ወይም ጥገኝነትዋን ምክንያት በማድረግ የሚፈፀም ድርጊት የወንጀሉን ዓይነት እና በወንጀል ህግ አንቀፅ 628 ሥር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

10. በወንጀል ሕግ አንቀፅ 626/1 ሥር ለተመለከተው ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል የተበዳይን የዕድሜ ሁኔታ፣ የተከሳሽን ከተበዳይ ወይም ከተበዳይ ቤተሰብ ጋር የነበረውን ቅርርብ፣ በተበዳይ ላይ የደረሰውን የስነ-ልቦና ጉዳት እንዲሁም ፣ በወንጀል ህግ አንቀፅ

626/4/ሀ እና 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ  አስራ አራት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

11. በወንጀል ህግ አንቀፅ 626/2 ስር ለተመለከተው ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል የተበዳይን የዕድሜ  ሁኔታ፣ የተከሳሽን ከተበዳይ ወይም ከተበዳይ ቤተሰብ ጋር የነበረውን ቅርርብ፣ በተበዳይ ላይ የደረሰውን የስነ-ልቦና ጉዳት እና በወንጀል ህግ አንቀጽ 626/4/ለ እና 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስራ አንድ የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

12. በወንጀል ሕግ አንቀፅ 626/3 ስር ለተመለከተው ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል የተበዳይን የእድሜ ሁኔታ እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 626/4/ሐ እና 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

13. በወንጀል ሕግ አንቀፅ 627/1 ስር ለተመለከተው በሕፃናት ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል የተበዳይን የእድሜ ሁኔታ እና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 627/4/ሀ ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ስድስት ደረጃዎች  ተዘጋጅተዋል፡፡

14. በወንጀል ሕግ አንቀፅ 627/2 ስር ለተመከተው በህፃናት ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል የተበዳይን የዕድሜ ሁኔታ እና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 627/4/ለ እና 628 ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስራ አንድ  የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

15. በወንጀል ሕግ አንቀፅ 627/3 ስር ለተመለከተው በህፃናት ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል የተበዳይን የእድሜ ሁኔታ እና በወንጀል ሕግ አንቀፅ 627/4/ሐ እና 628 ስር  የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች በመጠቀም ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

16.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 627/5 ማክበጃ ምክንያቶች ተሟልተው ከተገኙ የሚጣለውን የቅጣት ዓይነት ሕጉ እራሱ ወስኖ ስላስቀመጠው አንድ የወንጀል ደረጃ ብቻ ተዘጋጅቷል፡፡

17.አግባብነት ላለው ድንጋጌ የወንጀል ደረጃ ለመለየት የመሳሪያው አደገኛ መሆን ያለ መሆን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ በቅድሚያ ምክንያቱን በማስቀመጥ መወሰን አለበት፡፡

**64. መደፈር (የወንጀል ሕግ አንቀፅ 620/1 እና 628)**

| የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 620(1) | 1 | አስገድዶ መድፈሩ የተፈፀመው በብርቱ ዛቻ ከሆነ፡፡ | 27 |
| 620(1) | 2 | አስገድዶ መድፈሩ የተፈፀመው፣ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎች ሳይያዙ የሃይል ድርጊት በመጠቀም ከሆነ፡፡ | 29 |
| 620(1) | 3 | አስገድዶ መድፈሩ የተፈፀመው ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን፣ አስካሪ መጠጥ ወይም ሌሎች ሕሊናን የሚያስቱ ንጥረነገሮችን ወይም ዘዴዎችን በመጠቀም ከሆነ፡፡ | 31 |
| 620(1) | 4 | ጥፋተኛው ወንጀሉን ለመፈፀም የተጠቀመበት ዘዴ ከ ደረጃ 1 እስከ ደረጃ 3 ከተገለፀው ውስጥ ባንዱ ሆኖ ፤ | 34 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | 1. የወንጀል ድርጊት አፈፃፀሙ ፀያፍ ወይም አዋራጅ በሆነ መንገድ ከሆነ<br>ወይም<br>2. የወንጀሉ ፈፃሚው ከተበዳይ ጋር ባለው ቅርበት ምክንያት እምነት የተጣለበት ሰው ከሆነ ፡፡ | |
| 620(1) | 5 | ከላይ በደረጃ 4 የተዘረዘሩትን ሁለቱንም መመዘኛዎችን የሚያሟላ ከሆነ ፡፡ | 35 |
| 620(1) | 6 | ተበዳይ በወንጀሉ ምክንያት ከፍ ያለ የስነ-ልቦና ጉዳት የደረሰባት ከሆነ ፡፡ | 36 |
| 620(1)<br>እና<br>628 (ለ) | 7 | ሞትን የማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ተበዳይን አስገድዶ በመድፈር በሽታውን ያስያዘ ከሆነ፡፡ | 38 |
| 620(1)<br>እና<br>628 (ሀ) | 8 | በአስገድዶ መድፈሩ ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች ከሆነ፡፡ | 39 |
| 620(1)<br>እና | 9 | በደረጃ 7 እና 8 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች በአንድ ላይ ተሟልተው የተገኙ ከሆነ፡፡ | 40 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 628(ሀ) እና (ለ) | | | |
| 620(1)<br><br>እና<br><br>628 (ለ) | 10 | ሞትን የሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ተበዳይን አስገድዶ በመድፈር በሽታውን ያስያዘ ከሆነ፡፡ | 41 |
| 620(1)<br><br>እና<br><br>628 (ሀ)<br>እና (ለ) | 11 | ሞትን የሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ተበዳይን አስገድዶ በመድፈር በሽታውን ያስያዘ እና ተበዳይ ያረገዘች ከሆነ፡፡ | 42 |
| 620 (1)<br><br>እና<br><br>628 (ሐ) | 12 | ተበዳይ በአስገድዶ መድፈር ወንጀሉ ምክንያት በደረሰባት ከባድ ሃዘን ፣ጭንቀት፣ ሃፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሷን የገደለች ከሆነ፡፡ | 43 |

65. አስገድዶ መደፈር (የወንጀል ሕግ አንቀፅ 620/2/ ሀ-መ እና 628)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 620/2 | 1 | በወንጀል ሕግ አንቀፅ 620/2 ስር ከፊደል ሀ-መ ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ብቻ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | 37 |
| 620/2 እና 628/ለ | 2 | በወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2 ስር ከፊደል ሀ-መ ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተው ሲገኙ፡፡<br>ወይም<br>በወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2 ከማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ፣ ተከሳሽ ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ በግብረ ሥጋ ግንኙነቱ ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ ከሆነ ፡፡ | 38 |
| 620/2 | 3 | በወንጀል ሕግ አንቀፅ 620/2 ስር ከፊደል ሀ-መ ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሶስቱ ተሟልተው ሲገኙ፡፡ | 39 |
| 620/2 እና 628/ሀ | 4 | በወንጀል ሕግ አንቀፅ 620/2 ስር ከፊደል ሀ-መ ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ፣ በአስገድዶ መድፈሩ ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች ከሆነ፡፡ | 40 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ወይም<br><br>በወንጀል ሕግ አንቀጽ 620/2 ከማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልቶ ፣ ተከሳሽ ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ በግብረ ሥጋ ግንኙነቱ ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ ከሆነ፡፡ | |
| 620/2 | 5 | በወንጀል ሕግ አንቀፅ 620/2 ስር ከፊደል ሀ-መ ስር ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አራቱም ተሟልተው የተገኙ ከሆነ፡፡ | 41 |
| 620/2<br>እና<br>628/ለ | 6 | በወንጀል ሕግ አንቀፅ 620/2 ስር ከፊደል ሀ-መ ስር ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ቢያንስ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ እና ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር መያዙን እያወቀ ተበዳይን አስገድዶ በመድፈር በሽታው ያስያዘ ከሆነ፡፡ | 42 |
| 620/2<br>እና<br>628/ሐ | 7 | በወንጀል ሕግ አንቀፅ 620/2 ስር ከፊደል ሀ-መ ከተመለከቱት የማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ቢያንስ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ እና ተበዳይ በአስገድዶ መድፈሩ ምክንያት በደረሰባት ከባድ ሃዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሣ ራሷን የገደለች ከሆነ፡፡ | 43 |

66. አስገድዶ መደፈር (የወንጀል ሕግ አንቀፅ 620/3)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 620/3 | 1 | አስገድዶ መደፈሩ ከባድ የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ ከሆነ፡፡ | 44 |

67. አስገድዶ መደፈር (የወንጀል ሕግ አንቀፅ 621 እና 628 )

| የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 621 | 1 | አስገድዶ መድፈሩ የተፈፀመው በብርቱ ዛቻ ከሆነ፡፡ | 11 |
| 621 | 2 | አስገድዶ መድፈሩ የተፈፀመው፣ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎች ሳይያዙ የሃይል ድርጊት በመጠቀም ከሆነ፡፡ | 13 |
| 621 | 3 | አስገድዶ መድፈሩ የተፈፀመው ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን፣ አስካሪ መጠጥ | 15 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ወይም ሌሎች ሕሊናን የሚያስቱ ንጥረነገሮችን ወይም ዘዴዎችን በመጠቀም ከሆነ፡፡ | |
| 621 | 4 | ጥፋተኛዋ ወንጀሉን ለመፈፀም የተጠቀመችበት ዘዴ ከ ደረጃ 1 እስከ ደረጃ 3 ከተገለፀው ውስጥ ባንዱ ሆኖ ፤ አፈፃፀሙ ፀያፍ ወይም አዋራጅ ከሆነ፡ | 17 |
| 621 | 5 | ተበዳይ በወንጀሉ ምክንያት ከፍ ያለ የስነ-ልቦና ጉዳት የደረሰበት ከሆነ፡፡ | 20 |
| 621 እና 628 (ለ) | 6 | ጥፋተኛዋ ሞትን የማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዟን እያወቀች ተበዳይን አስገድዳ በመድፈር በሽታውን ያስያዘች ከሆነ፡፡ | 38 |
| 621 እና 628 (ለ) | 7 | ሞትን የሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዟን እያወቀች ተበዳይን አስገድዳ በመድፈር በሽታውን ያስያዘች ከሆነ፡፡ | 42 |
| 621 እና 628 (ሐ) | 8 | ተበዳይ በአስገድዶ መድፈር ወንጀሉ ምክንያት በደረሰበት ከባድ ሃዘን ፣ጭንቀት፣ ሃፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሱን የገደለ ከሆነ፡፡ | 43 |

68. በንፅህና ክብር ላይ የሚፈፀም የሃይል ድርጊት (የወንጀል ሕግ አንቀፅ 622 እና 628)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ለቀላል እስራት | ለፅኑ እስራት |
| 622 | 1 | የግብረ ሥጋ መሰል ተግባሩ ወይም ማናቸውም ሌላ ዓይነት ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆነው ድርጊት የተፈፀመው በብርቱ ዛቻ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ከሆነ፡፡ | 7 | 10 |
| 622 | 2 | ድርጊቱ የተፈፀመው፣ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎች ሳይያዙ የሃይል ድርጊት በመጠቀም ከሆነ፡፡ | 10 | 14 |
| 622 | 3 | ድርጊቱ የተፈፀመው ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን፣ አስካሪ መጠጥ ወይም ሌሎች ሕሊናን የሚያስቱ ንጥረነገሮችን ወይም ዘዴዎችን በመጠቀም ከሆነ፡፡ | 13 | 20 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 4 | ጥፋተኛው ወንጀሉን ለመፈፀም የተጠቀመበት ዘዴ ከ ደረጃ 1 እስከ ደረጃ 3 ከተገለፀው ውስጥ ባንዱ ሆኖ ፤<br><br>1. የወንጀል ድርጊት አፈፃፀሙ ፀያፍ ወይም አዋራጅ በሆነ መንገድ ከሆነ<br><br>ወይም<br><br>2. የወንጀሉ ፈፃሚው ከተበዳይ ጋር ባለው ቅርበት ምክንያት እምነት የተጣለበት ሰው ከሆነ ፡፡ | --- | 24 |
| 622 | 5 | ከላይ በደረጃ 4 የተዘረዘሩትን ሁለቱንም መመዘኛዎችን የሚያሟላ ከሆነ ፡፡ | --- | 28 |
| 622 | 6 | ድርጊቱ በተበዳይ ላይ ከባድ የስነ-ልቦና ጉዳት አስከትሎ እንደሆነ | ----- | 35 |
| 622 እና 628/ለ | 7 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ የግብረ ስጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊት ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ ከሆነ፡፡ | ----- | 37 |
| 622 እና 628/ሀ | 8 | የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ በሆነ | ----- | 38 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች ከሆነ፡፡ | | |
| 622 እና 628/ለ | 9 | በደረጃ 7 እና 8 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ ከሆነ፡፡ | ---- | 40 |
| 622 እና 628/ሐ | 10 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ከተበዳይ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆነ ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ድርጊት በመፈፀም በበሽታው ያስያዘ ከሆነ፡፡ | ---- | 41 |
| 622 እና 628/ለ | 11 | በደረጃ 8 እና 10 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ ከሆነ፡፡ | ---- | 42 |
| 622 እና 628/ሐ | 12 | ተበዳይ የግብረ ስጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊት ምክንያት በደረሰበት ከባድ ኃዘን ወይም ጭንቀት ፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሣ ራሱን የገደለ ከሆነ፡፡ | ----- | 43 |

69. **አእምሯቸውን በሳቱ ወይም በአእምሮ ደካማ በሆኑ ወይም ለመወቃወም በማይችሉ ሰዎች ላይ የሚፈፀም የክብረ ንፅኅና ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀፅ 623 እና 628)**

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ለቀላል እስራት | ለፅኑ እስራት |
| 623 | 1 | ድንጋጌውን በመተላለፍ የተፈፀመውን የወንጀል ድርጊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መሠል ወይም ሌላ ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ የሆነ ተግባር ከሆነ፡፡ | 10 | 15 |
| 623 | 2 | ድንጋጌውን በመተላለፍ የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከሆነ፡፡ | 14 | 28 |
| 623 | 3 | የወንጀሉ አፈፃፀም በደረጃ-1 እንደተመለከተው ሆኖ ፤<br><br>1. የወንጀል ድርጊት አፈፃፀሙ ፀያፍ ወይም አዋራጅ በሆነ መንገድ ከሆነ<br><br>ወይም<br><br>2. የወንጀሉ ፈፃሚው ከተበዳይ ጋር ባለው ቅርበት ምክንያት እምነት የተጣለበት ሰው ከሆነ ፡፡ | --- | 33 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 623 | | የወንጀሉ አፈፃፀም በደረጃ-1 እንደተመለከተው ሆኖ ፤<br><br>1. የወንጀል ድርጊት አፈፃፀሙ ፀያፍ ወይም አዋራጅ በሆነ መንገድ ከሆነ<br><br>ወይም<br><br>2. የወንጀሉ ፈፃሚው ከተበዳይ ጋር ባለው ቅርበት ምክንያት እምነት የተጣለበት ሰው ከሆነ ፡፡ | ---- | 34 |
| 623 | 4 | ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል፣ የአዕምሮ ወይም የስነ-ልቦና ጉዳትን አስከትሎ ከሆነ፡፡ | ….. | 35 |
| 623 | 5 | ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል፣ የአዕምሮ ወይም የስነ-ልቦና ጉዳትን አስከትሎ ከሆነ፡፡ | ---- | 36 |
| 623<br><br>እና<br><br>628/ለ | 6 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ በግብረ ስጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊት ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ ከሆነ፡፡ | ----- | 37 |
| 623 | 7 | በግብረ ስጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ስጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅኅና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ | ----- | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| እና<br>628/ሀ | | አይነት ድርጊት ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች ከሆነ፡፡ | | 38 |
| 623<br>እና<br>628/ለ | 8 | በደረጃ 5 እና 6 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ ከሆነ፡፡ | ----- | 40 |
| 623<br>እና<br>628/ሐ | 9 | ሞትን በሚያስከትል አባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ከተበዳይ ጋር በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆነ ማናቸውንም ሌላ አይነት ድርጊት በመፈፀም በበሽታው ያስያዘ ከሆነ፡፡ | ----- | 41 |
| 623<br>እና<br>628/ለ | 10 | በደረጃ 6 እና 8 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ ከሆነ፡፡ | ------ | 42 |
| 623<br>እና<br>628/ሐ | 11 | ተበዳይ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሰለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት በደረሰበት ከባድ ሀዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሱን የገደለ ከሆነ፡፡ | ------ | 43 |

70. ሆስፒታል ውስጥ በተኙ፣ በተጋዙ ወይም በታሰሩ ሰዎች ላይ የሚፈፀም የክብረ ንፅህና ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀፅ 624 እና 628)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | |
|---|---|---|---|---|
| | | | በቀላል እስራት | በፅኑ እስራት |
| 624 | 1 | ድንጋጌውን በመተላለፍ የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት መሠል ወይም ሌላ ለመልካም ጸባይ ተቃራኒ የሆነ ተግባር እንደሆነ፡፡ | 10 | 15 |
| 624 | 2 | ድንጋጌውን በመተላለፍ የተፈጸመው የወንጀል ድርጊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደሆነ፡፡ | 14 | 31 |
| 624 | 3 | ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ፣ የአዕምሮ ወይም የስነ-ልቦና ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ፡፡ | --- | 34 |
| 624 | 4 | ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል፣ የአዕምሮ ወይም ስነ-ልቦና ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ፡፡ | ---- | 36 |
| 624 | 5 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም | ----- | 38 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| እና<br>628/ለ | | ለንጽህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ፡፡ | | |
| 624<br>እና<br>628/ሀ | 6 | በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሠል ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊት ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች እንደሆነ ፡፡ | ----- | 39 |
| 624<br>እና<br>628/ለ | 7 | በደረጃ 5 እና 6 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ፡፡ | ----- | 40 |
| 624<br>እና<br>628/ሐ | 8 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ከተበዳይ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሠል ድርጊት ወይም ለንፅኀና ክብር ተቃራኒ የሆነ ማናቸውንም ሌላ አይነት ድርጊት በመፈፀም በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ ፡፡ | ----- | 41 |
| 624<br>እና<br>628/ለ | 9 | በደረጃ 6 እና 8 ስር የተመለከተቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ፡፡ | ------ | 42 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 624<br>እና<br>628/ሐ | 10 | ተበዳይ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅኀና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊት ምክንያት በደረሰበት ከባድ ሃዘን ወይም ጭንቀት ሀፍረት ፣ ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሣ ራሱን የገደለ እንደሆነ፡፡ | ------ | 43 |

71. **አንድ ሴት ያለባትን ከፍ ያለ ችግር ወይም ጥገኝነትዋን ምክንያት በማድረግ የሚፈጸም ድርጊት (የወንጀል ሕግ አንቀፅ 625 እና 628)**

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ለቀላል እስራት | ለፅኑ እስራት |
| 625 | 1 | ድንጋጌውን በመተላለፍ የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት የግብረ ስጋ ግንኙነት መሰል ወይም ሌላ ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ የሆነ ተግባር እንደሆነ፡፡ | 10 | ----- |
| 625 | 2 | ድንጋጌውን በመተላለፍ የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደሆነ፡፡ | 15 | ---- |
| 625 | 3 | ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል፣ የአዕምሮ ወይም የስነልቦና ጉዳትን አስከትሎ እንደሆነ፡፡ | 17 | ---- |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 625 | 4 | ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአዕምሮ ጉዳት አስከትሎ እንደሆነ፡፡ | 20 | ------- |
| 625 እና 628/ለ | 5 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም በንፅኀና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊት ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ፡፡ | ----- | 37 |
| 625 እና 628/ሀ | 6 | በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም በንፅህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውንም ሌላ አይነት ድርጊት ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች እንደሆነ፡፡ | | 38 |
| 625 እና 628/ለ | 7 | በደረጃ 5 እና 6 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ፡፡ | | 40 |
| 625 እና 628/ሐ | 8 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ከተበዳይ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆነ | | 41 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ማናቸውንም ሌላ አይነት ድርጊት በመፈፀም በበሽታ ያስያዘ እንደሆነ፡፡ | | |
| 625 እና 628/ለ | 9 | በደረጃ 6 እና 8 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ፡፡ | | 42 |
| 625 እና 628/ሐ | 10 | ተበዳይ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት ምክንያት በደረሰባት ከባድ ኃዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሣ ራሷን የገደለች እንደሆነ፡፡ | | 43 |

72. **ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀፅ 626/1 ፣ 626/4/ ሀ እና 628)**

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 626/1 | 1 | የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተፈፀመው ዕድሜዋ 16 ዓመት ከሞላት እና አስራ ስምንት ዓመት ካልሞላ ሴት ህፃን ልጅ ጋር እንደሆነ፡፡ | 25 |
| 626/1 | 2 | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ-1 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ጥፋተኛው ከተበዳይ ወይም ከተበዳይ ቤተሰብ ጋር ቅርበት ያለው ሰው እንደሆነ፡፡ | 26 |
| 626/1 | 3 | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ-1 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ተበዳይ በወንጀሉ ምክንያት ከፍ ያለ ስነ ልቦና ጉዳት የደረሰባት ከሆነ፡፡ | 27 |
| 626/1 | 4 | የግብረ ሥጋ ግንኙነቱ የተፈፀመው ዕድሜዋ 13 ዓመት ከሞላት እና አስራ ስድስት ዓመት ካልሞላት ሴት ህፃን ልጅ ጋር እንደሆነ፡፡ | 30 |
| 626/1 | 5 | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ-4 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ጥፋተኛው ከተበዳይ ወይም ከተበዳይ ቤተሰብ ጋር ቅርበት ያለው ሰው እንደሆነ፡፡ | 33 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 626/1 | 6 | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ-4 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ተበዳይ በወንጀሉ ምክንያት ከፍ ያለ ስነ ልቦና ጉዳት የደረሰባት ከሆነ፡፡ | 35 |
| 626/1<br>እና<br>626/4/ሀ | 7 | በደረጃ 1 የተመለከተችው ተበዳይ የጥፋተኛው ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ፣ተማሪ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው ፣ በሞግዚትነት የሚያሳድጋት ልጅ፣ ወይም እንዲጠብቃት ወይም እንዲንከባከባት በአደራ የተሠጠችው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የምትገኝ ልጅ እንደሆነች፡፡ | 36 |
| 626/1<br>እና<br>626/4/ሀ | 8 | በደረጃ 4 የተመለከተችው ተበዳይ የጥፋተኛው ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድጋት ልጅ ወይም እንዲጠብቃት ወይም እንዲንከባከባት በአደራ የተሰጠችው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚትገኝ ልጅ እንደሆነች፡፡ | 37 |
| 626/1<br>እና<br>628/ለ | 9 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ፡፡ | 38 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 626/1 እና 628/ሀ | 10 | በግብረ ሥጋ ግንኙነቱ ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች እንደሆነ ፡፡ | 39 |
| 626/1 እና 628/ለ | 11 | በደረጃ 9 እና 10 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ፡፡ | 40 |
| 626/1 እና 628/ሐ | 12 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ከተበዳይ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት በመፈፀም በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ፡፡ | 41 |
| 626/1 እና 628/ለ | 13 | በደረጃ 10 እና 12 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ፡፡ | 42 |
| 626/1 እና 628/ሐ | 14 | ተበዳይ በግብረ ስጋ ግንኙነት ምክንያት በደረሰባት ከባድ ኃዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት፣ ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሷን የገደለች እንደሆነ፡፡ | 43 |

73. **ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀፅ 626/2 ፣ 626/4/ለ እና 628)**

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 626/2 | 1 | የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተፈፀመው ዕድሜው 16 ዓመት ከሞላውና እና አስራ ስምንት ዓመት ካልሞላው ወንድ ህፃን ልጅ ጋር እንደሆነ፡፡ | 10 |
| 626/2 | 2 | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ-1 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ጥፋተኛው ከተበዳይ ወይም ከተበዳይ ቤተሰብ ጋር ቅርበት ያላት ሰው እንደሆነች፡፡ | 13 |
| 626/2 | 3 | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ-1 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ተበዳይ በወንጀሉ ምክንያት ከፍ ያለ ስነ ልቦና ጉዳት የደረሰበት ከሆነ፡፡ | 15 |
| 626/2 | 4 | የግብረ ሥጋ ግንኙነቱ የተፈፀመው ዕድሜው 13 ዓመት ከሞላው እና አስራ ስድስት ዓመት ካልሞላው ወንድ ህፃን ልጅ ጋር እንደሆነ፡፡ | 18 |
| 626/2 | 5 | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ-4 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ጥፋተኛው ከተበዳይ ወይም ከተበዳይ ቤተሰብ ጋር ቅርበት ያላት ሰው እንደሆነች፡፡ | 21 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 626/2 | 6 | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ-4 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ተበዳይ በወንጀሉ ምክንያት ከፍ ያለ ስነ ልቦና ጉዳት የደረሰበት ከሆነ፡፡ | 24 |
| 626/2 እና 626/4/ለ | 7 | በደረጃ 1 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛዋ ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ ፣ ወይም ጥፋተኛው ፣ በሞግዚትነት የምታሳድገው ልጅ ፣ ወይም እንድትጠብቀው ወይም እንድትንከባከበው በአደራ የተሠጣት ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሷ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ እንደሆነ፡፡ | 27 |
| 626/2 እና 626/4/ለ | 8 | በደረጃ 4 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛዋ ተማሪ ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛዋ በሞግዚትነት የምታሳድገው ልጅ ፣ ወይም እንዲጠብቀው ወይም እንድትንከባከበው በአደራ የተሰጣት ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሷ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ስር የሚገኝ ልጅ እንደሆነ ፡፡ | 30 |
| 626 /2/ እና 628/ለ | 9 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዟን እያወቀች በግብረ ሥጋ ግንኙነቱ ተበዳይን በበሽታው ያስያዘች እንደሆነ፡፡ | 41 |
| 626/2 | | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዟን እያወቀች ተበዳይን ግብረ ስጋ ግንኙነትን የመሠለ | 42 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| እና<br><br>628/ለ | 10 | ወይም ለንፅኅና ክብር ተቃራኒ የሆነ ነገር እንዲፈፅም በማድረግ በበሽታው ያስያዘች እንደሆነ፡፡ | |
| 626/2<br><br>እና<br><br>628/ሐ | 11 | ተበዳይ በግብረ ስጋ ግንኙነትን በመሠለው ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ በሆነው ድርጊት ምክንያት በደረሰበት ከባድ ኃዘን ወይም ጭንቀት ፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሱን የገደለ እንደሆነ ፡፡ | 43 |

74. **ዕድሜያቸው አስራ ሶስት ዓመት በሆነና አስራ ስምንት ዓመት ባልሞላቸው ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀፅ 626/3 ፣ 626/4/ለ እና 628)**

| የወንጀል ሕግ<br><br>ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን<br><br>(በፅኑ እስራት) |
|---|---|---|---|
| 626/3 | 1 | የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆነው ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊቱ የተፈፀመው ዕድሜው 16 ዓመት ከሞላውና እና አስራ ስምንት ዓመት ካልሞላው ወንድ ህፃን ልጅ ጋር እንደሆነ፡፡ | 15 |
| 626/3 | 2 | የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆነው ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊቱ የተፈፀመው ዕድሜው 13 ዓመት ከሞላው | 20 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | እና አስራ ስድስት ዓመት ካልሞላው ህፃን ልጅ ጋር እንደሆነ ፡፡ | |
| 626/3<br>እና<br>626/4/ሐ | 3 | በደረጃ 1 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛዋ ተማሪ ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የምታሳድገው ልጅ ፣ ወይም እንድትጠብቀው ወይም እንድትንከባከበው በአደራ የተሠጠው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ ከሆነ፡፡ | 23 |
| 626/3 እና 626/4/ሐ | 4 | በደረጃ 2 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛው ተማሪ ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ ፣ የቤት ሠራተኛ ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድገው ልጅ ፣ ወይም እንዲጠብቀው ወይም እንዲከባከበው በአደራ የተሰጠው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ስር የሚገኝ ልጅ እንደሆነ ፡፡ | 25 |
| 626/3 እና 628/ለ | 5 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ የግብረ ስጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅኅና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊት ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ ፡፡ | 38 |
| 626/3 እና 628/ሀ/ | 6 | የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊት ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች እንደሆነ | 39 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 626/3 እና 628/ለ/ | 7 | በደረጃ 5 እና 6 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ፡፡ | 40 |
| 626/3 እና 628/ሐ/ | 8 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ከተበዳይ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነትን የመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅኀና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊት በመፈፀም በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ ፡፡ | 41 |
| 626/3 እና 628/ለ | 9 | በደረጃ 6 እና 8 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ፡፡ | 42 |
| 626/3 እና 628/ሐ | 10 | ተበዳይ በግብረ ስጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊት ምክንያት በደረሰበት ከባድ ኃዘን ወይም ጭንቀት ፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሱን የገደለ እንደሆነ፡፡ | 43 |

75. **በህፃናት ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀፅ 627/1 እና 627/4/ሀ)**

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|

| | | | |
|---|---|---|---|
| 627/1 | 1 | ዕድሜዋ ዘጠኝ ዓመት ከሞላት እና አስራ ሶስት ዓመት ካልሞላት ሴት ህፃን ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ ወይም ኀፃኗ እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት ከእርሱ ጋር እንድትፈፅም ያደረገ እንደሆነ ፡፡ | 38 |
| 627/1 | 2 | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ-1 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ጥፋተኛው ከተበዳይ ወይም ከተበዳይ ቤተሰብ ጋር ቅርበት ያለው ሰው እንደሆነ፡፡ | 39 |
| 627/1 | 3 | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ-1 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ተበዳይ በወንጀሉ ምክንያት ከፍ ያለ ስነ ልቦና ጉዳት የደረሰባት ከሆነ፡፡ | 40 |
| 627/1 | 4 | ዕድሜዋ ዘጠኝ ዓመት ካልሞላት ሴት ህፃን ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የፈፀመ ወይም ኀፃኗ እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት ከእርሱ ጋር እንድትፈፅም ያደረገ እንደሆነ፡፡ | 41 |
| 627/1፣<br><br>627/1<br><br>እና<br><br>627/4/ሀ | 5 | በደረጃ 1 የተመለከተችው ተበዳይ የጥፋተኛው ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድጋት ልጅ ወይም እንዲጠብቃት ወይም እንዲንከባከባት በአደራ የተሰጠችው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥራ የምትገኝ ልጅ እንደሆነች፡፡<br><br>ወይም | 42 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ- 4 (አንቀጽ 627/1) እንደተመለከተው ሆኖ፣ ጥፋተኛው ከተበዳይ ወይም ከተበዳይ ቤተሰብ ጋር ቅርበት ያለው ሰው እንደሆነ፡ | |
| 627/1፣<br>627/1<br>እና<br>627/4/ሀ | 6 | በደረጃ 4 የተመለከተችው ተበዳይ የጥፋተኛው ተማሪ፣የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድጋት ልጅ፣ ወይም እንዲጠብቃት ወይም እንዲንከባከባት በአደራ የተሰጠችው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የምትገኝ ልጅ እንደሆነ፡፡<br>ወይም<br>የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ- 4 (አንቀጽ 627/1) እንደተመለከተው ሆኖ፣ ተበዳይ በወንጀሉ ምክንያት ከፍ ያለ ስነ ልቦና ጉዳት የደረሰባት ከሆነ፡፡ | 43 |

## 76. በህፃናት ልጆች ላይ የሚፈፀም የግብረ ሥጋ ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀፅ 627/2 እና 627/4/ለ፣ 628/ለ፣ 628/ሐ )

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|

| | | | |
|---|---|---|---|
| 627/2 | 1 | የግብረ ሥጋ ግንኙነቱ የተፈፀመው ዕድሜው ዘጠኝ ዓመት ከሞላው እና አስራ ሶስት ዓመት ካልሞላው ወንድ ህፃን ልጅ ጋር እንደሆነ ፡፡ | 23 |
| 627/2 | 2 | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ-1 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ጥፋተኛው ከተበዳይ ወይም ከተበዳይ ቤተሰብ ጋር ቅርበት ያላት ሰው እንደሆነች፡፡ | 25 |
| 627/2 | 3 | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ-1 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ተበዳይ በወንጀሉ ምክንያት ከፍ ያለ ስነ ልቦና ጉዳት የደረሰበት ከሆነ፡፡ | 26 |
| 627/2 | 4 | የግብረ ሥጋ ግንኙነት የተፈፀመው እድሜው ዘጠኝ ዓመት ካልሞላው ወንድ ህፃን ልጅ ጋር እንደሆነ፡፡ | 28 |
| 627/2 | 5 | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ-4 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ጥፋተኛው ከተበዳይ ወይም ከተበዳይ ቤተሰብ ጋር ቅርበት ያላት ሰው እንደሆነች፡፡ | 29 |
| 627/2 | 6 | የወንጀሉ አፈፃፀም በ ደረጃ-4 እንደተመለከተው ሆኖ፣ ተበዳይ በወንጀሉ ምክንያት ከፍ ያለ ስነ ልቦና ጉዳት የደረሰበት ከሆነ፡፡ | 30 |
| 627/2 እና | 7 | በደረጃ 1 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛዋ ተማሪ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የምታሳድገው ልጅ ወይም እንድትጠብቀው ወይም እንድትንከባከበው | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 627/4/ለ | | በአደራ የተሰጣት ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሷ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ እንደሆነ ፡፡ | 31 |
| 627/2 እና 627/4/ለ | 8 | በደረጃ 4 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛዋ ተማሪ፣የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የምታሳድገው ልጅ ወይም እንዲጠብቀው ወይም እንድትንከባከበው በአደራ የተሰጣት ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሷ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥራ የሚገኝ ልጅ እንደሆነ፡፡ | 34 |
| 627/2 እና 628/ለ | 9 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዟን እያወቀች በግብረ ስጋ ግንኙነቱ ተበዳይን በበሽታው ያስያዘች እንደሆነ፡፡ | 41 |
| 627/2 እና 628/ለ | 10 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዟን እያወቀች ከተበዳይ ጋር የግብረ ስራ ግንኙነት በመፈጸም በበሽታው ያስያዘች እንደሆነ፡፡ | 42 |
| 627/2 እና 628/ሐ | 11 | ተበዳይ በግብረ ስጋ ግንኙነቱ ምክንያት በደረሰበት ከባድ ኀዘን ወይም ጭንቀት፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ራሱን የገደለ እንደሆነ፡፡ | 43 |

77. በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 627/3፣ 627/4/ሐ እና 628)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 627/3 | 1 | የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆነው ማናቸውም ሌላ ዓይነት ደርጊቱ የተፈፀመው ዕድሜው ዘጠኝ ዓመት ከሞላው እና አስራ ሶስት ዓመት ካልሞላው ህፃን ልጅ ጋር ከሆነ፡፡ | 25 |
| 627/3 | 2 | የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ የሆነው ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊቱ የተፈፀመው እድሜው ዘጠኝ አመት ካልሞላው ህፃን ልጅ ጋር ከሆነ፡፡ | 30 |
| 627/3 እና 627/4/ሐ | 3 | በደረጃ 1 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛዋ ተማሪ ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ፣ የቤት ሠራተኛ ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የምታሳድገው ልጅ ፣ ወይም እንድትጠብቀው ወይም እንድትንከባከበው በአደራ የተሠጠው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ልጅ ከሆነ ፡፡ | 33 |
| 627/3 እና 627/4/ሐ | | በደረጃ 2 የተመለከተው ተበዳይ የጥፋተኛው ተማሪ ፣ የሙያ መለማመጃ ትምህርት ተማሪ ፣ የቤት ሠራተኛ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 4 | ፣ ወይም ጥፋተኛው በሞግዚትነት የሚያሳድገው ልጅ ፣ ወይም እንዲጠብቀው ወይም እንዲንከባከበው በአደራ የተሰጠው ልጅ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ጥገኝነት ወይም ቁጥጥር ስር የሚገኝ ልጅ እንደሆነ ፡፡ | 36 |
| 627/3 እና 628/ለ | 5 | ሞትን በማያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ የግብረ ስጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅኅና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊት ተበዳይን በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ፡፡ | 37 |
| 627/3 እና 628/ሀ/ | 6 | የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊት ምክንያት ተበዳይ ያረገዘች እንደሆነ፡፡ | 39 |
| 627/3 እና 628/ለ/ | 7 | በደረጃ 5 እና 6 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ፡፡ | 40 |
| 627/3 እና 628/ሐ/ | 8 | ሞትን በሚያስከትል የአባላዘር በሽታ መያዙን እያወቀ ከተበዳይ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነትን የመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅኅና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊት በመፈፀም በበሽታው ያስያዘ እንደሆነ ፡፡ | 41 |
| 627/3 እና 628/ለ | 9 | በደረጃ 6 እና 8 ስር የተመለከቱት መስፈርቶች ተደራርበው የተገኙ እንደሆነ፡፡ | 42 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 626/3 እና 628/ሐ | 10 | ተበዳይ በግብረ ስጋ ግንኙነትን በመሠለ ድርጊት ወይም ለንፅህና ክብር ተቃራኒ በሆነ ማናቸውም ሌላ አይነት ድርጊት ምክንያት በደረሰበት ከባድ ኃዘን ወይም ጭንቀት ፣ ሀፍረት ወይም ተስፋ መቁረጥ የተነሳ ረሱን የገደለ እንደሆነ፡፡ | 43 |

78. በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 627/5)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 627/5 | 1 | ዕድሜው አስራ ሶስት ዓመት ካልሞላው ህጻን ልጅ ጋር የተደረገው የግብረ ስራ ግንኙነት ወይም የግብረ ስጋ ግንኙነትን የመሰለ ድርጊት ወይም ለንጽህና ክብር ተቃራኒ የሆነው ማናቸውም ሌላ ዓይነት ድርጊት በተበዳይ ላይ ከባድ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ እንደሆነ ፡፡ | 44 |

## ርዕስ ሰባት

## በንብረት መብቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች

**79. ጠቅላላ**

1. በወንጀል ህግ አንቀጽ 665 እና 669 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

2. የስርቆት ወንጀልን (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 665) በተመለከተ በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበው የገንዘብ ወይም ንብረት ጥቅም ግምትን መሰረት በማድረግ ጥቅሙ ሲጨምር በጥፋተኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣትም እንዲጨምር ማድረግን ታሳቢ ባደረገ መልኩ፣ የቀላል እስራት እና የፅኑ እስራት አማራጮች ያካተተ የወንጀል ደረጃዎች እና ቅጣት እርከኖች ሰንጠረዥ ተዘጋጅተዋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

   ሀ. የወንጀል ህግ አንቀጽ 665 እና 669 አስመልክቶ በዚህ መመሪያ የተቀመጠው የ ወንጀል ደረጃ እና ቅጣት እርከን ሠንጠረዥ የወንጀል ድርጊት ፈጻሚውን ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ክፍል (intention) ለመቅጣት በቂ አይደለም ተብሎ ሲታመን፣ ፍ/ቤቱ ምክንያቱን በመግለጽ በመመሪያው ከተቀመጠው መነሻ ላይ ሁለት እርከን በማሳደግ የመነሻ ቅጣቱን ሊወስን ይችላል፡፡

   ለ. ወንጀሉ የተፈጸመበት ሰው ወይም ድርጅት በተሰረቀበት ሀብት/ንብረት ምክንያት የእለት ኑሮው ወይም የድርጅቱ ስራ አደጋ ላይ የወደቀ ከሆነ በመጀመሪያ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን በማሳደግ መነሻ ቅጣት ይወሰናል፡፡

   ሐ. የተሰረቀው ንብረት ለምሳሌ ፈንጂ፣ ተቀጣጣይ ወዘተ ከሆነ በመጀመሪያ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን በማሳደግ መነሻ ቅጣት ይወስናል፡፡

   መ. በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ ‹ሀ›፣‹ለ›፣ ‹ሐ› የተመለከቱት ምክንያቶች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ እያንዳንዱ የሚያስጨምረው እርከን ተደምሮ የሚያስገኘው እርከን ድረስ

ከፍ ይላል፡፡ ይሁንና በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለወንጀሉ ከተቀመጠው የቅጣት ጣሪያ በላይ አይሄድም፡፡

4. ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 669 (ከባድ ስርቆት) በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበው የገንዘብ ወይም ንብረት ጥቅም ግምትን እና በድንጋጌው የተመለከቱትን ማክበጃዎች ማለትም ‹የተሰረቀው እቃ ዓይነት›፣ ‹ድርጊቱን የፈጸመው አድራጊ ማንነት›፣ ‹የወንጀል አፈፃፀሙን›መሰረት ባደረገ መልኩ ዘጠኝ የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

5. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 669 የተመለከቱት ሶስቱ ማክበጃ ምክንያቶች የቅጣር ማክበጃ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡

6. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 669 ወንጀሉን የሚያከብዱ ምክንያቶች ከአንድ በላይ ተደራርበው በሚገኙበት ጊዜ የወንጀል ደረጃውና መነሻ ቅጣቱ ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡

7. የወንጀል ህግ አንቀጽ 665 እና 669 አስመልክቶ በወንጀሉ የተገኘውን የጥቅም መጠን መገመት ባልተቻለ ጊዜ ወይም በገንዘብ የሚገመት ካልሆነ ፍ/ቤቱ ምክንያቱን በማስቀመጥ በቅጣት እርከኑ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ባለው ደረጃ እና እርከን መሰረት ሊወስን ይችላል፡፡

8. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 852 የቀላል ስርቆት ደንብ መተላለፍ ድንጋጌ ታሳቢ በማድረግ፣ ለዚህ መመሪያ የስርቆት ወንጀል (በወ.ሕ. አ. 665(1)) ደረጃ አወጣጥ በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበው የገንዘብ ወይም ንብረት ጥቅም ግምት ከ ብር 1001.00 ( ከ አንድ ሽህ አንድ ብር ) እንዲጀምር ተደርጓል፡፡

9. ከላይ በአንቀጽ 94(8) ድንጋጌ ቢኖርም፣ በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበው የገንዘብ ወይም ንብረት ጥቅም ግምት ከ ብር 1001.00 (አንድ ሽህ አንድ ብር) በታች ሆኖ፣ ወንጀሉ የተፈፀመው ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት በሆነ ጊዜ በ ወንጀል ሕግ አንቀጽ 665 (1) መሰረት የሚቀርብን ክስ የሚያስቀር አይሆንም፡፡

80. ስርቆት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 665/1)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | |
|---|---|---|---|---|
| | | | ለ ቀላል እስራት | ለ ፅኑ እስራት |
| 665(1) | 1 | ከ 1,001.00 - 4000.00 ብር | 6 | 8 |
| 665(1) | 2 | ከ 4,001.00 - 7,000.00 | 9 | 12 |
| 665(1) | 3 | ከ 7,001.00 - 30,000 | 13 | 14 |
| 665(1) | 4 | ከ 30,001.00 - 70,000.00 | 14 | 16 |
| 665(1) | 5 | ከ 70,001.00 - 200,000.00 | ----- | 17 |
| 665(1) | 6 | ከ 200,001.00 - 500,000.00 | ------ | 18 |
| 665(1) | 7 | ከ 500,001.00 — 1,000,000.00 | ------ | 19 |
| 665(1) | 8 | ከ 1,000,001.00 - 1,500,000.00 | ------ | 20 |
| 665(1) | 9 | ከ ብር 1,500,000.00 በላይ | ------ | 21 |

## አንቀፅ 96. ከባድ ስርቆት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 669)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 669 | 1 | እስከ ብር 10,000.00 ሆኖ በ አንቀጽ 669 የተመለከተቱት ውስጥ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | 12 |
| 669 | 2 | 1. እስከ ብር 10,000.00 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>2. ከብር 10,001.00 እስከ ብር 15,000.00 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ ፡፡ | 14 |
| 669 | 3 | 1. እስከ ብር 10,000.00 ሆኖ ሶስት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>2. ከብር 10,001.00 እስከ ብር 15,000.00 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>3. ከብር 15,001 እስከ ብር 30,000.00 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | 16 |
| 669 | 4 | 1. ከብር 10,001.00 እስከ ብር 15,000.00 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም<br>2. ከብር 15,001.00 እስከ ብር 30,000.00 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>3. ከብር 30,001.00 እስከ ብር 70,000.00 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | 24 |
| | 5 | 1. ከብር 15,001.00 እስከ ብር 30,000.00 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፣ ወይም<br>2. ከብር 30,001.00 — 70,000.00 ሆኖ ሁለቱ ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም | 26 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 669 | | 3. ከብር 70,001.00 — 350,000.00 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | |
| 669 | 6 | 1. ከብር 30001.00 - 70000.00 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>2. ከብር 70001.00 - 350,000.00 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>3. ከብር 350001.00 — 700,000.00 ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | 28 |
| 669 | 7 | 1. ከብር 70001.00- 350,000.00 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>2. ከብር 350,001.00 — 700,000.00 ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>3. ከብር 700,001.00 በላይ ሆኖ አንድ ማክበጃ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | 30 |
| 669 | 8 | 1. ከብር 350,001.00 — 700,000.00 ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ ወይም<br>2. ከ ብር 700,001.00 በላይ ሆኖ ሁለት ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፡፡ | 32 |
| 669 | 9 | ከ ብር 700,001.00 በላይ ሆኖ ሶስቱም ማክበጃዎች ተሟልተው ሲገኙ፡፡ | 34 |

### 81. <u>የውንብድና ወንጀሎች (670 እና 671)</u>

1. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 እና 671 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

2. የውንብድና ወንጀል የተገኘ ወይም ሊገኝ የታሰበውን የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰ ወይም ሊደርስ የታሰበውን ጉዳት እና የሀይል አጠቃቀሙን መሰረት ባደረገ መልኩ

ለወንጀል ሕግ አንቀፅ 670 ስምንት ፣ ለወንጀል ሕግ 671(1) ዘጠኝ እንዲሁም ፣ ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 671(2) ሁለት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) እንደተመለከተው የሀይል አጠቃቀምን በተመለከተ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የወጣላቸው ሲሆን እነርሱም የማስፈራራቱና ሀይል የመጠቀሙ ተግባር የተፈጸመው፣

    ሀ. ጉዳት የሚያደርስ መሳሪያ ሳይያዝ በሆነ ጊዜ፣ (ዝቅተኛ)

    ለ. ጉዳት የሚያደርስ መሳሪያ ተይዞ ከሆነ (መካከለኛ)

    ሐ. የጦር መሳሪያ በመያዝ ከሆነ (ከፍተኛ) በማለት

እንደቅደም ተከተላቸው የወንጀል አፈፃፀሙን የሚያከብዱ እንደሚሆኑ ታሳቢ በማድረግ የወንጀል ደረጃዎቹ ተዘጋጅተዋል፡፡

4. የወንጀል ሕግ አንቀፅ 671/1 ቅጣቱን ለማክበድ በተቋቋመ የወንበዴ ቡድን አባል መሆንን ያካተተ ስለሆነ፣ በዚህ መሰረት የወንበዴ ቡድን አባል መሆን ቅጣትን የሚያከብድ በሚሆን መልኩ የወንጀል ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ስራ ላይ ውሏል፡፡

## 82. ውንብድና (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 670)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 670 | 1 | ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ እና በወንጀሉ የተገኘው የገንዘብ ጥቅም እስከ ብር 20,000.00 ከሆነ፡፡ | 12 |
| | | 1. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 670 | 2 | የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ በወንጀሉ የተገኘው የገንዘብ ከብር 20,001-100,000 ከሆነ፤<br>ወይም<br>2. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሐይል ተግባር የፈጸመ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም እስከ ብር 20,000 ከሆነ፡፡ | 15 |
| 670 | 3 | 1. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ እና የገንዘብ መጠኑ ከብር 100,001-200,000 ከሆነ<br>ወይም<br>2. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሐይል ተግባር የፈጸመ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም 20,001.00-100,000.00 ከሆነ<br>ወይም<br>3. የጦር መሳሪያ በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እና በወንጀሉ የተገኘ ጥቅም እስከ 20,000.00 ብር ከሆነ ፡፡ | 19 |
| | 4 | 1. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 670 | | የፈጸመ እንደሆነ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ከብር 200,001.00 - 700,000.00 ከሆነ<br>ወይም<br>2. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሐይል ተግባር የፈጸመ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ከብር 100,001.00-200,000.00 ከሆነ<br>ወይም<br>3. የጦር መሳሪያ በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ከ ብር 20,001.00-100,000.00 ከሆነ ፡፡ | 22 |
| 670 | 5 | 1. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ከብር 700,001.00 - 1,000,000.00 ከሆነ<br>ወይም<br>2. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሐይል ተግባር የፈጸመ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ከብር ከብር 200,001.00 - 700,000.00 ከሆነ<br>ወይም | 25 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | 3. የጦር መሳሪያ በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ከብር 100,001.00-200,000.00 ከሆነ፡፡ | |
| 670 | 6 | 1. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እንደሆነ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ከብር ከ 1,000,000.00 በላይ ከሆነ<br>ወይም<br>2. የጦር መሳሪያዎችን በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሐይል ተግባር የፈጸመ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ከብር 700,001.00,- 1,000,000.00 ከሆነ ፡፡<br>ወይም<br>3. የጦር መሳሪያ በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሀይል ተግባር የፈጸመ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ከብር 200,001.00-700,000.00 ከሆነ ፡፡ | 29 |
| 670 | 7 | 1. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሐይል ተግባር የፈጸመ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ከብር 1,000,000.00 በላይ ከሆነ<br>ወይም | 31 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | 2. የጦር መሳሪያ በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሐይል ተግባር የፈጸመ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም ከብር 700,001.00 - 1,000,000.00 ከሆነ፡፡ | |
| 670 | 8 | የጦር መሳሪያ በመያዝ የገጠመውን ተቃውሞ ለማስወገድ ከባድ ዛቻ እና የማንገላታት ተግባር ወይም የሐይል ተግባር የፈጸመ እና በወንጀሉ የተገኘው ጥቅም,ከብር 1,000,000.00 በላይ ከሆነ፡፡ | 34 |

83. ከባድ ውንብድና (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 671/1)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|
| 671/1 | 1 | ወንጀሉ የተፈፀመው ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ሳይዝ፣ ወንጀል ለመፈፀም በተደራጀ የወንበዴ ቡድን ሆኖ፣ የገንዘብ መጠኑ እስከ ብር 20,000.00 የሚደርስ እንደሆነ፡፡ | 23 |
| 671/1 | 2 | 1. ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን በመያዝ ያስፈራራ፣ ወይም የአካል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነና የገንዘቡ መጠን እስከ ብር 20,000.00 የሚደርስ እንደሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ ወንጀል ለመፈፀም የተደራጀ የወንበዴ ቡድን የተፈፀመ ወይም ዘላቂ ያልሆነ የአካል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ እና የገንዘብ መጠኑ እስከ ብር 20,000.00 የሚደርስ እንደሆነ ወይም | 25 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | 3. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 20,001-100,000.00 የሚደርስ እንደሆነ ፡፡ | |
| 671/1 | 3 | 1. የጦር መሳሪያ ይዞ ያስፈራራ ወይም የአካል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነና የገንዘብ መጠኑም እስከ ብር 20,000.00 የሆነ እንደሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ ወንጀል ለመፈፀም የተደራጀ የወንበዴ ቡድን የተፈፀመ ሆኖ ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን ወይም የጦር መሳሪያ በመያዝ ያስፈራራ ወይም ዘላቂ ያልሆነ ጉዳት ያደረሰ ከሆነና የገንዘብ መጠኑም እስከ ብር 20,000.00 የሆነ እንደሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100,001-200,000.00 ከሆነ ወይም፣<br>4. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 20,001-100,000.00 ከሆነ፡፡ | 27 |
| 671/1 | 4 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100001.00-200,000.00 ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 20001.00 - 100000.00 ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ እስከ 20000.00 ከሆነ ፡፡ | 30 |
| 671/1 | 5 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 200001.00-700,000.00 ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 100001.00-200,000.00 ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 20,001.00 - 100,000.00 ከሆነ፡፡ | 33 |
| | | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 700001.00 -1,000,000.00 ከሆነ ወይም | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 671/1 | 6 | 2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 200,001.00 -700,000.00 ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 100,001.00-200,000.00 ከሆነ፡፡ | 35 |
| 671/1 | 7 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 1 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 1,000,001.00 በላይ ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 700,001.00- 1000000.00 ከሆነ ወይም<br>3. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 200001.00-700,000.00 ከሆነ ፡፡ | 37 |
| 671/1 | 8 | 1. ድርጊቱ በደረጃ 2 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 1,000,000.00 በላይ ከሆነ ወይም<br>2. ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር 700,001.00 -1,000,000.00 ከሆነ ፡፡ | 39 |
| 671/1 | 9 | ድርጊቱ በደረጃ 3 የተመለከተው ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከብር 1,000,000.00 በላይ ከሆነ ፡፡ | 40 |

84. ከባድ ውንብድና (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 671/2)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 671/2 | 1 | ወንጀል ለመፈፀም ከተደራጀ ቡድን ጋር በመሆን ወይም የጦር መሳሪያ ወይም ሌላ አደገኛ መሳሪያ በመያዝ የሕዝብ ፀጥታን አደጋ ላይ የሚጥል ወይም የተለየ ጨካኝነትን የሚያሳይ ዘዴን የተጠቀመ ወይም የተፈጸመው | 44 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ተግባር ዘላቂ የአካል ጉዳትን ወይም ሞትን ያስከተለ እንደሆነ፡፡ | | |
| 671/2 | 2 | በጦር መሳሪያ አማካይነት በልማደኛነት በቡድን በሚፈጸም ውንብድና የተለየ ጨካኝነትን የሚያሳይ ዘዴ በመጠቀም የተፈፀመው ተግባር ሞትን ያስከተለ እንደሆነ፡፡ | 45 | |

85. **የማታለል ወንጀሎች** (692 እና 693)

1. በዚህ መመሪያ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 692 እና 693 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በሚረጋገጥባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

2. የአታላይነት ወንጀል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 692) በተመለከተ በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበው የገንዘቡ ወይም ንብረቱ ጥቅም ግምትን መሰረት በማድረግ የጥቅሙን መጨመር ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስር የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. የአታላይነት ወንጀል (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 692)) በቀላል እስራት ወይም እንደ ነገሩ ከባድነት ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና መቀጮ እንደሚያስቀጣ የተደነገገ በመሆኑ፣ ከ ደረጃ 1 እስከ 4 ድረስ ላሉት የወንጀል ደረጃዎች ፣ ሁለቱንም የእስር ቅጣት ዓይነቶች ባገናዘበ መልኩ የቅጣት እርከኖች ተለይተዋል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አንድ እና ሁለት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

    ሀ. የወንጀል ሕግ አንቀጽ 692 አስመልክቶ ፍ/ቤቱ የወንጀል ድርጊት ፈፃሚውን ወንጀል የማድረግ ሀሳብ ክፍል ለመቅጣት በቂ አይደለም ብሎ ሲያምን ምክንያቱን በመግለጽ ሁለት እርከን በማሳደግ የቅጣቱን መነሻ ሊወስን ይችላል፡፡

    ለ. ወንጀሉ የተፈጸመበት ሰው ወይም ድርጅት በማታለሉ ተግባር በተወሰደበት ገንዘብ ወይም ንብረት ምክንያት የእለት ኑሮው ወይም የድርጅቱ ስራ አደጋ ላይ የወደቀ

ከሆነ የገንዘብ መጠኑን መሰረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ወደላይ ያድጋል፡፡

ሐ. የተወሰደው ንብረት ለምሳሌ ፈንጂ፣ ተቀጣጣይ ወዘተ ከሆነ የገንዘብ መጠኑን መሰረት አድርጎ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በሁለት እርከን ወደ ላይ ያድጋል፡፡

መ. በወንጀሉ የተወሰደው ንብረት ለተጎጂው ልዩ ትርጉም ያለው ከሆነና ወንጀል አድራጊውም ይህን እያወቀ የወሰደው ከሆነ በመጀመሪያ ከተመደበበት የቅጣት እርከን በ ሁለት እርከን ወደ ላይ ያድጋል፡፡

ሠ. በዚህ ድንጋጌ በ‹ለ›፣‹ሐ›፣‹መ› የተመለከቱት ምክንያቶች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ፣ እያንዳንዱ የሚያስጨምረው እርከን ተደምሮ የሚያስገኘው እርከን ድረስ ከፍ ይላል፡፡ ይሁንና በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለወንጀሉ ከተቀመጠው የቅጣት ጣሪያ በላይ አይሄድም፡፡

5. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 693 ‹የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት› ወንጀል በተመለከተ የገንዘቡን መጠን መሰረት በማድረግ የጥቅሙን መጨመር ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ አስራ አንድ የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡
6. የወንጀል ሕግ አንቀፅ 693(1) ‹የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት ወንጀል› በቀላል እስራት ወይም እንደ ነገሩ ከባድነት ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና መቀጮ የሚያስቀጣ በመሆኑ፣ ከ ደረጃ 1 እስከ 6 ድረስ ላሉት የወንጀል ደረጃዎች ፣ ሁለቱንም የእስር ቅጣት ዓይነቶች ባገናዘበ መልኩ የቅጣት እርከኖች ተለይተዋል፡፡

**86. አታላይነት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 692/1)**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ |

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀ ሉ ደረጃ | (በኢትዮጵያ ብር) | ለ ቀላል እስራት | ለ ፅኑ እስራት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 692(1) | 1 | እስከ 4000.00 | 6 | 8 | 1 |
| 692(1) | 2 | 4,001.00 - 7,000.00 | 9 | 12 | 2 |
| 692(1) | 3 | ከ 7,001.00 - 30,000.00 | 13 | 14 | 2 |
| 692(1) | 4 | ከ 30,001.00 - 70,000.00 | 14 | 16 | 3 |
| 692(1) | 5 | ከ 70,001.00 - 200,000.00 | ------ | 17 | 3 |
| 692(1) | 6 | ከ 200,001.00 - 500,000.00 | ------ | 18 | 4 |
| 692(1) | 7 | ከ 500,001.00 - 700,000.00 | ------ | 19 | 4 |
| 692(1) | 8 | ከ 700,001.00 - 1,000,000.00 | ------ | 20 | 5 |
| 692(1) | 9 | ከ 1,000,000.00 ብር በላይ | ------- | 21 | 5 |

87. የሚያዙበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት (የወንጀል ሕግ አንቀጽ 693/1)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ (በኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | | የገንዘብ ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ለ ቀላል እስራት | ለ ፅኑ እስራት | |
| 693(1) | 1 | እስከ 35,000.00 | 9 | 10 | 1 |
| 693(1) | 2 | ከ 35,001.00 - 70000.00 | 10 | 12 | 1 |
| 693(1) | 3 | ከ 70,001.00 - 150,000.00 | 11 | 14 | 1 |
| 693(1) | 4 | ከ 150,001.00 - 300,000.00 | 12 | 16 | 2 |
| 693(1) | 5 | ከ 300,001.00 - 600,000.00 | 13 | 18 | 2 |
| 693(1) | 6 | ከ 600,001.00 - 1,100,000.00 | 14 | 20 | 2 |
| 693(1) | 7 | ከ 1,100,001.00 - 2,200,000.00 | ---- | 22 | 3 |
| 693(1) | 8 | ከ 2,200,001 - 5,000,000.00 | ----- | 24 | 3 |
| 693(1) | 9 | ከ 5,000,001.00 - 9,000,000.00 | ----- | 26 | 3 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 693(1) | 10 | ከ 9,000,001.00 - 18,000,000.00 | ----- | 28 | 4 |
| 693(1) | 11 | ከ 18,000,001.00 - 40,000,000.00 | ----- | 29 | 4 |
| 693(1) | 12 | ከ ብር 40,000,000.00 በላይ | ….. | 30 | 4 |

**88. በችልተኝነት የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት (የወ. ሕግ አን. 693/2)**

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 693(2) | 1 | ድርጊቱ የተፈፀመው ባልታወቀ ችልተኝነት ከሆነ፡፡ | 3 | 1 |
| 693(2) | 2 | ድርጊቱ የተፈፀመው በታቀወ ችልተኝነት ከሆነ፡፡ | 4 | 2 |

## ርዕስ- ስምንት

## የቴሌኮሚኒኬሽን እና የኤሌክትሪክ ሃይል አውታሮችን ደህንነት ለመጠበቅ የወጣ አዋጅ በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (አዋጅ ቁጥር 464/1997)

**89. ጠቅላላ**

1. አዋጅ ቁጥር 464/1997 አንቀጽ 4 በመተላለፍ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ክስ ቀርቦባቸው ጥፋተኛነታቸው በፍ/ቤት በሚረጋገጥባቸው ተከሰሾች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው::

2. በአዋጅ ቁጥር 464/1997 አንቀጽ 4 የተመለከተው የወንጀል ድርጊቱ ሊፈፀም የሚችልበትን ሁኔታዎች እና በወንጀል ድርጊቱ የሚገኘው ጥቅም ወይም የሚደርሰው ጉዳት፣ድርጊቱ የተፈፀመበትን ዓለማ ታሣቢ በማድረግ እና ወንጀሉ ሆን ብሎ ከተፈጸመ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው ድረስ በአጠቃላይ 12 የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመው በቸልተኝነት ከሆነ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው ድረስ በአጠቃላይ 5 የወንጀል ደረጃዎች ተጋጅተዋል፡፡

4. የዚህ መመሪያ ክፍል ደረጃ አወጣጥ፣ አዋጅ ቁጥር 464/1997 በመተላለፍ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፣ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 669 (ከባድ ስርቆት) ስር ከተመለከቱት የወንጀል ድርጊቶች የተለየ ክብደት ያላቸው ወንጀሎች መሆናቸውን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

| የወንጀል ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርካን |
|---|---|---|---|
| አዋጅ ቁጥር 464 አንቀጽ 4፣ (የወንጀል | 1 | ማንኛዉም ሰዉ ገንዘቡ ወይም ግምቱ እስከ 50,000 ብር የሆነዉን የሀገር ደህንነትን ወይም ኢኮኖሚን በሚጎዳ ሁኔታ በቴሌኮሙኒኬሽን ወይም በኤሌክትሪክ አውታር ላይ የስርቆት | 21 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ድርጊቱ የተፈመዉ ሆን ተብሎ ከሆነ) | | ተግባር የፈፀመ ወይም ሆን ብሎ ጉዳት ያደረሰ ወይም አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ያደረገ ፡፡ | |
| | 2 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 50,001-70,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 22 |
| | 3 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 70,001-100,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 23 |
| | 4 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 100,001-150,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 25 |
| | 5 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ150,001-200,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 27 |
| | 6 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ200,001-250,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 29 |
| | 7 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ250,001-350,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 31 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 8 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ350,001-450,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 33 |
| | 9 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ450,001-800,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 35 |
| አዋጅ ቁጥር 464 አንቀጽ 4፣ የወንጀል ድርጊቱ የተፈመዉ ሆን ተብሎ ከሆነ | 10 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ800,001-2,000,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 37 |
| | 11 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ2,000,001-10,000,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 39 |
| | 12 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ10,000,000.00 ብር በላይ ከሆነ፡፡ | 41 |
| አዋጅ ቁጥር 464 አንቀጽ 4፣ የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመው | 1 | ግምቱ እስከ 20,000.00 የሆነዉን ጉዳት ያደረሰ ወይም አገልግሎቱ እንዲቋረጥ ያደረገ፡፡ | 4 |
| | 2 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ20,001-50,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 6 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| በቸልኝነት ከሆነ | 3 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ50,001-150,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 8 |
| | 4 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ150,001-500,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 10 |
| | 5 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ500,000.00 ብር በላይ ከሆነ፡፡ | 18 |

## ርዕስ- ዘጠኝ

## የቴሌኮም ማጭበርበር ወንጀል (አዋጅ ቁጥር 761/2004)

**90. ጠቅላላ**

1. አዋጅ ቁጥር 761/2004 አንቀጽ 3፣4 እንዲሁም ከ አንቀጽ 7 እስከ 10 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች በተያያዘ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ የሚባሉ ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች እና በአዋጁ አንቀጽ 11 እና 12 ድንጋጌዎች መሰረት ነዉ፡፡

2. የአዋጁን አንቀጽ 3(1) ተግባራዊ የሚሆነው ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጪ ማንኛውም አይነት የቴሌኮም መሳሪያ ከተመረተ፣ ከተገጣጠመ፣ ከውጭ ሃገር እንዲመጣ ከተደረገ ወይም ከተሸጠ በመሆኑ የተመረተው ወይም የተገጣጠመው ወይም ከውጭ አገር እንዲመጣ የተደረገው ወይም እንዲሸጥ የተደረገው የቴሌኮም መሳሪያ የገበያ ዋጋ አነስተኛ ግምት የሚሰጠው ሆኖ ወንጀሉ ቀላል በሚሆንበት ጊዜ በመሆኑ ለዚህ ንዑስ ድንጋጌ አፈጻጸም፡-

   ሀ. እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺ) ግምት ያላቸዉ የቴሌኮም መሳሪያዎች በጣም አንስተኛ ግምት ያላቸዉ ተደርገዉ ተወስደዋል፡፡

   ለ. ከብር 200.001 (ሁለት መቶ ሺህ አንድ ብር) እስከ ብር 400.000.00 (አራት መቶ ሺህ ብር) ድረስ ግምት ያላቸው የቴሌኮም መሳሪያዎች አንስተኛ ግምት ተደርጎ ተወስዷል፡፡

   ሐ. ከብር 400,001.00 (አራት መቶ ሺህ አንድ ብር) እስከ ብር 650,000.00 (ስድስት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ድረስ ግምት ያላቸው የቴሌኮም መሳሪያዎች መካከለኛ ግምት ተደርጎ ተወስዷል፡፡

   መ. ከብር 651,000.00 (ከስድስት መቶ ሃምሳ ሺህ አንድ ብር) እስከ 1,500,000.00 (አንድ ሚሊዩን አምስት መቶ ሺህ ብር) ድረስ ግምት ያላቸው የቴሌኮም መሳሪያዎች ከፍተኛ ግምት ተደርጎ ተወስዷል፡፡

ሠ. ከብር 1,500,000.00 (አንድ ሚሊዩን አምስት መቶ ሺህ ብር) በላይ ግምት ያላቸው ቴሌኮም መሳሪያዎች ደግሞ በጣም ከፍተኛ ግምት ያላቸው ተደርገው ተወስደዋል፡፡

ረ. የቴሌኮም መሳሪያዎቹ ቁጥር ከአንድ በላይ ከሆነ ግምቱ የሚያዘዉ የመሳሪያዎቹ ግምት ድምር ዉጤት ይሆናል፡፡

3. የአዋጁን አንቀፅ 3(2) ተግባራዊ የሚሆነው ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጪ ማንኛውም አይነት የቴሌኮም መሳሪያ በሚጠቀም ወይም ይዞ በሚገኝ ሰው በመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ መሠረት ቅጣት ለመወሰን በወንጀሉ የተገኘው ወይም ሊገኝ የታሰበው የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰው ወይም ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ወይም የመሳሪያው ግምትን መሠረት በማድረግ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ለዚሁ ድንጋጌ አፈጻጸም፡-

ሀ. በጣም ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት እስከ ብር 150,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺ. ብር) ሲሆን ነው፡፡

ለ. ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር 150,001 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ አንድ ብር) እስከ 250,000.00 (ሁለት መቶ አምሳ ሺ. ብር) ሲሆን ነዉ፡፡

ሐ. መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር 250,001.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ አንድ ብር) እስከ 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ ብር) ሲሆን ነው፡፡

መ. ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር 500,001.00 (አምስት መቶ ሺህ አንድ ብር) እስከ ብር 1,500,000.00 (አንድ ሚሊዩን አምስት መቶ ሺህ ብር) ሲሆን ነው፡፡

ሠ. በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰዉ ጉዳት ከብር 1,500,000 (አንድ ሚሊየን አምስት መቶ ሺ. ብር) በላይ ሲሆን ነዉ፡፡

4. ለአዋጁ አንቀጽ 4፣ 7(1) ወይም 7(2)፣ አንቀጽ 8 (1)፣ አንቀጽ 9(1) (ሀ) ወይም (1)፣ እና 10 (1)፣ 10 (2)(ሀ) ወይም (2)(ለ)) እና 10(3) ድንጋጌዎች ጥቅም ወይም ጉዳት ማለት የተገኘውን ወይም ሊገኝ የታሰበውን ጥቅም እንዲሁም የደረሰውን ወይም ሊደርስ የታሰበውን ጉዳት የሚያካትት በመሆኑ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የወንጀሉ ደረጃ የወጣው የገንዘቡን መጠን መሰረት በማድረግ ነዉ፡፡

ሀ. በተፈጸመው ወንጀል የተገኘውን የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰውን ጉዳት በገንዘብ ገምቶ ለማስቀመጥ የማይቻል በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ምክንያቱን በማስቀመጥ የተገኘውን የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰዉ ጉዳት መጠን ደረጃ ይወሰናል፡፡

ለ. በተፈጸመዉ ወንጀል የተገኘዉ ጥቅምና የደረሰዉ ጉዳት የሚታወቅ ከሆነ ደረጃውን ለመወሰን ከሁለቱ የሚልጠዉ ይወሰዳል፡፡

91. **ቴሌኮም መሳሪያዎች ጋር የተያያዙ ወንጀሎች (የአዋጅ ቁጥር 761/2004 አንቀጽ 3(1) እና (2)**

| የወንጀሉ ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| | 1 | አንስተኛ ግምት ያለዉ/ላቸዉ የቴሌኮም መሳሪያ/ዎች ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጪ ማንኛውም አይነት የቴሌኮም መሳሪያ የሚያመርት፣ የሚገጣጥም፣ ከውጭ ሃገር የሚያስመጣ ወይም የሚሸጥ፡፡ | 21 | 12 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3(1) | 2 | መካከላኛ ግምት ያለዉ/ላቸዉ የቴሌኮም መሳሪያ/ዎች ሆኖ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጪ ማንኛውም አይነት የቴሌኮም መሳሪያ የሚያመርት፣ የሚገጣጥም፣ ከውጭ ሃገር የሚያስመጣ ወይም የሚሸጥ፡፡ | 23 | 13 |
| | 3 | ከፍተኛ ግምት ያለዉ/ላቸዉ የቴሌኮም መሳሪያ/ዎች ሆኖ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጪ ማንኛውም አይነት የቴሌኮም መሳሪያ የሚያመርት፣ የሚገጣጥም፣ ከውጭ ሃገር የሚያስመጣ ወይም የሚሸጥ፡፡ | 25 | 14 |
| | 4 | በጣም ከፍተኛ ግምት ያለዉ/ላቸዉ የቴሌኮም መሳሪያ/ዎች ሆኖ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጪ ማንኛውም አይነት የቴሌኮም መሳሪያ የሚያመርት፣ የሚገጣጥም፣ ከውጭ ሃገር የሚያስመጣ ወይም የሚሸጥ፡፡ | 27 | 15 |
| | 5 | አንስተኛ ግምት ያለዉ/ላቸዉ የቴሌኮም መሳሪያ/ዎች ሆኖ አራቱ መስፈርት ወይም መካከለኛ ግምት ሆኖ ሶስቱ መስፈርት ወይም ከፍተኛ ሆኖ ሁለቱ መስፈርቶች ተሟልተው ከተገኙ፡፡ | 30 | |
| | 6 | መከካለኛ ግምት ያለዉ/ላቸዉ ሆኖ አራቱ መስፈርቶች ወይም ከፍተኛ ግምት ሆኖ ሶስቱ መስፈርቶች ወይም በጣም ከፍተኛ ሆኖ ሁለቱ መስፈርቶች ተሞልተው ከተገኙ፡፡ | 32 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 7 | ከፍተኛ ግምት ያለዉ/ላቸዉ ሆኖ አራቱ መስፈርት ወይም በጣም ከፍተኛ ግምት ሆኖ ሶስቱ መስፈርቶች ተሟልተው ከተገኙ፡፡ | 34 | |
| | 8 | በጣም ከፍተኛ ግምት ያለዉ/ላቸዉ ሆኖ አራቱ መስፈርቶች ተሟልተው ከተገኙ፡፡ | 35 | |
| 3(2) | 1 | በጣም ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት ወይም አነስተኛ ግምት ያለዉ/ላቸዉ የቴሌኮም መሳሪያ/ዎች ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጪ ማንኛውም አይነት የቴሌኮም መሳሪያ የሚጠቀም ወይም ይዞ የሚገኝ፡፡ | 5 | 6 |
| | 2 | ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት ወይም አነስተኛ ግምት ያለዉ/ላቸዉ የቴሌኮም መሳሪያ/ዎች ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጪ ማንኛውም አይነት የቴሌኮም መሳሪያ የሚጠቀም ወይም ይዞ የሚገኝ፡፡ | 6 | 7 |
| | 3 | መካከላኛ ጥቅም/ጉዳት ወይም አነስተኛ ግምት ያለዉ/ላቸዉ የቴሌኮም መሳሪያ/ዎች ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጪ ማንኛውም አይነት የቴሌኮም መሳሪያ የሚጠቀም ወይም ይዞ የሚገኝ፡፡ | 7 | 8 |
| | 4 | ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት ወይም አነስተኛ ግምት ያለዉ/ላቸዉ የቴሌኮም መሳሪያ/ዎች ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጪ ማንኛውም አይነት | 8 | 9 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የቴሌኮም መሳሪያ የሚጠቀም ወይም ይዞ የሚገኝ፡፡ | | |
| | 5 | በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት ወይም አነስተኛ ግምት ያለዉ/ላቸዉ የቴሌኮም መሳሪያ/ዎችከሚኒስቴሩ ፈቃድ ውጪ ማንኛውም አይነት የቴሌኮም መሳሪያ የሚጠቀም ወይም ይዞ የሚገኝ፡፡ | 9 | 9 |
| | 6 | ዝቅተኛ ሆኖ ሶስቱ መስፈርቶች ተሟልተው ከተገኙ ወይም መካከለኛ ሆኖ ሁለቱ ተሟልተው ከተገኙ፡፡ | 10 | |
| | 7 | መካከለኛ ሆኖ ሶስቱ መስፈርቶች ተሟልተው ከተገኙ ወይም ከፍተኛ ሆኖ ሁለቱ መስፈርቶች ተሟልተው ከተገኙ፡፡ | 12 | |
| | 8 | ከፍተኛ ሆኖ ሶስቱ መስፈርቶች ተሟልተው ከተገኙ ወይም በጣም ከፍተኛ ሆኖ ሁለቱ መስፈርቶች ተሟልተው ከተገኙ፡፡ | 14 | |
| | 9 | በጣም ከፍተኛ ሆኖ ሶስቱ መስፈርቶች ተሟልተው ከተገኙ፡፡ | 15 | |

92. ቴሌኮም መሳሪያዎች ጋር የተያያዙ ወንጀሎች (የአዋጅ ቁ. 761/2004 አንቀጽ 4)

| አንቀጽ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት እርከን | የገንዘብ መቀጮ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 4 | 1 | እስከ ብር 100,000.00 | 26 | ሶስት እጥፍ |
| | 2 | ከብር 100,001.00 - 200,000 | 27 | ሶስት እጥፍ |
| | 3 | ከብር 200,001.00 - 400,000 | 28 | ሶስት እጥፍ |
| | 4 | ከብር 400,001.00 - 600,000 | 29 | ሶስት እጥፍ |
| | 5 | ከብር 600,001.00 -1,000,000.00 | 30 | ሶስት እጥፍ |
| | 6 | ከብር 1,000,001.00 - 2,000,000.00 | 31 | ሶስት እጥፍ |
| | 7 | ከብር 2,000,001.00 - 4,000,000.00 | 32 | ሶስት እጥፍ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 8 | ከብር 4,000,001.00 - 6,000,000.00 | 33 | ሶስት እጥፍ |
| | 9 | ከብር 6,000,001.00 - 10,000,000.00 | 34 | ሶስት እጥፍ |
| | 10 | ከብር 10,000,001.00 - 15,000,000.00 | 35 | ሶስት እጥፍ |
| | 11 | ከብር 15,000,000.00 በላይ | 36 | ሶስት እጥፍ |

## 93. የአገልግሎት ዋጋ የማጭበርበር ወንጀል (አንቀጽ 7)

| የአዋጁ አንቀጽ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት እርከን | የገንዘብ መቀጮ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 7(1) ወይም 7(2) | 1 | እስከ ብር 100,000.00 | 21 | ተጭበርብራል ተብሎ የተገመተዉ ገንዘብ ሶስት እጥፍ |
| | 2 | ከብር 100,001.00-200,000.00 | 22 | ተጭበርብራል ተብሎ የተገመተዉ ገንዘብ ሶስት እጥፍ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3 | ከብር 200,001.00-400,000.00 | 23 | ተጭበርብራል ተብሎ የተገመተዉ ገንዘብ ሶስት እጥፍ |
| | 4 | ከብር 400,001.00-600,000.00 | 24 | ተጭበርብራል ተብሎ የተገመተዉ ገንዘብ ሶስት እጥፍ |
| | 5 | ከብር 600,001.00-1,000,000.00 | 25 | ተጭብርብራል ተብሎ የተገመተዉ ገንዘብ ሶስት እጥፍ |
| | 6 | ከ ብር 1,000,001.00-4,000,000.00 | 26 | ተጭበርብራል ተብሎ የተገመተዉ ገንዘብ ሶስት እጥፍ |
| | 7 | ከብር 4,000,001.00-8000,000.00 | 27 | ተጭበርብራል ተብሎ የተገመተዉ ገንዘብ ሶስት እጥፍ |
| | 8 | ከብር 8,000,001.00-12,000,000.00 | 28 | ተጭበርብራል ተብሎ የተገመተዉ ገንዘብ ሶስት እጥፍ |
| | 9 | ከ 12,000,001.00 -15,000,000.00 | 29 | ተጭበርብራል ተብሎ የተገመተዉ ገንዘብ ሶስት እጥፍ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 10 | ከ 15,000,00.00 በላይ | 30 | ተጭበርብራል ተብሎ የተገመተዉ ገንዘብ ሶስት እጥፍ |

## 94. የኮልባክ አገልግሎትን ስለሚመለከቱ ወንጀሎች (የአዋጅ ቁ.761/2004 አንቀጽ 8)

| | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርካን |
|---|---|---|---|---|
| 8(1) | 1 | እስከ ብር 100,000.00 | 21 | የገቢዉ አምስት እጥፍ |
| | 2 | ከብር 100,001.00-200,000.00 | 22 | የገቢዉ አምስት እጥፍ |
| | 3 | ከብር 200,001.00-400,000.00 | 24 | የገቢዉ አምስት እጥፍ |
| | 4 | ከብር 400,001.00-600,000.00 | 26 | የገቢዉ አምስት እጥፍ |
| | 5 | ከብር 600,001.00-1,000,000 | 28 | የገቢዉ አምስት እጥፍ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 6 | ከብር 1,000,001.00-4,000,000 | 29 | የገቢ.ዉ. አምስት እጥፍ |
| | 7 | ከብር 4,000,000.00 በላይ | 30 | የገቢ.ዉ. አምስት እጥፍ |

95. **ሕገ ወጥ የቴሌኮም ኦፐሬተርን ስለሚመለከቱ ወንጀሎች** (**የአዋጅ ቁ.** 761/2004 **አንቀጽ** 9)

| አንቀጽ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት እርከን | የገንዘብ መቀጮ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 9(1)(ሀ) ወይም 9(1) (ለ) | 1 | እስከ ብር 100,000.00 | 31 | የገቢ.ዉ. አስር እጥፍ |
| | 2 | ከብር 100,001.00 - 200,000.00 | 32 | የገቢ.ዉ. አስር እጥፍ |
| | 3 | ከብር 200,001 - 400,000.00 | 33 | የገቢ.ዉ. አስር እጥፍ |
| | 4 | ከብር 400,001 - 600,000.00 | 34 | የገቢ.ዉ. አስር እጥፍ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 5 | ከብር 600,001-1,000,000.00 | 35 | የገቢ.ወ. አስር እጥፍ |
| | 6 | ከብር 1,000,001 - 2,000,000.00 | 36 | የገቢ.ወ. አስር እጥፍ |
| | 7 | ከብር 2,000,001 - 4,000,000.00 | 37 | የገቢ.ወ. አስር እጥፍ |
| | 8 | ከብር 4,000,001.00 - 6,000,000.00 | 38 | የገቢ.ወ. አስር እጥፍ |
| | 9 | ከብር 6,000,001-10,000,000 | 39 | የገቢ.ወ. አስር እጥፍ |
| | 10 | ከብር 10,000,001 - 15,000,000 | 40 | የገቢ.ወ. አስር እጥፍ |
| | 11 | ከ ብር 15,000,000 በላይ | 41 | የገቢ.ወ. አስር እጥፍ |

**96. ሌሎች ወንጀሎች (የአዋጅ ቁ፤ 761/2004 አንቀጽ 10)**

| የወንጀል ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 10(1) | 1 | እስከ ብር 100,000.00 | 31 | ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚገመት ውን ገቢ አስር እጥፍ |
| | 2 | ከብር 100,001.00-500,000.00 | 32 | ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚገመት ውን ገቢ አስር እጥፍ |
| | 3 | ከብር 500,001-1000,000.00 | 33 | ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚገመት ውን ገቢ አስር እጥፍ |
| | 4 | ከብር 1,000,001 - 5,000,000.00 | 34 | ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚገመት ውን ገቢ አስር እጥፍ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 5 | ከብር 5,000,001-10,000,000.00 | 35 | ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚገመት ውን ገቢ አስር እጥፍ |
| | 6 | ከብር 10,000,000.00 ብር በላይ | 36 | ሊያገኝ ይችላል ተብሎ የሚገመት ውን ገቢ አስር እጥፍ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 10(2)(ሀ) ወይም (ለ) | 1 | እስከ ብር 100,000.00 | 13 | 8 |
| | 2 | ከብር 100,001.00 - 200,000.00 | 14 | 8 |
| | 3 | ከብር 200,001.00 - 400,000.00 | 15 | 9 |
| | 4 | ከብር 400,001.00 - 600,000.00 | 16 | 9 |
| | 5 | ከብር 600,001.00 - 1,000,000.00 | 17 | 10 |
| | 6 | ከብር 1,000,001.00 - 2,000,000.00 | 18 | 10 |
| | 7 | ከብር 2,000,001 - 4,000,000.00.00 | 19 | 11 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 8 | ከብር 4,000,001 - 6,000,000.00 | 20 | 11 |
| | 9 | ከብር 6,000,001-10,000,000.00 | 22 | 12 |
| | 10 | ከብር 10,000,001 - 15,000,000.00 | 24 | 12 |
| | 11 | ከብር 15,000,000 በላይ | 26 | 12 |
| 10(3) | 1 | እስከ 50,000.00 | 13 | የገቢ.ወ. አምስት እጥፍ |
| | 2 | ከብር 50,001 - 150,000.00 | 14 | የገቢ.ወ. አምስት እጥፍ |
| | 3 | ከብር 150,001.00 - 200,000.00 | 15 | የገቢ.ወ. አምስት እጥፍ |
| | 4 | ከብር 200,001.00 - 400,000.00 | 16 | የገቢ.ወ. አምስት እጥፍ |
| | 5 | ከብር 400,001.00 - 600,000.00 | 17 | የገቢ.ወ. አምስት እጥፍ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 6 | ከብር 600,001.00 - 1,000,000.00 | 18 | የገቢ.ወ. አምስት እጥፍ |
| | 7 | ከብር 1,000,001.00 - 2,000,000.00 | 20 | የገቢ.ወ. አምስት እጥፍ |
| | 8 | ከብር 2,000,001.00 - 4,000,000.00 | 21 | የገቢ.ወ. አምስት እጥፍ |
| | 9 | ከብር 4,000,001.00 - 6,000,000.00 | 22 | የገቢ.ወ. አምስት እጥፍ |
| | 10 | ከ 6,000,001.00 - 10,000,000.00 | 23 | የገቢ.ወ. አምስት እጥፍ |
| | 11 | ከ 10,000,001.00 - 13,000,000.00 | 24 | የገቢ.ወ. አምስት እጥፍ |
| | 12 | ከ 13,000,001 - 15,000,000.00 | 25 | የገቢ.ወ. አምስት እጥፍ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 13 | ከ 15,000,000.00 በላይ | 26 | የገቢ.ወ. አምስት እጥፍ |

## <u>ርዕስ - አስር</u>

## <u>በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ( አዋጅ ቁጥር 780/2005) ፤ በአዋጅ ቁጥር 1387/2017 እንደተሻሻለው፡፡</u>

**97. ጠቅላላ**

1. አዋጅ ቁጥር 780/2005) (በአዋጅ ቁጥር 1387/2017 እንደተሻሻለው) በመተላለፍ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ንብረት ወይም ገንዘብ ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል ጥፋተኛ በተባሉ ተከሳሾች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው::

2. በ አንቀጽ 29(1)-(3) የተመለከቱት የወንጀል ድንጋጌዎች ድርጊቱ ሊፈፀም የሚችልበትን ሁኔታዎች፣ድርጊቱ የተፈፀመበትን ዓላማ እና በወንጀል ድርጊቱ የ ተመለከተው የገንዘብ ወይም ንብረት መጠን እና ታሣቢ በማድረግ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው ድረስ በአጠቃላይ 4 የወንጀል ደረጃዎች የተዘጋጁ ሲሆን፤ ለ አንቀፅ 29(4) በወንጀሉ የተመለከተውን የ የገንዘብ ወይም ንብረት መጠን መሰረት በማድረግ 5 የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. በ አንቀጽ 29(5) የተመለከተው የወንጀል ድርጊቱ ሊፈፀም የሚችልበትን ሁኔታ ፣ ከወንጀል ድርጊቱ ተመለከተው የገንዘብ ወይም ንብረት መጠን እና በ በአዋጁ አንቀጽ 29(5) ስር የተዘረዘሩ የማክበጃ ምክንያቶች ጋር በማጣመር በአጠቃላይ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው 6 የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀል ደረጃዉ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የመቀጮ ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| አንቀጽ 29(1) (በአዋጅ ቁጥር 1387/2017 እንደተሻሻለው፡፡) | 1 | ማንኛውም ሰው እስከ 2,000,000.00 ብር የሆነን ንብረት ወይም ገንዘብ፤<br><br>ሀ. የንብረቱን ሕገ-ወጥ ምንጭ ለመደበቅ ወይም ለመሸፈን ወይም አመንጭዉን ወንጀል የፈጸመው ሰው ከሕግ ተጠያቂነት እንዲያመልጥ ለማድረግ ንብረቱን የለወጠ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ፤ ወይም<br><br>ለ. ንብረቱን፣ የንብረቱን ትክክለኛነት፣ ምንጩን፣ ቦታዉን፣ ዝዉዉሩን ወይም የባለቤትነት መብትን የደበቀ ወይም እንዳይታወቅ ያደረገ እንደሆነ፡፡ | 33 | 14 |
| | 2 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 2,000,001-4,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 34 | 15 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 4,000,001- 10,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 35 | 16 |
| | 4 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 10,000,001-19,999,999 ብር ከሆነ፡፡ | 36 | 18 |
| አንቀጽ 29(2) (በአዋጅ ቁጥር 1387/2017 እንደተሻሻለ ው፡፡) | 1 | የድንጋጌው ንዑስ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ከአመንጭ ወንጀል ፈጻሚው ውጭ የሆነ ሦስተኛ ወገን፣ ገንዘቡ ወይም ግምቱ እስከ 2,000,000.00 ብር የሆነ ንብረት የወንጀል ፍሬ መሆኑን እያወቀ የተረከበ፣ በይዞታ ያደረገ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ፡፡ | 33 | 14 |
| | 2 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 2,000,001- 4,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 34 | 15 |
| | 3 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 4,000,001 - 10,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 35 | 16 |
| | 4 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 10,000,001 - 19,999,999.00 ብር ከሆነ፡፡ | 36 | 18 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አንቀጽ 29(3) (በአዋጅ ቁጥር 1387/2017 እንደተሻሻለ ው፡፡) | 1 | በድንጋጌው በንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሱትን ወንጀል የሚፈጽምን ሰው ለመርዳት ያደመ፣ የሞከረ፣ የደገፈ፣ ያመቻቸ ወይም እንዲፈጸም ያማከረ ሆኖ ንብረቱ እስከ 2,000,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 33 | 14 |
| | 2 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 2,000,001 - 4,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 34 | 15 |
| | 3 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 4,000,001 - 10,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 35 | 16 |
| | 4 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ10,000,001 - 19,999,999 ብር ከሆነ፡ | 36 | 18 |
| አንቀጽ 29(4) ( በአዋጅ ቁጥር 1387/2017 እንደተሻሻለ ው፡፡) | 1 | በድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) እና (3) ላይ የተዘረዘሩትን ድርጊቶች በቸልተኝነት የፈጸመ ሆኖ ንብረቱ እስከ 2,000,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 23 | 10 |
| | 2 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 2,000,001 - 4,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 25 | 11 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 4,000,001 - 10,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 27 | 12 |
| | 4 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 10,000,001-15,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 29 | 13 |
| | 5 | ከላይ በደረጃ 1 ስር የተዘረዘሩት የወንጀሉ መቋቋሚያ እንደጠበቀ ሆኖ ግምቱ ከ 15,000,001 - 19,999,999 ብር ከሆነ፡፡ | 30 | 14 |
| አንቀጽ 29(5)<br>(በአዋጅ ቁጥር 1387/2017 እንደተሻሻለ ው፡፡) | 1 | 1. ህጋዊ እንዲመስል ተደርጎ የቀረበዉ በወንጀል ድርጊት የተገኘዉ ገንዘብ ወይም የንብረት ግምት ከ 20,000,000.00 - 25,000,000.00 ብር ከሆነ፡፡ ወይም<br>2. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ እስከ 10,000,000.00 ብር ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 29(5) ስር በፊደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ከተገኘ፡፡ | 38 | 16 |
| | 2 | 1. ህጋዊ እንዲመስል ተደርጎ የቀረበዉ በወንጀል ድርጊት የተገኘዉ ገንዘብ ወይም የንብረት ግምት ከ | 39 | 17 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 25,000,001.00 - 30,000,000.00 ብር ከሆነ ፡፡ ወይም<br>2. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ከ 20,000,000.00 - 25,000,000.00 ብር ሆኖ፤ በአንቀጽ 29(5) ስር በፊደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ከተገኘ፡፡ ወይም<br>3. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ እስከ 10,000,000.00 ብር ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 29(5) ስር በፊደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተው ከተገኙ፡፡ | | |
| | 3 | 1. ህጋዊ እንዲመስል ተደርጎ የቀረበዉ በወንጀል ድርጊት የተገኘዉ ገንዘብ ወይም የንብረት ግምት ከ 30,000,001.00 - 40,000,000.00 ብር ከሆነ፡፡ ወይም<br>2. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ከ 25,000,001.00 - 30,000,000.00 ብር ሆኖ፤ በአንቀጽ 29(5) ስር በፊደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ከተገኘ፡፡ ወይም<br>3. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ከ 10,000,001.00 - 20,000,001.00 ብር ሆኖ፤ በአንቀጽ 29(5) ስር በፊደል | 40 | 18 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተው ከተገኙ፡፡ ወይም<br>4. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ እስከ 10,000,000.00 ብር ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 29(5) ስር በፊደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሶስቱ ተሟልተው ከተገኙ፡ | | |
| | 4 | 1. ህጋዊ እንዲመስል ተደርጎ የቀረበዉ በወንጀል ድርጊት የተገኘዉ ገንዘብ ወይም የንብረት ግምት ከ 40,000,001.00 - 50,000,000.00 ብር ከሆነ፡፡ ወይም<br>2. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ከ 30,000,001.00 - 40,000,000.00 ብር ሆኖ፤ በአንቀጽ 29(5) ስር በፊደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ከተገኘ፡፡ ወይም<br>3. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ከ 25,000,001.00 - 30,000,001.00 ብር ሆኖ፤ በአንቀጽ 29(5) ስር በፊደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተው ከተገኙ፡፡ ወይም<br>4. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ 10,000,001.00 እስከ 20,000,000.00 ብር ሆኖ በአዋጁ | 41 | 19 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አንቀጽ 29(5) ስር በፌደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሶስቱ ተሟልተው ከተገኙ፡፡ ወይም<br>5. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ እስከ 10,000,000.00 ብር ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 29(5) ስር በፌደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አራቱ ተሟልተው ከተገኙ፡፡ | | |
| | 5 | 1. ህጋዊ እንዲመስል ተደርጎ የቀረበዉ በወንጀል ድርጊት የተገኘዉ ገንዘብ ወይም የንብረት ግምት ከ 50,000,001.00 - 60,000,000.00 ብር ከሆነ፡፡ ወይም<br>2. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ከ 40,000,001.00 - 50,000,000.00 ብር ሆኖ፣ በአንቀጽ 29(5) ስር በፌደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ከተገኘ፡፡ ወይም<br>3. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ከ 30,000,001.00 - 40,000,001.00 ሆኖ፣ በአንቀጽ 29(5) ስር በፌደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተው ከተገኙ፡፡ ወይም | 42 | 20 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 4. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ከ 25,000,001.00 - 30,000,000.00 ብር ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 29(5) ስር በፊደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሶስቱ ተሟልተው ከተገኙ፡፡ ወይም<br>5. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ከ 20,000,001.00 - 25,000,000.00 ብር ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 29(5) ስር በፊደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አራቱ ተሟልተው ከተገኙ፡፡ | | |
| | 6 | 1. ህጋዊ እንዲመስል ተደርጎ የቀረበዉ በወንጀል ድርጊት የተገኘዉ ገንዘብ ወይም የንብረት ግምት ከ 60,000,001.00 ብር በላይ ከሆነ፡፡ ወይም<br>2. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ከ 50,000,001.00 - 60,000,000.00 ብር ሆኖ፤ በአንቀጽ 29(5) ስር በፊደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ከተገኘ፡፡ ወይም<br>3. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ከ 40,000,001.00 - 50,000,001.00 ሆኖ፤ በአንቀጽ 29(5) ስር በፊደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ | 43 | 21 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተው ከተገኙ፡፡ ወይም<br>4. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ ከ 30,000,001.00 - 40,000,000.00 ብር ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 29(5) ስር በፊደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሶስቱ ተሟልተው ከተገኙ፡፡ ወይም<br>5. ገንዘቡ ወይም ንብረቱ 25,000,001.00 ብር በላይ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 29(5) ስር በፊደል ሀ፣ለ፣ሐ፣ሠ የተጠቀሱት የወንጀሉ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አራቱ ተሟልተው ከተገኙ፡፡ | | |

## ርዕስ- አስራ አንድ

## የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅ ( አዋጅ ቁጥር 881/2007)

### 98. ጠቅላላ

1. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9፣13፣23፣25 እና 32 ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በፍርድ ቤት በተረጋገጠባቸው ወንጀል አድራጊዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡

2. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9 እና አንቀጽ 13 ቅጣት ለመወሰን በድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ውስጥ ያሉትን መስፈርቶች ማለትም ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ፤ የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት፤ የጥፋተኛው የኃላፊነት ወይም የሥልጣን ደረጃ፤ በግለሰብ፣ በመንግሥት ወይም በሕዝባዊ ድርጅት ወይም በሕዝብ ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት እንዲሁም የጥፋተኛው ልዩ ሃላፊነት ወይም እምነት መሠረት በማድረግ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ፣ለአንቀጽ 9/1 እና 13(1) አስራ አንድ፣ ለአንቀጽ 9/2 እና 13(2) አስራ አራት እና ለአንቀጽ 9/3 እና 13(3) አስራ ሰባት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. የአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9(1)፣13(1)፣23(1)፣25(1) እና 32(1) የተደነገጉት ቀላል እስራት ወይም በፅኑ እስራት በአማራጭነት እንደሚያስቀጡ የተደነገገ ቢሆንም፤ በዚህ መመሪያ ደረጃ እና እርከን የወጣው ለጽኑ እስራት አማራጭ ብቻ ነዉ፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ ለእነኝህ ወንጀሎች የቀላል እስራት አማራጭ የሚመረጥ ከሆነ ወንጀሉ ደረጃ እንዳልወጣለት ተቆጥሮ ቅጣት የሚሰላ ይሆናል፡፡

4. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም አፈጻጸም ስባል የሙስና ወንጀልን በተመለከተ ብቻ፡-

    ሀ. ከፍተኛ ሥልጣን፤- ማለት የመንግስት መስሪያ ቤት ከሆነ በተሻሻለው የፌዴራል ሥነምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2/5 (እንደተሻሻለዉ በአዋጅ ቁጥር 883/2007 እንደተሻሻለ) አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀጽ 2(6)፣በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(6) ውስጥ የተዘረዘሩ ስሆን የሕዝባዊ ድርጅትና የመንግሥት የልማት ድርጅት ከፍተኛ ስልጣን ማለት በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀጽ 2(8) እና 2(9) ላይ የተዘረዘሩት አካለት ነቸዉ፡፡

ለ. መካከለኛ ስልጣን፤- ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሀ› ውስጥ የማይካተቱ ነገር ግን ውሳኔ የሚወስኑ የሥራ ኀላፊነት ቦታዎች ማለትም የመምሪያ ኀላፊዎች፡ የሥራ ሂደት መሪዎች፣ ለመስሪያ ቤቱ የበላይ ኀላፊ ተጠሪ የሆኑ ኀላፊዎች፣ የዞን ኀላፊዎች፡ የወረዳ ኀላፊዎችና በዞንና በወረዳ መስተዳድሮች መምሪያ ኀላፊዎችንና እነዚህ ጋር ተመሳሳይ ስልጣን ያላቸውን ያካትታል፡፡የሕዝባዊ ድርጅትና የመንግሥት የልማት ድርጅት መስሪያ ቤት ላይም በተመሳሳይ መልኩ ተፈጸሚነት አለዉ፡፡

ሐ.ዝቅተኛ ሥልጣን፤- ማለት መካከለኛ የስልጣን ሀላፊነት በሚለው ውስጥ የማይካተቱ ዝቅተኛ ስራ መደብ ላይ የሚገኙ የመንግስት፣ የሕዝባዊ ድርጅትና የመንግሥት የልማት ድርጅት ሠራተኞችን ሥልጣን ማለት ነው፡፡

መ.በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 ከፊደል ሀ-ሐ የተመለከቱት የሥልጣን ደረጃ ትርጓሜዎች እንደተጠባቁ ሆኖ በአዲስ አበባ ከተማ፣ድሬዳዋ ከተማ እና በክልል የስነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽኖች ማቋቋሚያ አዋጆች ወይም አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች ውስጥ የተመለከቱ ትርጓሜዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

5. ጥቅም/ጉዳት፤- ግልጽ የሆነ ሌላ ተቃራኒ ህግ ከሌለ በስተቀር ጥቅም ወይም ጉዳት ማለት የተገኘን ወይም ሊገኝ የታሰበውን ጥቅም እንዲሁም የደረሰውን ወይም ሊደርስ የታሰበውን ጉዳት የሚያካትት ነው፡፡ በመሆኑም ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም፡-

ሀ.በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፤- ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር 4, 000,000.00 (አራት ሚሊዮን ብር) በላይ ሲሆን ነው፡፡

ለ.ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፤- ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር 1,000.001.00 (አንድ ሚሊዮን አንድ ብር) እስከ 4,000,000.00 ብር (አራት ሚሊዮን ብር) ሲሆን ነው፡፡

ሐ.መካከለኛ ጥቅም/ጉዳት፤- ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር 500,001.00 (አምስት መቶ ሺህ አንድ) እስከ ብር 1,000,000.00 (አንድ ሚሊዮን) ሲሆን ነው፡፡

መ.ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፤- ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት ከብር 100,001.00 (አንድ መቶ ሺህ አንድ ብር) እስከ ብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ) ሲሆን ነው፡፡

ሠ.በጣም ዝቅተኛ ጥቅም/ጉዳት፤- ማለት በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ጥቅም ወይም የደረሰው ጉዳት እስከ ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ) ሲሆን ነው፡፡

6. ከባድ ዓላማ፦ ማለት የፌዴራል ስነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ (በአዋጅ ቁጥር 433/97 ፣በአዋጅ ቁጥር 882/2007 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 2(9) እና በተሻሻለው የፌዴራል ስነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ( አዋጅ ቁጥር 883/2007) አንቀጽ 2(1)(ሀ) ላይ በተደነገገዉ መሰረት ጥቅም ወይም መብት ላይ የደረሰ ጉዳትን ለመመዘን ከፍተኛ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች፣የመንግሥት የልማት ድርጅቶች፣ ሕዝባዊ ድርጅቶች ላይ እና ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች የሚንቀሳቀሱ ሕዝባዊ ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም በሀገር ሉዓላዊነት፣ ኢኮኖሚ፣ ጸጥታ እንዲሁም በሕብረተሰቡ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ የሚችሉ የሙስና ወንጀሎች ሲሆኑ ነዉ፡፡

7. በተፈጸመው ወንጀል የተገኘው የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰውን ጉዳት በገንዘብ ገምቶ ለማስቀመጥ የማይቻል በሆነ ጊዜ ፍ/ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ምክንያቱን በማስቀመጥ የተገኘውን የገንዘብ ጥቅም ወይም የደረሰውን የጉዳት መጠን ደረጃ ይወስናል፡፡

8. በተፈጸመው ወንጀል የተገኘው ጥቅም እና የደረሰው ጉዳት የሚታወቅ ከሆነ ደረጃውን ለመወሰን ከሁለቱ የሚበልጠው ይወሰዳል፡፡

9. የመንግስት፣ የህዝባዊ ድርጅት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ሰራተኛ ያልሆነ ሰዉ በወ/ህ/አንቀጽ 33 መሰረት ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ ማንኛዉም ሰዉ የወንጀል ደረጃ እና የቅጣት እርከኑ የሚወሰነዉ የመንግስት፣ የህዝባዊ ድርጅት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ሰራተኛ ሆነዉ ሰዉ የወንጀል ደረጃ እና እርከን በተወሰነበት አግባብ ነዉ፡፡

99. አዋጅ ቁ. 881/2007 አንቀጽ 9(1)፣(2) እና (3) እና አንቀጽ 13(1)፣13(2) እና 13(3)

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀል ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| አንቀጽ 9(1) እና አንቀጽ 13(1) | 1 | 1. ዝቅተኛ ስልጣን እና የተገኘው ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበው ጥቅም/ጉዳት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ እስከ 20,000.00 ብር ከሆነ፤<br>ወይም<br>2. መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘው ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበው ጥቅም/ጉዳት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ እስከ 10,000.00 ብር ከሆነ ፡፡ | 10 | 1 |
| | 2 | 1. ዝቅተኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የተሰበው ጥቅም/ጉዳት ቅዝተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 20,001.00-50,000.00 ብር ከሆነ፤ ወይም<br>2. መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበዉ ጥቅም/ጉዳት በጣም ቅዝተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 10,001.00-30,000.00 ብር ከሆነ ፡፡ | 11 | 1 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 | 1. ዝቅተኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበዉ ጥቅም/ጉዳት ቅዝተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 50,001-100,000.00 ብር ከሆነ፤ ወይም<br>2. መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበዉ ጥቅም/ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 30,001-70,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 12 | 2 |
| 4 | 1. ዝቅተኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበዉ ጥቅም/ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 100,001-200,000.00 ብር ከሆነ ወይም<br>2. መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበዉ ጥቅም/ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 70,001-100,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 13 | 2 |
| 5 | 1. ዝቅተኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበዉ ጥቅም/ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 200,001-300,000.00 ብር ከሆነ፤ ወይም<br>2. መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበዉ ጥቅም/ጉዳት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 100,001-200,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 15 | 3 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 6 | 1. ዝቅተኛ ስልጣን እና የተገኘው ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበው ጥቅም/ጉዳት መካከለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 300,001-400,000.00 ብር ከሆነ፤ ወይም<br>2. መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘው ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበዉ ጥቅም/ጉዳት በጣም ቅዝተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 200,001-300,000.00 ብር ከሆነ ፡፡ | 17 | 3 |
| | 7 | 1. ዝቅተኛ ስልጣን እና የተገኘው ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበዉ ጥቅም/ጉዳት መካከለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 400,001-500,000.00 ብር ከሆነ፤ ወይም<br>2. .መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ወይም ልገኝ/ልደርስ የተሰበው ጥቅም/ጉዳት መከካለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 300,001-400,000.00 ብር ከሆነ ፡፡ | 19 | 4 |
| | 8 | 1. ዝቅተኛ ስልጣን እና የተገኘው ወይም ልገኝ/ልደርስ የተሰበው ጥቅም/ጉዳት መካከለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 500,001-600,000.00 ብር ከሆነ፤ ወይም<br>2. መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘው ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበው ጥቅም/ጉዳት መከካለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 400,001-500,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 21 | 4 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 9 | 1. ዝቅተኛ ስልጣን እና የተገኘው ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበዉ ጥቅም/ጉዳት መካከለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 600,001-700,000.00 ብር ከሆነ ወይም<br>2. መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘው ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበዉ ጥቅም/ጉዳት መከካለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 500,001-600,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 23 | 5 |
| | 10 | 1. ዝቅተኛ ስልጣን እና የተገኘው ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበው ጥቅም/ጉዳት መካከለኛ ሆኖ ገንዘቡ ብር 700,001-800,000.00 ከሆነ ወይም<br>2. መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበዉ ጥቅም/ጉዳት መከካለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 600,001-700,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 25 | 5 |
| | 11 | መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘው ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበዉ ጥቅም/ጉዳት መከካለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 800,001-900,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 27 | 5 |
| | 12 | 1. ዝቅተኛ ስልጣን እና የተገኘው ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበው ጥቅም/ጉዳት መካከለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 900,001-1,000,000.00 ብር ከሆነ፤ ወይም | 28 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 2. መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘው ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበዉ ጥቅም/ጉዳት መከካለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 800,001-900,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | | |
| | 13 | መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘው ወይም ሊገኝ/ሊደርስ የታሰበው ጥቅም/ጉዳት መከካለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 900,001-1,000,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 30 | |
| አንቀጽ 9(2) እና አንቀጽ 13(2) | 1 | 1. ከፍተኛ ስልጣን እና የተገኘው ጥቅም/የደረሰው ጉዳት በጣም ዝቅተኛ ወይም<br>2. ከባድ ዓላማና የተገኘው ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት በጣም ዝቅተኛ ወይም<br>3. ዝቅተኛ ስልጣን እና የተገኘው ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት በጣም ከፍተኛ ወይም<br>4. መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ከፍተኛ ከሆነ፡፡ | 28 | 6 |
| | 2 | 1. ከፍተኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ዝቅተኛ ወይም<br>2. ከባድ ዓላማና የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ዝቅተኛ ወይም<br>3. መከካለኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ከፍተኛ ከሆነ፡፡ | 29 | 7 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3 | 1. ከፍተኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ጥቅም/ የደረሰዉ ጉዳት መካከለኛ ወይም<br>2. ከባድ ዓላማና የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት መካከለኛ ወይም<br>3. መከካለኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት በጣም ከፍተኛ ከሆነ፡፡ | 30 | 8 |
| | 4 | 1. ከፍተኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ጥቅም/ የደረሰዉ ጉዳት ከፍተኛ ወይም<br>2. ከባድ ዓላማና የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ከፍተኛ ከሆነ፡፡ | 32 | 9 |
| | 5 | ከፍተኛ ስልጣን፡ከባድ ዓላማ እና የተገኘዉ ጥቅም/ ያደረሰዉ ጉዳት በጣም ከፍተኛ ከሆነ፡፡ | 36 | 11 |
| አንቀጽ 9(3) እና አንቀጽ 13(3) | 1 | ከፍተኛ ስልጣን/ከባድ ዓላማ እና ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም ወይም የደረሰዉ ጉዳት ከ 1,000,001 - 2,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 33 | 7 |
| | 2 | 1. ከፍተኛ ስልጣን እና ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት ሆኖ ከ 2,000,001 - 3,000,000 ብር ወይም | 35 | 8 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 2. ከባድ ዓላማና ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም ወይም የደረሰዉ ጉዳት ከ 2,000,001 - 3,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | | |
| | 3 | 1. ከፍተኛ ስልጣን እና ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት ሆኖ ከ 3,000,001- 4,000,000 ብር ወይም<br>2. ከባድ ዓላማና ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም ወይም የደረሰዉ ጉዳት ከ 3,000,001- 4,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 37 | 9 |
| | 4 | 1. ከፍተኛ ስልጣን እና በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት ወይም<br>2. ከባድ ዓላማና በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት፡፡ | 40 | 12 |
| | 5 | ከፍተኛ ስልጣን፣ በጣም ከፍተኛ ጥቅም/ጉዳት እና ከባድ ዓላማ፡፡ | 42 | 13 |

**100. *መንግስታዊ ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰተኛነት በመለወጥ ወይም በሀሰተኛ ሰነድ መገልገል ( አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23)***

1. *አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 በመተላለፍ ሐሰተኛ ሠነዶችን በመፍጠር፣ ወደ ሐሰተኛነት በመለወጥና በማጥፋት በሚፈፀሙ ወንጀሎች ክስ ቀርቦባቸው ጥፋተኛነታቸው በፍ/ቤት በሚረጋገጥባቸው ተከሳሾች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው::*

2. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23(1)(ሀ-ሐ)እና (3) የተመለከተው በግዙፍ የሚፈፀም ሐሰት የወንጀል ድርጊቱ ሊፈፀም የሚችልበትን ሁኔታዎች እና በወንጀል ድርጊቱ የሚገኘው ጥቅም ወይም የሚደርሰው ጉዳት፤ድርጊቱ የተፈፀመበትን የሠነድ አይነትና ባህሪ፤ እንዲሁም የድርጊቱን ፈፃሚ ማንነት ታሣቢ በማድረግ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው ድረስ ድንጋጌዎቹን በማጣመር በአጠቃላይ 12 የወንጀል ደረጃዎች ተጋጅተዋል።

3. አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23(2) የተመለከተው በሀሰተኛ ሠነድ መገልገል የወንጀል ድርጊቱ ሲፈፀም የሚችልበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም ከወንጀል ድርጊቱ የሚገኘውን የጥቅም ወይም የሚደርሰውን የጉዳት መጠን ድርጊቱ የሚፈፀምበትን የሠነድ አይነትና ባህሪ እና የፈፃሚውን ማንነት መሠረት በማድረግ በአጠቃላይ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው 7 የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀል ደረጃ | የወንጀል ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የመቀጮ ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| አንቀጽ 23 (1) እና (3) | 1 | 1. አንድ ፅሑፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ እና ምንም ጥቅም ያላገኘ ወይም ጉዳት ያልደረሰ ከሆነ፤ወይም<br>2. በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ፣ ጽሑፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛውን ጽሑፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት | 16 | 1 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ስልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ ያዘጋጀ እንደሆነ፤ ወይም የፈጠረ እንደሆነ እና ምንም ጥቅም ያላገኘ ወይም ጉዳት ያልደረሰ ከሆነ፤ ወይም<br>3. አንድን የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነድ በተለይም የፈራሚውን ስም ወይም ፊርማ ወይም የሰነዱን ይዘት፣ አሃዝ፣ ፍሬ ነገር ወይም ዝርዝር መግለጫ በሙሉ ወይም በከፊል በመለወጥ፣ በማሻሻል፣ በመቀነስ ወይም በመጨመር ወይም በማጥፋት ወደ ሐሰተኛነት የለወጠ ወይም ማናቸውንም ሐሰተኛ ፍሬ ነገር ያስገባ ወይም እንዲገባ ያደረገ እንደሆነ እና ምንም ጥቅም ያላገኘ ወይም ያደረሰዉ ጉዳት የሌለ ከሆነ፡፡ | | |
| | 2 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ የተገኘዉ/ልገኝ የተሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት በጣም አነስተኛ ከሆነ ወይም ተገለግሎ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ እስከ ብር 75,000.00 ከሆነ፡፡ | 17 | 1 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ የተገኘዉ/ሊገኝ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት በጣም አነስተኛ ከሆነ ወይም ተገለግሎ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 75,001-100,000 ብር ከሆነ ፡፡ | 18 | 2 |
| | 4 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ የተገኘዉ/ሊገኝ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት በጣም አነስተኛ ከሆነ ወይም ተገለግሎ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 100,001.00 - 200,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 20 | 2 |
| | 5 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ የተገኘዉ/ሊገኝ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የተሰበዉ ጉዳት በጣም አነስተኛ ከሆነ ወይም ተገለግሎ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 200,001 - 300,000 ብር ከሆነ፡ | 22 | 3 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 6 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ የተገኘዉ/ሊገኝ የተሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት በጣም አነስተኛ ከሆነ ወይም ተገለግሎ የተሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 300,001-400,000 ብር ከሆነ፡፡ | 24 | 3 |
| | 7 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ የተገኘዉ/ሊገኝ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት በጣም አነስተኛ ከሆነ ወይም ተገለግሎ የተሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 400,001 - 500,000 ብር ከሆነ፡፡ | 25 | 4 |
| | 8 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ የተገኘዉ/ሊገኝ የተሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት በጣም አነስተኛ ከሆነ ወይም ተገለግሎ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት መካከለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 500,001-600,000 ብር ከሆነ፡፡ | 26 | 4 |
| | 9 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ የተገኘዉ/ሊገኝ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት በጣም አነስተኛ ከሆነ ወይም ተገለግሎ የታሰበዉ ጥቅም | 27 | 5 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት መካከላኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ600,001-700,000 ብር ከሆነ፡፡ | | |
| | 10 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ የተገኘዉ/ሊገኝ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት በጣም አነስተኛ ከሆነ ወይም ተገለግሎ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለው/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት መካከላኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ700,001- 800,000 ብር ከሆነ፡፡ | 28 | 5 |
| | 11 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ የተገኘዉ/ሊገኝ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት በጣም አነስተኛ ከሆነ ወይም ተገለግሎ የተሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለው/ሊያስከትል የታሰበው ጉዳት መካከላኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ800,001-900,000 ብር ከሆነ፡፡ | 29 | 6 |
| | 12 | ድርጊቱ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ የተገኘዉ/ሊገኝ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊስከትል የታሰበዉ ጉዳት በጣም አነስተኛ ከሆነ ወይም ተገለግሎ የታሰበዉ ጥቅም ወይም ያስከተለዉ/ሊያስከትል የታሰበዉ ጉዳት መካከለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 900,001-1000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 30 | 6 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 23(2)(ሀ) እና 23(3) | 1 | 1.ከላይ ለአንቀጽ 23(1) እና (3) እንደተገለፀው በደረጃ-1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ ወንጀሉ የተፈጸመው እነዚህን የመሳሰሉትን መዝገቦች፥ ጽሑፎች፣ የታወቁ ሰነዶች ወይም ሌሎች ሰነዶችን እንዲያዘጋጅ፣ እንዲመዘግብ፣ እንዲጠብቅ ወይም ከነዚሁ ውስጥ ቅጅዎችን እንዲሰጥ ኃላፊነት በተሰጠው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ከሆነ እና ምንም ጥቅም ካልገኘ ወይም ጉዳት ካልደረሰ ወይም<br><br>2.ማንኛዉም ሰዉ ሆኖ ሰነዱን በመገልገል የተገኘዉ ጥቅም ከፍተኛ ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ1,000,000-2,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 23 | 4 |
| | 2 | 1.ከላይ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ ወንጀሉ የተፈጸመው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ከሆነ እና ያገኘዉ ጥቅም ወይም የደረሰዉ ጉዳት በጣም አነስተኛ ሆኖ ገንዘቡ እስከ 50,000.00 ብር ከሆነ ወይም<br><br>2.ማንኛዉም ሰዉ ሆኖ ሰነዱን በመገልገል የተገኘዉ ጥቅም ከፍተኛ ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 2,000,001-3,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 28 | 5 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3 | 1.ከላይ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ ወንጀሉ የተፈጸመው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ከሆነ እና ያገኘዉ ጥቅም ወይም የደረሰዉ ጉዳት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ50,001-100,000 ብር ከሆነ ወይም<br><br>2.ማንኛዉም ሰዉ ሆኖ ሰነዱን በመገልገል የተገኘዉ ጥቅም ከፍተኛ ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 3,000,001-4,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 32 | 5 |
| | 4 | 1.ከላይ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ ወንጀሉ የተፈጸመው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ከሆነ እና የተገኘዉ ጥቅም ወይም የደረሰዉ ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 100,001-300,000 ብር ከሆነ ወይም<br><br>2.ማንኛዉም ሰዉ ሆኖ ሰነዱን በመገልገል የተገኘዉ ጥቅም ከፍተኛ ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ 4,000,001-5,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 36 | |
| | 5 | 1.ከላይ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ ወንጀሉ የተፈጸመው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ከሆነ እና የተገኘዉ ጥቅም ወይም የደረሰዉ ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ3,000,001-500,000 ብር ከሆነ ወይም | 38 | 5 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 2.ማንኛዉም ሰዉ ሆኖ ሰነዱን በመገልገል የተገኘዉ ጥቅም ከፍተኛ ወይም በግለሰብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት በጣም ከፍተኛ ከሆነ፡፡ | | |
| | 6 | 1.ከላይ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ ወንጀሉ የተፈጸመው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ከሆነ እና ያገኘው ጥቅም ወይም የደረሰዉ ጉዳት መከካለኛ ሆኖ ገንዘቡ ከ500,001-1,000,000 ብር ከሆነ፡፡ | 40 | 6 |
| | 7 | 1.ከላይ በደረጃ 1 ላይ የተመለከተዉ ሆኖ ወንጀሉ የተፈጸመው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ከሆነ እና የተገኘዉ ጥቅም ወይም የደረሰዉ ጉዳት ከፍተኛ ከሆነ፡፡ | 42 | 6 |
| 23(2)(ለ) | | ለአንቀጽ 9(3) እና 13(3) የወጡት ደረጃዎች ለአንቀጽ 23(2)(ለ) ተፈጸሚነት ይኖራቸዋል፡፡ | | 6 |

**101. ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት (አዋጅ ቁጥር 881/2007፣ አንቀጽ 25)**

1. አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 25 በመተላለፍ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ከስ ቀርቦባቸው ጥፋተኛነታቸው በፍ/ቤት በሚረጋገጠባቸው ተከሰሾች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው::

2. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 25(1)፣(2) እና (3) የተመለከተው የወንጀል ድርጊቱ ሊፈፀም የሚችልበትን ሁኔታዎች እና በወንጀል ድርጊቱ የሚገኘው ጥቅም ወይም የሚደርሰው ጉዳት፤ድርጊቱ የተፈፀመበትን ዓለማ፤ እንዲሁም የድርጊቱን ፈፃሚ ማንነት ታሣቢ በማድረግ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው ድረስ በአጠቃላይ 7 የወንጀል ደረጃዎች ተጋጅተዋል።

3. አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 25(4) የተመለከተው የወንጀል ድርጊቱ ሲፈፀም የሚችልበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም ከወንጀል ድርጊቱ የሚገኘውን የጥቅም ወይም የሚደርሰውን የጉዳት መጠን ድርጊት መሠረት በማድረግ በአጠቃላይ ከዝቅተኛው አስከ ከፍተኛው 7 የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

| የወንጀል ህግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የመቀጮ ቅጣት መነሻ እርካን |
|---|---|---|---|---|
| አንቀጽ 25(1)፣(2) እና (3) | 1 | ማንኛዉም ሰዉ በአንቀጽ 25(1)(2) እና (3) ስር በመተላላፍ ወንጀል ከፈጸመ እና ጥቅሙ በጣም ዝቅተኛ ከሆነ፡፡ | 10 | 1 |
| | 2 | ደረጃ 1 ስር ለተጠቀሱት ሰዎች የተሰጠዉ/የቀረበዉ ጥቅም፣ጉቦ ወይም ስጦታ ዝቅተኛ ሆኖ ብሩ ከ100,001-250,000 ብር ከሆነ፡፡ | 14 | 2 |
| | 3 | ደረጃ 1 ስር ለተጠቀሱት ሰዎች የተሰጠዉ/የቀረበዉ ጥቅም፣ጉቦ ወይም ስጦታ ዝቅተኛ ሆኖ ብሩ ከ250,001-500,000 ከሆነ፡፡ | 16 | 3 |
| | 4 | ደረጃ 1 ስር ለተጠቀሱት ሰዎች የተሰጠዉ/የቀረበዉ ጥቅም፣ጉቦ ወይም ስጦታ | 20 | 4 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | መካከለኛ ሆኖ ከ 500,001-600,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | | |
| | 5 | ደረጃ 1 ስር ለተጠቀሱት ሰዎች የተሰጠዉ/የቀረበዉ ጥቅም፣ጉቦ ወይም ስጦታ አነስተኛ ሆኖ ከ 600,001-700,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 22 | 5 |
| | 6 | ደረጃ 1 ስር ለተጠቀሱት ሰዎች የተሰጠዉ/የቀረበዉ ጥቅም፣ጉቦ ወይም ስጦታ አነስተኛ ሆኖ ብሩ 700,001-800,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 24 | 6 |
| | 7 | ደረጃ 1 ስር ለተጠቀሱት ሰዎች የተሰጠዉ/የቀረበዉ ጥቅም፣ጉቦ ወይም ስጦታ አነስተኛ ሆኖ ከ 800,001.00-1000,000.00 ብር ከሆነ ፡፡ | 26 | 7 |
| አንቀጽ 25(4) | 1 | 1.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) ወይም (3) ስር ለተመለከተው ወንጀል አድራጊው ያቀረበው ገንዘብ ከፍተኛ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም ከ1,000,001-2,000,000 ከሆነ ወይም<br>2.ድርጊቱ በግለሰብ፣ በህዝብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳትን ያስከተለ ሆኖ የጉዳቱ መጠን ከ 1,000,001-2,000,000 ከሆነ ወይም | 23 | 5 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 3) ጥቅም እና ጉዳት አንድ ላይ የተሟላ ሆኖ ያቀረበው ገንዘብ ከፍተኛ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም ከ 1,000,001-1,500,000 ከሆነ እና የጉዳቱ መጠን ከ 1,000,001-1,500,000 ከሆነ፡፡ | | |
| | 2 | 1.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) ወይም (3) ስር ለተመለከተው ወንጀል አድራጊው ያቀረበው ገንዘብ ከፍተኛ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም ከ 2,000,001-3,000,000 ከሆነ ወይም<br><br>2.ድርጊቱ በግለሰብ፣ በህዝብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳትን ያስከተለ ሆኖ የጉዳቱ መጠን ከ 2,000,001-3,000,000.00 ብር ከሆነ ወይም<br><br>3. ጥቅም እና ጉዳት አንድ ላይ የተሟላ ሆኖ ያቀረበው ገንዘብ ከፍተኛ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም ከ 1,500,001-2,000,000.00 ብር ከሆነ እና የጉዳቱ መጠን ከ 1,500,001-2,000,000.00 ከሆነ፡፡ | 25 | 6 |
| | 3 | 1.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) ወይም (3) ስር ለተመለከተው ወንጀል አድራጊው ያቀረበው ገንዘብ ከፍተኛ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም ከ 3,000,001.00-4,000,000.00 ብር ከሆነ ወይም<br><br>2.ድርጊቱ በግለሰብ፣ በህዝብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ ከፍተኛ | 27 | 7 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ጉዳትን ያስከተለ ሆኖ የጉዳቱ መጠን ከ 3,000,001.00 - 4,000,000.00 ብር ከሆነ ወይም<br><br>3.ጥቅም እና ጉዳት አንድ ላይ የተሟላ ሆኖ ያቀረበው ገንዘብ ከፍተኛ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም ከ 2,000,001-2,500,000.00 ብር ከሆነ እና የጉዳቱ መጠን ከ 2,000,001-2,500,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | | |
| | 4 | 1.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) ወይም (3) ስር ለተመለከተው ወንጀል አድራጊው ያቀረበው ገንዘብ ከፍተኛ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም ከ 4,000,001- 5,000,000 ከሆነ ወይም<br><br>2.ድርጊቱ በግለሰብ፣ በህዝብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳትን ያስከተለ ሆኖ የጉዳቱ መጠን ከ 4,000,001-5,000,000.00 ብር ከሆነ<br><br>3. ጥቅም እና ጉዳት አንድ ላይ የተሟላ ሆኖ ያቀረበው ገንዘብ ከፍተኛ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም ከ 2,500,001-3,000,000.00 ከሆነ እና የጉዳቱ መጠን ከ 2,500,001-3,000,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 30 | 8 |
| | 5 | 1.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) ወይም (3) ስር ለተመለከተው ወንጀል አድራጊው ያቀረበው ገንዘብ በጣም ከፍተኛ ከሆነ ወይም | 32 | 9 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 2.ድርጊቱ በግለሰብ፣ በህዝብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ በጣም ከፍተኛ ጉዳትን ያስከተለ ከሆነ ወይም<br><br>3. ጥቅም እና ጉዳት አንድ ላይ የተሟላ ሆኖ ያቀረበው ገንዘብ ከፍተኛ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም ከ 3,000,001-4,000,000.00 ከሆነ እና የጉዳቱ መጠን ከ 3,000,001-4,000,000.00 ከሆነ፡፡ | | |
| 6 | 1.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) ወይም (3) ስር ለተመለከተው ወንጀል አድራጊው ያቀረበው ገንዘብ በጣም ከፍተኛ ከሆነ እና<br><br>2.ድርጊቱ በግለሰብ፣ በህዝብ፣ በመንግስት፣ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ጥቅም ላይ በጣም ከፍተኛ ጉዳትን ያስከተለ ከሆነ፡፡ | 34 | 10 |
| 7 | የቀረበዉ ጥቅም እና ጉዳት አንድ ላይ የተሟላ ሆኖ ያቀረበው ገንዘብ እና የደረሰዉ ጉዳት በጣም ከፍተኛ ከሆነ፡፡ | 35 | 11 |

## 102. ከባድ አታላይነት ( አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32)

1. አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32 በመተላለፍ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ክስ ቀርቦባቸው ጥፋተኛነታቸው በፍ/ቤት በሚረጋገጠባቸው ተከሰሾች ላይ ቅጣት የሚወሰነው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ነው::

2. በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32(1) እና (3) የተመለከተው የወንጀል ድርጊቱ ሊፈፀም የሚችልበትን ሁኔታዎች እና በወንጀል ድርጊቱ የሚገኘው ጥቅም ወይም የሚደርሰው

ጉዳት፤ድርጊቱ የተፈፀመበትን ዓላማ፤ እንዲሁም የድርጊቱን ፈፃሚ ማንነት ታሣቢ በማድረግ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው ድረስ በአጠቃላይ 11 የወንጀል ደረጃዎች ተጋጅቷል።

3. አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32(2) የተመለከተው የወንጀል ድርጊቱ ሊፈፀም የሚችልበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም ከወንጀል ድርጊቱ የሚገኘውን የጥቅም ወይም የሚደርሰውን የጉዳት መጠን ድርጊት መሠረት በማድረግ በአጠቃላይ ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው 5 የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

| የወንጀል ህጉ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የመቀጮ ቅጣት መነሻ እርካን |
|---|---|---|---|---|
| አንቀጽ 32(1) እና (3) | 1 | ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በንዑስ 1 ስር የተጠቀሰዉ ወንጀል ድርጊት በመፈጸም በጣም ዝቅተኛ ጥቅም ካገኘ/ለሌላ ሰዉ ካስገኘ ወይም በሌላ ሰዉ ላይ በጣም ዝቅተኛ ጉዳት ካደረሰ እና የጥቅሙ ወይም ጉዳቱ መጠን እስከ 50,000 ብር ከሆነ ፡፡ | 16 | 3 |
| | 2 | ወንጀሉ በደረጃ አንድ ስር በተገለጸዉ መሰረት የተፈጸመ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት በጣም ዝቅተኛ ሆኖ | 17 | 3 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የገንዘቡ መጠን ከ 50,001-100,000 ብር ከሆነ ፡፡ | | |
| | 3 | ወንጀሉ በደረጃ አንድ ስር በተገለጸዉ መሰረት የተፈጸመ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከ 100,001-200,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 18 | 3 |
| | 4 | ወንጀሉ በደረጃ አንድ ስር በተገለጸዉ መሰረት የተፈጸመ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከ 200,001-300,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 19 | 4 |
| | 5 | ወንጀሉ በደረጃ አንድ ስር በተገለጸዉ መሰረት የተፈጸመ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከ 200,001-300,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 20 | 4 |
| | 6 | ወንጀሉ በደረጃ አንድ ስር በተገለጸዉ መሰረት የተፈጸመ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከ 300,001- 400,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 21 | 4 |
| | 7 | ወንጀሉ በደረጃ አንድ ስር በተገለጸዉ መሰረት የተፈጸመ ሆኖ የተገኘዉ | 23 | 5 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከ 400,001-500,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | | |
| | 8 | ወንጀሉ በደረጃ አንድ ስር በተገለጸዉ መሰረት የተፈጸመ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ዝቅተኛ ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከ 400,001-500,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 24 | 5 |
| | 9 | ወንጀሉ በደረጃ አንድ ስር በተገለጸዉ መሰረት የተፈጸመ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት መካከለኛ ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከ 500,001.00-600,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 25 | 6 |
| | 10 | ወንጀሉ በደረጃ አንድ ስር በተገለጸዉ መሰረት የተፈጸመ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት መካከለኛ ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከ 600,001-800,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 27 | 7 |
| | 11 | ወንጀሉ በደረጃ አንድ ስር በተገለጸዉ መሰረት የተፈጸመ ሆኖ የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት መካከለኛ ሆኖ የገንዘቡ መጠን ከ 800,001-1000,000.00 ብር ከሆነ፡፡ | 30 | 7 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አንቀጽ 32(2) እና 32(3) | 1 | 1.ከፍተኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት በጣም ዝቅተኛ ወይም<br><br>2. ዝቅተኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ጥቅም/ የደረሰዉ ጉዳት ከፍተኛ ወይም<br><br>3. መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ከፍተኛ ከሆነ | 23 | 3 |
| | 2 | 1.ከፍተኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ዝቅተኛ ወይም<br><br>2. ዝቅተኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ጥቅም/ የደረሰዉ ጉዳት በጣም ከፍተኛ ከሆነ፡፡ | 27 | 3 |
| | 3 | 1.ከፍተኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት መካከለኛ ወይም<br><br>2.መካከለኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት በጣም ከፍተኛ ከሆነ ፡፡ | 30 | 3 |
| | 4 | 1.ከፍተኛ ስልጣን እና የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት ከፍተኛ ከሆነ፡፡ | 33 | 6 |
| | 5 | ከፍተኛ ስልጣንና የተገኘዉ ጥቅም/የደረሰዉ ጉዳት በጣም ከፍተኛ ከሆነ | 35 | 7 |

## <u>ርዕስ አስራ ሁለት</u>

## <u>የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ( አዋጅ ቁጥር 983/2008)</u>

### 103. ጠቅላላ

1. የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ( አዋጅ ቁጥር 983/2008) አንቀጽ 120(1) ከደረሰኝ ጋር የተገናኙ ጠቅላላ ወንጀሎች፣ አንቀጽ 128 ያለ ደረሰኝ ግብይትን መርዳት ወይም ማበረታታት እና አንቀጽ 131(1)(ለ) ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች ጋር በተገናኘ ያለ ደረሰኝ ግብይት በመፈፀም ጥፋተኛ በተባሉ ሰዎች ላይ ቅጣት የሚጣለው በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

2. ወንጀሉ አፈፃፀም ለተፈጸመ ግብይት ደረሰኝ ባለመቁረጥ የመንግስትን ገቢ ማሳጣት እና ለራስ ያልተገባ ገቢ ለማግኘት በመሆኑ ፣ ግብይቱ የተፈጸመበት የገንዘብ መጠን ለወንጀሉ ደረጃ ለማውጣት እንደ መስፈርት ተወስዷል፡፡

3. ለዚህ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አፈጻጸም ሲባል ከላይ ለተጠቀሱት ድንጋጌዎች በአዋጁ አንቀጽ 2(36) ስር የታክስ ህግ በማለት የተደነገገዉን ይይዛል፡፡

### 104. ያለ ደረሰኝ ግብይት መፈጸም

| የአዋጁ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ<br>(በኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| አንቀጽ 120/1 ፣128፣132/1 | 1 | ግብይት የተፈጸመበት ዕቃ ዋጋ እስከ 10,000.00 ከሆነ፡፡ | 16 | 7 |
| | 2 | ግብይት የተፈጸመበት ዕቃ ዋጋ ከ10,001.00 እስከ 50,000.00 ከሆነ፡፡ | 17 | 7 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3 | ግብይት የተፈጸመበት ዕቃ ዋጋ ከ50,001.00 እስከ 100,000.00 ከሆነ፡፡ | 18 | 8 |
| | 4 | ግብይት የተፈጸመበት ዕቃ ዋጋ ከ100,001.00 እስከ 300,000.00 ሲሆን ከሆነ፡፡ | 19 | 8 |
| | 5 | ግብይት የተፈጸመበት ዕቃ ዋጋ ከ300,001.00 እስከ 500,000.00 ከሆነ፡፡ | 20 | 9 |
| | 6 | ግብይት የተፈጸመበት ዕቃ ዋጋ ከ500,001.00 በላይ ከሆነ፡፡ | 21 | 9 |
| አንቀጽ 131(1)(ለ) እና 128፣ 132/1 | 1 | ግብይት የተፈጸመበት ዕቃ ዋጋ እስከ 7,000.00 ከሆነ | 12 | - |
| | 2 | ግብይት የተፈጸመበት ዕቃ ዋጋ ከ7,001.00 እስከ 45,000.00 ከሆነ፡፡ | 14 | - |
| | 3 | ግብይት የተፈጸመበት ዕቃ ዋጋ ከ45,001.00 እስከ 90,000.00 ከሆነ፡፡ | 16 | - |
| | 4 | ግብይት የተፈጸመበት ዕቃ ዋጋ ከ90,001.00 እስከ 150,000.00 ከሆነ፡፡ | 18 | - |
| | 5 | ግብይት የተፈጸመበት ዕቃ ዋጋ ከ150,001.00 እስከ 300,000.00 ከሆነ፡፡ | 20 | - |
| | 6 | ግብይት የተፈጸመበት ዕቃ ዋጋ ከ300,000.00 በላይ ከሆነ | 21 | - |

# ርዕስ አስራ ሶስት

## የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር (አዋጅ ቁጥር 859/2006) እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2011

**105. ጠቅላላ**

1. የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር (አዋጅ ቁጥር 859/2006) እና የዚህ ሕግ ማሻሻያ (አዋጅ ቁጥር 1160/2011) በመተላለፍ የጉምሩክ ሥነ- ሥርዓት ያልተፈጸመባቸዉ እና ገደብ ተደርጎባቸዉ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ የተከለከሉ ዕቃዎችን ወደ ሀገር በማስገባት ወይም ከሀገር በማስወጣት ጥፋተኛ በሆኑ ሰዎች ላይ ቅጣት የሚወሰነው በዚህ መመሪያ መሰረት ነው፡፡
2. የድርጊቱ አፈፃፀም መንግስትን ገቢ በማሳጣት እና ለራስ ያልተገባ ገቢ ማግኘት በመሆኑ ይኸው የገንዘብ መጠን ለወንጀሉ ደረጃ ለማውጣት እንደ መስፈርት ተወስዷል፡፡
3. የመመሪያው ደረጃ አወጣጥ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 168(1)-(3) እና የዚህ ሕግ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2011 አንቀጽ 44 (1) መሰረት ነው፡፡

**106. ኮንትሮባንድ**

| የአዋጁ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ (በኢትዮጵያ ብር) | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 168/1 እንደተሻሻለዉ 44/1 | 1 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን እስከ 300,000.00 ከሆነ፡፡ | 23 | 9 |
| | 2 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት | 24 | 9 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዕቃ የታክስ መጠን ከ 300,001.00 እስከ 500,000.00 ከሆነ፡፡ | | |
| | 3 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 500,001.00 እስከ 800,000.00 ከሆነ፡፡ | 25 | 10 |
| | 4 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 800,001.00 እስከ 1,500,000.00 ከሆነ፡፡ | 26 | 11 |
| | 5 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 1,500,001.00 እስከ 2,500,000.00 ከሆነ፡፡ | 27 | 11 |
| | 6 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 2,500,001.00 እስከ 5,000,000.00 ከሆነ፡፡ | 28 | 12 |
| | 7 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 5,000,001.00 እስከ 7,000,000.00 ከሆነ፡፡ | 29 | 13 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 8 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 7,000,001.00 እስከ 10,000,000.00 ከሆነ፡፡ | 30 | 13 |
| | 9 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 10,000,001.00 በላይ ከሆነ፡፡ | 31 | 14 |
| 168/2 | 1 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን እስከ 400,000.00 ከሆነ፡፡ | 16 | 9 |
| | 2 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 400,001.00 እስከ 800,000.00 ከሆነ፡፡ | 17 | 9 |
| | 3 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 800,001.00 እስከ 1,200,000.00 ከሆነ፡፡ | 18 | 10 |
| | 4 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት | 19 | 10 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ዕቃ የታክስ መጠን ከ1,200,001.00 እስከ 2,000,000.00 ከሆነ፡፡ | | |
| | 5 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 2,000,001.00 እስከ 4,000,000.00 ከሆነ፡፡ | 20 | 11 |
| | 6 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 4,000,001.00 በላይ ከሆነ፡፡ | 21 | 11 |
| 168/3 | 1 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን እስከ 300,000.00 ከሆነ፡፡ | 31 | 9 |
| | 2 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 300,001.00 እስከ 500,000.00 ከሆነ፡፡ | 32 | 10 |
| | 3 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 500,001.00 እስከ 1,000,000.00 ከሆነ፡፡ | 33 | 11 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 4 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 1,000,001.00 እስከ 2,000,000.00 ከሆነ፡፡ | 34 | 12 |
| | 5 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 2,000,001.00 እስከ 5,000,000.00 ከሆነ፡፡ | 35 | 13 |
| | 6 | የተከለከለ፣ ገደብ የተደረገበት ወይም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ያልተፈጸመበት ዕቃ የታክስ መጠን ከ 5,000,001.00 በላይ ከሆነ፡፡ | 36 | 14 |

## ርዕስ አስራ አራት

## የጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1177/2012)

### 107. ጠቅላላ

1. የጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1177/2012) አንቀጽ 22(2)፣ 22(3)፣ 22(5) በመተላለፍ ጥፋተኛ በተባሉ ተከሳሾች ላይ ቅጣት የሚወሰነው በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

2. የጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1177/2012) የወንጀል ድንጋጌዎች ደረጃ ለማውጣት የጦር መሳርያውን አደገኝነት እንዲሁም ብዛት መሰረት በማድረግ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ በአጠቃላይ አምስት የወንጀል ደረጃዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

3. የሕግ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች ጥፋተኛ ሆነው በሚገኙበት ጊዜ የሚጣለው የገንዘብ መቀጮ የአዋጁን አንቀፅ 22(11) መሰረት በማድረግ ፣ ለእያንዳንዱ የወንጀል ደረጃ ተጓዳኝ የገንዘብ መቀጮ እርከን ተለይቷል፡፡

4. እነኝህን ወንጀሎች በተመለከተ በአቃቤ ሕግ የሚቀርብ የወንጀል ክስ ማመልከቻ፣ የክስ ምክንያት የሆነውን የጦር መሳሪያ ዓይነት፣ ብዛት እና በቅጣት አወሳሰን መመሪያ የተገለፁ ሌሎች መስፈርቶችን በግልፅ ማሳየት አለበት፡፡

5. በዚህ መመሪያ ክፍል ደረጃ የወጣላቸው ወንጀሎች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 481 ውስጥ የማይካተቱ በጦር መሳሪያ ከመነገድ ዓላማ ውጭ የተፈፀሙ ወንጀሎች ናቸው፡፡

6. በዚህ መመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር፣ የጦር መሳሪያ አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1177/2012)፣ "የጦር መሳሪያ"፣ "ተያያዥነት ያላቸው አባሪዎች"፣ "ጥይት" ፣ "ቀላል የጦር መሳሪያ"፣"አውቶማቲክ ያልሆነ የጦር መሳሪያ" ፣ "በከፊል አውቶማቲክ የጦር መሳሪያ"፣ "ሙሉ አውቶማቲክ ጠመንጃ"፣ "ብዛት ያለው መሳሪያ" የሚሉት ቃላት/ሃረጋት ውስጥ የተሰጣቸው ትርጉም በዚህ መመሪያም ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

7. አዋጁ አንቀፅ አንቀፅ 2(10) "ብዛት ያለው የጦር መሳሪያ" ለሚለው ሃረግ የተሰጠው ትርጓሜ ቢኖርም፣ ለዚህ መመሪያ አተገባበር አንድ ቀላል የጦር መሳሪያ እና አውቶማቲክ ያልሆነ የጦር መሳሪያ ከ ፋብሪካ በተሰራለት ካርታ መሰረት መያዝ እስከሚችለው ድረስ ብዛት ያላቸው መሰል ጥይቶች ጋር እንደ "ብዛት ያለው የጦር መሳሪያ" አይቆጠርም፡፡

8. ከላይ በንኡስ አንቀጽ 7 የተመለከተው ዓይነት ወንጀሎች ባጋጠሙ ጊዜ፣ በዚህ መመሪያ ለ አዋጁ አንቀጽ 22(2) በተዘጋጀው ደረጃ መሰረት የጦር መሳሪያው ከሚያርፍበት መነሻ የቅጣት እርከን ላይ አንድ እርከን በማሳደግ መነሻ ቅጣት ይወሰናል፡፡

9. ከአንቀፅ 22(3) እና 22(5) ስር የተከለከሉት ድርጊቶች የተፈፀሙት ብዛት ያላቸውን የጦር መሳሪያዎችን በተመለከተ ከሆነ ፣ ቅጣት በሚወሰንበት ጊዜ የጦር መሳሪያውን አይነት መሰረት በማድረግ በሚገኘው መነሻ የቅጣት እርከን ላይ እስከ አራት እርከን ከፍ በማድረግ መነሻ ቅጣት ይወሰናል፡፡ ሆኖም ግን በአዋጁ ለወንጀሉ ዓይነት ከተቀመጠው የቅጣት መጠን ጣሪያ ማለፍ የለበትም፡፡

10. ፍርድ ቤቱ ከላይ በተመለከተው ድንጋጌ በመሰረት የሚጨመረው የመነሻ ቅጣት እርከን፣ በአዋጁ አንቀፅ 2(10) እና በዚህ መመሪያ ንኡስ አንቀፆች "ብዛት ያለው የጦር መሳሪያን" በተመለከተ የተደነገጉ ዝቅተኛ መመዘኛዎችን ቅጣት በሚወሰንበት ጉዳይ በማስረጃ ከተረጋገጠው የጦር መሳሪያ ብዛት ጋር በማነፃፀር ምክንያታዊነትን በተከተለ መንገድ መሆን አለበት፡፡

11. ከላይ ከተመለከቱት ንዑስ አንቀፆች ውጭ ወንጀሎቹ የተፈፀሙት አጠቃላይ ብዛታቸው ከሁለት በላይ ሆኖ ፣ ዓይነታቸው የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን በተመለከተ ከሆነ፣ ይበልጥ አደገኛ የሆነው የጦር መሳሪያ የሚያርፍበትን ደረጃ እና የቅጣት እርከን መሰረት በማድረግ መነሻ ቅጣት ይያዛል፡፡ ፍ/ቤቱ ለተጨማሪው የጦር መሳሪያ ዓይነት አግባብ ነው ያለውን የእርከን ጭማሪ ያደርጋል፡፡

12. ፍርድ ቤቱ በዚህ መመሪያ ደረጃ ለማውጣት ጥቅም ላይ በዋሉ መስፈርቶች ውስጥ የማይካተቱ ወንጀሎች በተገኙ ጊዜ፣ የአዋጁን እና የመመሪያውን ዓላማ መሰረት በማድርግ ቅጣት ይወሰናል፡፡

**108. የአዋጁ አንቀጽ 22(2)**

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን (ለተፈጥሮ ሰዎች) | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን (የሕግ ሰውነት ለተሰጣቸው) |
|---|---|---|---|---|---|
| አንቀጽ 22(2) | 1 | ማንም ሰው የፀና ፈቃድ ሳይኖረው ስምንት እና ከዚያ በታች ብዛት ያላቸው የጦር ሜዳ መነፅር፣ የጦር መሳሪያ ላይ ሊገጠም የሚችል ማናቸውም ዓይነት መነፅር ወይም የጦር መሳሪያ ሲተኮስ ድምፅ ለማስወገድ የሚያገለግል መሳሪያ ወይም ተያያዥነት ያላቸውን አባሪዎች ወደ ሃገር ያስገባ፣ ካገር ያስወጣ፣ያስቀመጠ፣ የተገለገለ፣ያሳየ፣ የደለለ፣ የሸጠ፣ የገዛ፣ ያጓጓዘ፣ ያመረተ፣ ያሰለጠነ፣ የጠገነ፣ ያስወገደ፣ በማናቸውም መንገድ | 7 | 3 | 18 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ያስተላለፈ ወይም የያዘ እንደሆነ፡ | | | |
| አንቀጽ 22(2) | 2 | 1. በደረጃ-1 የተመለከቱት ድርጊቶች የተፈፀሙት ብዛታቸው ስምንት እና ከዚያ በታች የሆኑ ቀላል የጦር መሳሪያ እና አውቶማቲክ ያልሆነ የጦር መሳሪያ ጥይቶችን (በካርታ ወይም ያለ ካርታ) ከሆነ፡፡<br>ወይም<br>2. ለአንድ ሰው ፈቃድ ሊሰጠው እስከሚችለው ድረስ ብዛት ያላቸው የአውቶማቲክ እና በከፊል አውቶማቲክ ጥይቶችን ከሆነ፡፡ | 8 | 4 | 19 |
| አንቀጽ 22(2) | 3 | በደረጃ-1 የተመለከቱት ድርጊቶች የተፈፀሙት አነስተኛ የጦር መሳሪያን ወይም አውቶማቲክ ያልሆነ የጦር መሳሪያን በተመለከተ ከሆነ፡ | 9 | 4 | 20 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አንቀጽ 22(2) | 4 | በደረጃ-1 የተመለከቱት ድርጊቶች የተፈፀሙት በከፊል አውቶማቲክ የሆነ የጦር መሳሪያን በተመለከተ ከሆነ፡፡ | 12 | 4 | 21 |
| አንቀጽ 22(2) | 5 | በደረጃ-1 የተመለከቱት ድርጊቶች የተፈፀሙት ሙሉ አውቶማቲክ ጠመንጃን ወይም ቦምብን በተመለከተ ከሆነ፡፡ | 13 | 5 | 22 |

**109. የአዋጁ አንቀጽ 22(3)**

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን (ለተፈጥሮ ሰዎች) | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን (የሕግ ሰውነት ለተሰጣቸው) |
|---|---|---|---|---|---|

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አንቀጽ 22(3) | 1 | ማንም ሰው የፀና ፈቃድ ሳይኖረው ዘጠኝ እና ከዚያ በላይ የሆኑ የጦር ሜዳ መነፅሮች፣ የጦር መሳሪያ ላይ ሊገጠሙ የሚችሉ ማናቸውም ዓይነት መነፅሮች ወይም የጦር መሳሪያ ሲተኮስ ድምፅ ለማስወገድ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች ወይም ተያያዥነት ያላቸውን አባሪዎች ወደ ሃገር ያስገባ፣ ካገር ያስወጣ፣ያስቀመጠ፣ የተገለገለ፣ያሳየ፣ የደለለ፣ የሸጠ፣ የገዛ፣ ያጓጓዘ፣ ያመረተ፣ ያሰለጠነ፣ የጠገነ፣ ያስወገደ፣ በማናቸውም መንገድ ያስተላለፈ ወይም የያዘ እንደሆነ፡፡ | 30 | 11 | 18 |
| አንቀጽ 22(3) | 2 | 1. በድንጋጌው የተከለከቱት ተግባራት የተፈፀሙት ብዛታቸው ዘጠኝ እና ከዚያ በላይ የሆኑ ቀላል የጦር መሳሪያ እና አውቶማቲክ ያልሆነ የጦር መሳሪያ ጥይቶችን (በካርታ ወይም ያለ ካርታ) በተመለከተ ከሆነ፡፡<br>ወይም<br>2. ለአንድ ሰው ፈቃድ ሊሰጠው ከሚችለው በላይ ብዛት ያላቸው የአውቶማቲክ እና | 32 | 11 | 19 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በከፊል አውቶማቲክ ጥይቶችን ከሆነ፡፡ | | | |
| አንቀጽ 22(3) | 3 | በድንጋጌው የተከለከሉት ተግባራት የተፈፀሙት ብዛታቸው ከሁለት በላይ የሆኑ አነስተኛ የጦር መሳሪያዎች ወይም አውቶማቲክ ያልሆኑ የጦር መሳሪያዎችን በተመለከተ ከሆነ፡፡ | 34 | 12 | 20 |
| አንቀጽ 22(3) | 4 | በድንጋጌው የተከለከሉት ተግባራት የተፈፀሙት ብዛታቸው ከሁለት በላይ የሆኑ በከፊል አውቶማቲክ የሆኑ የጦር መሳሪያዎች በተመለከተ ከሆነ፡፡ | 36 | 13 | 21 |
| አንቀጽ 22(3) | 5 | በድንጋጌው የተከለከሉት ተግባራት የተፈፀሙት የተፈፀሙት ብዛታቸው ከሁለት በላይ በሆኑ ሙሉ አውቶማቲክ ጠመንጃዎችን ወይም ቦምቦችን በተመለከተ ከሆነ | 38 | 14 | 22 |

## 110. ሕጋዊ የጦር መሳሪያን በተቆጣጣሪ አካል ሳይፈቀድ ለአሸባሪ ወይም ሕገወጥ ቡድን መሸጥ ( የአዋጁ አንቀፅ 22(5))

| የወንጀል ሕግ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን (ለተፈጥሮ ሰዎች) | የገንዘብ መቀጮ መነሻ እርከን (የሕግ ሰውነት ለተሰጣቸው) |
|---|---|---|---|---|---|
| አንቀጽ 22(5) | 1 | ማንም ሰው በ ተቆጣጣሪው አካል ሳይፈቀድለት በሕጋዊ መንገድ የታጠቀውን የጦር ሜዳ መነፅር፣ የጦር መሳሪያ ላይ ሊገጠም የሚችል ማናቸውም ዓይነት መነፅር ወይም የጦር መሳሪያ ሲተኮስ ድምፅ ለማስወገድ የሚያገለግል መሳሪያ ወይም ተያያዥነት ያላቸውን አባሪዎች ለ አሸባሪ ወይም ሕገ ወጥ ቡድን የሸጠ እንደሆነ፡፡ | 8 ወይም 10 | ---- | 18 |
| አንቀጽ 22(5) | 2 | ለ አሸባሪ ወይም ሕገ ወጥ ቡድን የተሸጠው ጥይት ከሆነ፡፡ | 9 ወይም | --- | 19 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | 11 | | |
| አንቀጽ 22(5) | 3 | ለ አሸባሪ ወይም ሕገ ወጥ ቡድን የተሸጠው የተሸጠው አነስተኛ የጦር መሳሪያ ወይም አውቶማቲክ ያልሆነ የጦር መሳሪያ ከሆነ፡፡ | 12 ወይም 14 | ---- | 20 |
| አንቀጽ 22(5) | 4 | ለ አሸባሪ ወይም ሕገ ወጥ ቡድን የተሸጠው በከፊል አውቶማቲክ የሆነ የጦር መሳሪያ ከሆነ፡፡ | 13 ወይም 16 | ----- | 21 |
| አንቀጽ 22(5) | 5 | ለ አሸባሪ ወይም ሕገ ወጥ ቡድን የተሸጠው ሙሉ አውቶማቲክ ጠመንጃ ወይም ቦምብ ከሆነ፡፡ | 14 ወይም 18 | ------ | 22 |

# ርዕስ አስራ አምስት

## ሰዉን በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1178/2012)

### 111. ጠቅላላ

1. ሰዉን በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣውን (አዋጅ ቁጥር 1178/2012) ክልከላዎች በመተላለፍ በወንጀል ጥፋተኛ በሚባሉ ሰዎች ላይ ቅጣት የሚጣለው በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

2. በዚህ መመሪያ ደረጃ በወጣላቸው ወንጀሎች ደረጃ ለመለየት ፣ በድንጋጌዎቹ ላይ የተዘረዘሩትን የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬነገሮች፣ ወንጀሉን ለማክበድ የተደነገጉት ምክንያቶች፣ ጥፋተኛ የተባለው ሰዉ ባገኘዉ የገንዘብ ጥቅም ወይም ተበዳይ ያጣዉ የጥቅም መጠን እንደ መስፈርት ተወስደዋል፡፡

3. ከዚህ በታች ባለዉ ሰንጠረዥ፣ አነስተኛ የቅጣት መጠን ካለው ወንጀል ለመጀመር ሲባል ከአዋጁ አንቀጽ 3/2 ድንጋጌ እንዲጀምር ተደርጓል፡፡

| የአዋጁ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 3/2 | 1 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ከሆነ፡፡ | 27 | 8 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 2 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ፣ ተከሳሽ እስከ ሁለት መቶ ሺ. ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ ከሆነ | 28 | |
| | 3 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከሁለት መቶ አንድ ሺ. ብር እስከ አምስት መቶ ሺ. ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ ከሆነ | 29 | 9 |
| | 4 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከአምስት መቶ አንድ ሺ. ብር እስከ አንድ ሚሊዮን ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ ከሆነ | 31 | 10 |
| | 5 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ጥቅም ያገኘ ከሆነ | 34 | 11 |
| 3/1 | 1 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ከሆነ፡፡ | 28 | 9 |
| | 2 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ እስከ ሁለት መቶ ሺ. ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ ከሆነ | 29 | 9 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከሁለት መቶ አንድ ሺ ብር እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ ከሆነ | 30 | 10 |
| | 4 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከአምስት መቶ አንድ ሺ ብር እስከ አንድ ሚሊዮን ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ ከሆነ | 32 | 11 |
| | 5 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ጥቅም ያገኘ ከሆነ | 36 | 11 |
| 4/1 | 1 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ከሆነ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | 33 | 7 |
| | 2 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ ወይም<br><br>በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም | 34 | 7 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ያልታወቀ ከሆነ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተው ሲገኙ፡፡ | | |
| | 3 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም ከአምስት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ በድጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ ወይም<br><br>በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ከሆነ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሶስቱ ተሟልተው ሲገኙ፡፡ | 35 | 7 |
| | 4 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ሆኖ ወይም/ እና በድጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ ወይም<br><br>በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ከሆነ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አራቱ ተሟልተው ሲገኙ፡፡ | 36 | 8 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 5 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም ከአምስት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 37 | 8 |
| | 6 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ሆኖ ወይም/ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሦሥቱ ተሟልተዉ ሲገኙ | 38 | 9 |
| | 7 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም ከአምስት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሦሥቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 39 | 9 |
| | 8 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ሆኖ ወይም/ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አራቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 40 | 10 |
| | 9 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም ከአምስት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አራቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 41 | 11 |
| 4/2 | 1 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም | 38 | 9 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ያልታወቀ ከሆነ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | | |
| | 2 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም እስከ አምስት መቶሺ ብር ሆኖ ወይም/ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | 39 | 9 |
| | 3 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም ከአምስት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | 40 | 10 |
| | 4 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ሆኖ ወይም/ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 41 | 11 |
| | 5 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም ከአምስት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 42 | 11 |
| | 6 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ሆኖ ወይም/ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሦሥቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 43 | 12 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 7 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም ከአምስት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሦሥቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 43 | 12 |
| 4/2/መ | 1 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም መጠን ምንም ያህል ቢሆን ወይም ጥቅም ባያገኝም በድንጋጌዉ ስር ያለዉ ማክበጃ ምክንያት ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | 45 | 14 |
| **የአዋጁ ድንጋጌ** | **የወንጀሉ ደረጃ** | **የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ** | **የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን** | **የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን** |
| 8/1 | 1 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ከሆነ። | 23 | 5 |
| | 2 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ወይም/እና ተከሳሽ እስከ ሁለት መቶ ሺ ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ። | 24 | 5 |
| | 3 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ከሁለት መቶ አንድ ሺ ብር እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ። | 26 | 7 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 4 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከአምስት መቶ አንድ ሺ ብር እስከ አንድ ሚሊዮን ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ፡፡ | 29 | 9 |
| | 5 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ጥቅም ያገኘ | 31 | 11 |
| 8/2 | 1 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | 28 | 9 |
| | 2 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ሆኖ በድጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ ወይም በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተው ሲገኙ፡፡ | 29 | 9 |
| | 3 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም ከአምስት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ በድጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ ወይም በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት | 30 | 9 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሶስቱ ተሟልተው ሲገኙ፡፡ | | |
| | 4 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ሆኖ ወይም/ እና በድጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡<br><br>በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አራቱ ተሟልተው ሲገኙ፡፡ | 31 | 10 |
| | 5 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም ከአምስት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ በድጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 32 | 10 |
| | 6 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ሆኖ ወይም/ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሦሥቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 33 | 11 |
| | 7 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም ከአምስት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሦሥቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 34 | 11 |
| | 8 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ሆኖ ወይም/ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት | 35 | 12 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አራቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | | |
| | 9 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም ከአምስት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አራቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 36 | 12 |
| 8/3 | 1 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ከሆነ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | 33 | 7 |
| | 2 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ሆኖ ወይም/ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ ወይም<br><br>በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ከሆነ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተው ሲገኙ፡፡ | 34 | 7 |
| | 3 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም ከአምስት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ ወይም | 35 | 8 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ከሆነ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሶስቱ ተሟልተው ሲገኙ፡፡ | | |
| | 4 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ሆኖ ወይም/ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 37 | 9 |
| | 5 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም ከአምስት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 39 | 10 |
| | 6 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ሆኖ ወይም/ እና በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሦሥቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 40 | 11 |
| | 7 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም ከአምስት መቶ ሺ ብር በላይ ሆኖ በድንጋጌዉ ስር ካሉት ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ ሦሥቱ ተሟልተዉ ሲገኙ፡፡ | 41 | 12 |
| 8/3/መ | 10 | ተከሳሽ ያገኘዉ ጥቅም መጠን ምንም ያህል ቢሆን ወይም ጥቅም ባያገኝም በድንጋጌዉ ስር ያለዉ ማክበጃ ምክንያት ተሟልቶ ሲገኝ፡፡ | 45 | 14 |

| የአዋጁ ድንጋጌ | የወንጀሉ ደረጃ | የወንጀሉ ደረጃ መግለጫ | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን | የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን |
|---|---|---|---|---|
| 11/1 | | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ከሆነ። | 27 | 7 |
| | 1 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ወይም/ እና ተከሳሽ እስከ ሁለት መቶ ሺ ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ ከሆነ። | 28 | 7 |
| | 2 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከሁለት መቶ አንድ ሺ ብር እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ ከሆነ። | 29 | 8 |
| | 3 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከአምስት መቶ አንድ ሺ ብር እስከ አንድ ሚሊዮን ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ ከሆነ። | 31 | 9 |
| | 4 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ጥቅም ያገኘ ከሆነ። | 33 | 10 |
| 11/2 | 1 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ከሆነ። | 26 | 7 |
| | 2 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ወይም/ እና ተከሳሽ እስከ አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ ከሆነ። | 27 | 7 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከአንድ መቶ ሃምሳ አንድ ሺ ብር እስከ ሦሥት መቶ ሃምሳ ሺ ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ ከሆነ፡፡ | 29 | 8 |
| | 4 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከሦሥት መቶ ሃምሳ አንድ ሺ ብር እስከ ሰባት መቶ ሺ ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ ከሆነ፡፡ | 32 | 9 |
| | 5 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከሰባት መቶ አንድ ሺ ብር በላይ ጥቅም ያገኘ ከሆነ፡፡ | 36 | 10 |
| 11/3 | 1 | በድንጋጌው አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ያገኘው ጥቅም፣ ወይም በተበዳይ ላይ የደረሰው የገንዘብ ጉዳት የሌለ ወይም ያልታወቀ ከሆነ፡፡ | 38 | 9 |
| | 2 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ወይም/ እና ተከሳሽ እስከ አንድ መቶ ሺ ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ፡፡ | 39 | |
| | 3 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከአንድ መቶ አንድ ሺ ብር እስከ ሁለት መቶ ሃምሳ ሺ ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ፡፡ | 40 | 11 |
| | 4 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከሁለት መቶ ሃምሳ አንድ ሺ ብር እስከ አምስት መቶ ሺ ብር ድረስ ጥቅም ያገኘ፡፡ | 42 | 13 |
| | 5 | በድንጋጌዉ አግባብ ድርጊቱ ተፈጽሞ ተከሳሽ ከአምስት መቶ አንድ ብር በላይ ጥቅም ያገኘ፡፡ | 44 | 14 |

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>ደረጃ ላልወጣላቸው ወንጀሎች በቅጣት ማንዋሉ መሰረት ስለሚሰራበት ሁኔታ</u>

### 112. ደረጃ ላልወጣላቸው ወንጀሎች የወንጀል ደረጃና የቅጣት መነሻ እርከን አወሳሰን

1. ወደፊት በወንጀል ሕጉ እና በሌሎች የወንጀል ሕጎች ለተደነገጉት ዝርዝር የወንጀል ድርጊቶች የወንጀል ደረጃዎች እየተለየ የሚወጣላቸው ሆኖ፣ ደረጃ ወጥቶ እስከሚመደብ ድረስ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በታች በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ቅጣት ይወስናል፡፡

2. ወንጀሉን የሚደነግገው ድንጋጌ በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት ሊያስቀጣ እንደሚችል በደነገገ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ደረጃውን ለማውጣት በቅድሚያ በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ይወስናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሁለት በተመለከተው መሰረት ከተወሰነ በኋላ፣ ፍርድ ቤቱ በወንጀል ድንጋጌው ከተቀመጠው መስፈርት (ፍሬ ነገር) አንጻር እና የቅጣት ማክበጀና ማቅለያ ምክንያቶችን ታሳቢ ከማድረጉ በፊት ወንጀሉን በክብደቱና በአፈፃፀሙ፣

    ሀ. ቀላል

    ለ. መካከለኛ፣

    ሐ. ከባድ የወንጀል ደረጃ በማለት ይመድባል፡፡

4. ፍርድ ቤቱ ወንጀሉን ‹ቀላል› ‹መካከለኛ› ወይም ‹ከባድ› በማለት ለመመደብ ምክንያቱን በውሳኔው ላይ በግልፅ ማስፈር አለበት፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ወይም 3 መሰረት የወንጀሉን ደረጃ ለመወሰን የሚከተሉት እንደመለኪያ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ ይሁንና ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች ደረጃውን ለመወሰን እንደመለኪያ (መስፈርት) ሊወሰዱ አይችሉም፡፡

    ሀ. የወንጀሉ አፈፃፀም ሁኔታ

    ለ. የደረሰው ጉዳት ዓይነትና መጠን፣

    ሐ. የተገኘው ጥቅም መጠን፣

መ. ወንጀሉ ታስቦ የተሰራ መሆን አለመሆን

ሠ. ወንጀሉ በቸልተኝነት ሲሰራ የሚያስቀጣ ከሆነ ቸልተኝነቱ የታወቀ ወይም ያልታወቀ ቸልተኝነት መሆኑ፣

6. ፍርድ ቤቱ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ስር በተመለከቱትን መስፈርቶች ብቻ ሳይወሰን ሌሎች መስፈርቶችን በመጠቀም ደረጃውን ለመወሰን ይችላል፡፡ በተለይም በመመሪያው ደረጃ ለወጣላቸው ተመሳሳይ ባሕሪይ ላላቸው ወንጀሎች ደረጃ ለማውጣት ጥቅም ላይ የዋሉ መስፈርቶችን ደረጃ ያልወጣላቸው ወንጀሎችም የክብደት ደረጃ ለመለየት ታሳቢ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተመለከተው መሰረት የወንጀል ደረጃው ከተለየ በኋላ ለወንጀል ደረጃው የቅጣት እርከኑን ለመወሰን እንዲቻል በልዩ ክፍሉ ለወንጀሉ በተቀመጠው የቅጣት መነሻና መካከል ያለውን ርዝመት ለአራት እኩል በመክፈል፤

ሀ. በወንጀል ሕግ ለቅጣቱ መነሻ ተብሎ ከተቀመጠው የቅጣት መጠን የሚጀምረው አንድ አራተኛ (ጊዜ ወይም መጠን) እርከን አንድ ይባላል፡፡

ለ. ከመጀመሪያው አንድ አራተኛ ቀጥሎ ያሉት እርከኖች እንደ ቅደም ተከተላቸው እርከን ሁለት፣ እርከን ሶስት፣ እርከን አራት ይባላሉ፡፡

8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ‹ቀላል› በሚለው የወንጀል ደረጃ ውስጥ ለተመደበው ፍርድ ቤቱ በእርከን አንድ ባለው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ መነሻ ቅጣቱን ይወስናል፡፡

9. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 3 መሰረት ‹መካከለኛ› በሚለው የወንጀል ደረጃ ውስጥ ለተመደበው ፍርድ ቤቱ በእርከን ሁለት ባለው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ መነሻ ቅጣቱን ይወስናል፡፡

10. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት ‹ከባድ› በሚለው የወንጀል ደረጃ ውስጥ ለተመደበው ፍርድ ቤቱ በእርከን ሦስት ባለው ፍቃድ ሥልጣን ውስጥ መነሻ ቅጣቱን ይወስናል፡፡ ሆኖም የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት እጅግ ከባድ ነው ብሎ ፍ/ቤቱ ከወሰነ በዚህ ድንጋጌ ሳይወሰን መነሻ ቅጣቱን እርከን 4 ስር ሊወስን ይችላል፡፡

11.በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 8፣ 9 ወይም 10 መሰረት በፍርድ ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት በአባሪ-1 በተያያዘው የቅጣት ሠንጠረዥ እርከን የትኛው እርከን ላይ እንደሚወድቅ በመለየት የቅጣት እርከኑን በሰንጠረዥ መሰረት ይለያል፡፡ ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 8፣ 9 ወይም 10 መሰረት ያስቀመጠው የቅጣት መጠን በአባሪ አንድ በተያያዘው የቅጣት ሰንጠረዥ ሁለት ተከታታይ እርከኖች ውስጥ የሚወድቅ ከሆነ፡ በዝቅተኛ እርከን ውስጥ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

12.በዚህ አንቀፅ መሰረት ቅጣታቸው የሚወሰን የወንጀል አይነቶች በመቀጮ ብቻ የሚያስቀጡ ወይም በእስር የሚያስቀጡ ወይም በመቀጮ እና በእስር የሚያስቀጡ መሆን በተደነገገ ጊዜ፣ ወይም በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 92/2 መሰረት መቀጮ መጣል የሚያስፈልግ በሆነ ግዜ ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ወይም ልዩ ክፍል ወይም በሌላ ሕግ የተቀመጠውን ጣሪያ መሰረት በማድረግ፣ ‹ለከባዱ› በሕጉ እስከተመለከተው ጣሪያ ድረስ፣ ‹መካከለኛ› ለሆነው በሕጉ ከተመለከተው ጣሪያ ላይ የጣሪያውን አንድ ሶስተኛ በመቀነስ እስከሚደረስበት መጠን ድረስ፣ እንዲሁም ‹ቀላል› ለሆነው በሕጉ ከተመለከተው ጣሪያ ላይ፣ የጣሪያውን በሁለት ሶስተኛ በመቀነስ እስከሚደርስበት መጠን ድረስ መቀጮውን ይወስናል፡፡

## 113. ቅጣቱ በወንጀል ሕግ ተለይቶ በሚታወቅበት ጊዜ ስለ ቅጣት አጣጣል

1. በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ወይም በልዩ ልዩ ሕጎች ለተፈፀመው ወንጀል የሚጣለው ቅጣት ለፍርድ ቤት ፍቅድ ስልጣን ያልሰጠ አንድ የታወቀ ቅጣት ከሆነ ይህ ቅጣት መነሻ ቅጣት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
2. በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ወይም በልዩ ልዩ ሕጎች ለተፈጸመው ወንጀል የሚጣለው ቅጣት ከሁለት ያልበለጡ አማራጮች ያሉት ከሆነ በዚህ መመሪያ መመሪያ መመሪያ መመሪያ መመራት ሳያስፈልግ ጥፋቱ ከባድ ወይም ቀላል መሆኑ ይለያል ቀላል ከሆነ ዝቅተኛው አማራጭ ወይም ከባድ ከሆነ ከፍተኛው አማራጭ መነሻ ቅጣት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

# ክፍል አራት

## የቅጣት ማክበጃና ማቅለያዎችን ስለ ማስላት

### ንዑስ ክፍል አንድ

### የቅጣት ማክበጃዎችን ስለ ማስላት

**114. ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ቅጣቱ ስለሚከብድበት አሰራር**

ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩ ጊዜ ቅጣቱ የሚከብደው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው መሰረት ይሆናል፡፡

1. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ 1 ከ‹ሀ› እስከ ‹ሠ› በአምስት ንዑሳን ድንጋጌዎች ተዘርዝረው የተመለከቱት ማክበጃ ምክንያቶች እያንዳንዳቸው እንደ አንድ ማክበጃ ምክንያት በጠቅላላው እንደ አምስት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ተደርገው ተወስደዋል፡፡ ሆኖም በአንዱ ፊደል ስር የተደራረቡ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በተገኙ ጊዜ፣ በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ለወንጀሉ የተቀመጠው ከፍተኛው ቅጣት ጣሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፍ/ቤቱ ምክንያቱን በመግለጽ ቅጣቱን እንደ ሁኔታው በማክበድ ይወስናል፡፡ ነገር ግን በተደራራቢነት የሚወሰዱ እና በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ፊደላት ስር የሚገኙ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች አጠቃላይ ብዛት ከአምስት መብለጥ የለባቸውም፡፡

2. በእያንዳንዱ ድንጋጌ ‹ሀ›፣‹ለ›፣‹ሐ›፣‹መ›፣‹ሠ› ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ እንኳን ተሟልቶ ቢገኝ አንድ የቅጣት ማክበጃ እንደተሟላ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

3. በእያንዳንዱ ድንጋጌ ‹ሀ›፣‹ለ›፣‹ሐ›፣‹መ›፣‹ሠ› ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ ወይም በከፊል ወይም በሙሉ ተሟልተው ሲገኙ፣ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ ሲከብድ የሚደርስበት የቅጣት እርከን ውስጥ ባለው ፍቅድ ስልጣን ከዝቅተኛው እስከ ጣሪያው ባለው ውስጥ ቅጣቱ የሚወድቅበትን ይወስናል፡፡

4. ፍርድ ቤቱ በእያንዳንዱ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ብዛት ልክ መነሻ ቅጣቱ ከሚያርፍበት የቅጣት እርከን ወደላይ ይጨምራል፡፡ ይሁንና በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል

ወይም በሌሎች ልዩ ልዩ የወንጀል ሕጎች ለወንጀሉ ከተቀመጠው የቅጣት ጣሪያ ማለፍ አይችልም፡፡

### 115. ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በሚኖሩ ጊዜ ቅጣቱ ስለሚከብድበት አሰራር

1. ወንጀል አድራጊው በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ በሆነ ጊዜ፣

   ሀ. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 በተመለከተው መሰረት ለእያንዳንዱ ወንጀል ቅጣት ወስኖ የሚደመር በሆነ ጊዜ በዚህ መመሪያ መሰረት ለእያንዳንዱ ወንጀል መነሻ ቅጣት ካስቀመጠ በኋላ እነዚህን በመደመር ድምሩ የቅጣት መጠን የሚያርፍበትን ዝቅተኛ የቅጣት እርከን በመምረጥ እርከኑን ይለያል፡፡ በመቀጠልም በወንጀል ሕግ ከተመለከተው ጣሪያ ሳይበልጥ ጠቅላላ ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣቱ ያድጋል፡፡

   ለ. ከላይ ባለው ንኡስ አንቀፅ የተደነገገው ቢኖርም ፣ የሚመረጠው ዝቅተኛ የቅጣት እርከን ፣ ለተደራራቢ ወንጀሎቹ በተናጥል መነሻ ቅጣት ሲሰላ፣ ከባዱ ወንጀል አርፎበት ከነበረው የቅጣት እርከን በታች ሊሆን አይችልም፡፡

   ሐ. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 187 ንዑስ አንቀጽ 1 ሁለተኛ ፓራግራፍ እና ንዑስ አንቀጽ 2/ለ እንደተመለከተው ቅጣቱ የሚከብድ በሆነ ጊዜ ለእያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል ከመነሻው እርከን በሁለት እርከን እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ በመቀጠልም ጠቅላላ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት አድርጎ ይከብዳል፡፡ ይሁንና ለከባዱ ወንጀል ከተደነገገው ጣሪያ መብለጥ የለበትም፡፡

2. ጥፋተኛው ደጋጋሚ ወንጀለኛ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ለአዲስ ወንጀል የመነሻ ቅጣቱ የሚያርፍበትን እርከን በዚህ መመሪያ መሰረት ከለየ በኋላ ቅጣቱን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 188 በተመለከተው መሰረት ከአንድ እርከን ጀምሮ ቅጣቱን ሊያሳድግ ይችላል፡፡ በመቀጠልም ጠቅላላ ቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ቅጣቱን ያከብዳል፡፡ ነገር ግን በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ለቅጣቱ ዓይነት ከተቀመጠው ጣሪያ ሊበልጥ አይችልም፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የቅጣት ማቅለያዎችን ስለማስላት

### 116. ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ ስለሚኖረው አሰራር

ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያዎች በሚኖሩ ጊዜ ቅጣቱ የሚቀለው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው መሰረት ይሆናል፡፡

1. ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሕግ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 1 ከ‹ሀ› እስከ ‹ሠ› በአምስት ንዑሳን ድንጋጌዎች ተዘርዝረው የተመለከቱት ማቅለያ ምክንያቶች እያንዳንዳቸው እንደ አንድ ማቅለያ ምክንያት በጠቅላላው እንደ አምስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ተደርገው ተወስደዋል፡፡ ሆኖም በአንዱ ፊደል ስር የተደራረቡ የቅጣት ማቅለያ ድንጋጌዎች በተገኙ ጊዜ ፍ/ቤቱ ምክንያቱን በመግለጽ ቅጣቱን እንደ ሁኔታው በማቅለል ሊወስን ይችላል፡፡ ነገር ግን በተደራራቢነት የሚወሰዱ እና በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ፊደላት ስር የሚገኝ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አጠቃላይ ብዛት ከአምስት መብለጥ የለባቸውም፡፡

2. በእያንዳንዱ ድንጋጌ ‹ሀ›፣‹ለ›፣‹ሐ›፣‹መ›፣‹ሠ› ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ እንኳን ተሟልቶ ቢገኝ አንድ የቅጣት ማቅለያ እንደተሟላ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

3. በእያንዳንዱ ድንጋጌ ‹ሀ›፣‹ለ›፣‹ሐ›፣‹መ›፣‹ሠ› ከተመለከቱት ምክንያቶች አንዱ ወይም በከፊል ወይም በሙሉ ተሟልተው ሲገኙ፣ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱ ሲቀል የሚደርስበት የቅጣት እርከን ውስጥ ባለው ፍቅድ ስልጣን ከዝቅተኛው እስከ ጣሪያው ባለው ውስጥ ቅጣቱ የሚወድቅበትን ይወስናል፡፡

4. በቀላል እና በጽኑ እስራት ለሚያስቀጡ ወንጀሎች ፍርድ ቤቱ ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት መነሻ ቅጣቱ ከሚያርፍበት የቅጣት እርከን አንድ እርከን ወደታች ይቀንሳል፡፡ ስለሆነም በቅጣት ማቅለያዎቹ ቁጥር ልክ የቅጣት እርከኑም እንደዚሁ ይቀንሳል፡፡ ይሁንና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 179 ከተደነገገው ዝቅተኛ ወለል በታች ሊወርድ አይችልም፡፡

5. በቀላል እና ጽኑ እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራራቢ ሆነው የሚደመሩ በሆነ ጊዜ በቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች የሚቀንሰውን እርከን መጠን ለመወሰን የቀላል እስራት ቅጣት በሕጉ አግባብ ወደ ጽኑ እስራት ተቀይሮ ቅጣቶቹ ተደምረው የሚመጣው ውጤት የቅጣት መነሻ ተደርጎ ይወሠዳል፡፡
6. በሙከራ ደረጃ የቀሩ ወንጀሎችን በተመለከተ፣ ፍ/ቤቱ ቅጣትን ማቅለል የሚገባ ሆኖ ሲያገኘው፣ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 179 ከተደነገገው ዝቅተኛ ወለል በታች ሳይወርድ ቅጣት ሊያቀል ይችላል፡፡
7. በሙከራ ደረጃ ለቀሩ ወንጀሎች ቅጣት ማቅለል ተገቢ መሆኑን ለመወሰን፣የሙከራውን ዓይነት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ፍሬነገሮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡

### 117. ልዩ የቅጣት ማቅለያዎች

በወንጀል ሕግ ቅጣትን በመሰለው እንዲያቀል በፈቀደ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት ሳይወሰን ቅጣቱን በማቅለል ይወስናል፡፡

### 118. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 86 መሰረት የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያዎች በሚኖሩ ጊዜ ስለሚሰላበት ሁኔታ

1. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 86 መሰረት የቀረቡ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩበት ጊዜ፣ ተቀባይነታቸው የሚመዘናው ድንጋጌው የልዩ ሁኔታ ድንጋጌ መሆኑን ታሳቢ ባደረገ እና ምክንያቶቹ ይህን ጥብቅ መመዘኛ ማሟላታቸውን በማረጋገጥ መሆን አለበት፡፡ ለዚሁም ምክንያቱን በውሳኔው ላይ በግልፅ መስፈር አለበት፡፡
2. ተመሳሳይ ባህርይ ያላቸው ምክንያቶች ከአንድ ጊዜ በላይ በቅጣት ማቅለያነት መያዝ የለባቸውም፡፡
3. በዚሁ መሰረት ተቀባይት ያላቸው የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በዚህ መመሪያ ጠቅላላ ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች በሚኖሩ ጊዜ እንደሚኖረው አሰራር ቅጣቱን የሚያከብዱ ወይም የሚያቀሉ ይሆናል፡፡
4. ከላይ ባሉት ንዑሳን አንቀጾች ሌሎች የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አያየዝን አስመልክቶ የተደነገገው፣ በቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ላይም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል አምስት

## የቅጣት አሰላል ስነ ስርዓት

### 119. የቅጣት አሰላል ስነ ስርዓት ቅደም ተከተል

በዚህ መመሪያ መሰረት ፍርድ ቤቱ ቅጣት ሲወስን የሚከተለውን ቅደም ተከተል መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡

1. የወንጀል ደረጃ የወጣላቸውን የወንጀል አይነቶች በተመለከተ፣

   ሀ. የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በዚህ መመሪያ ክፍል ሶስት በተመለከተው መሰረት የወንጀሉን ደረጃ ይወስናል፡፡

   ለ. የወንጀሉ ደረጃ የሚወድቅበትን የቅጣት እርከን በአባሪ አንድ ከተያያዘው የቅጣት ሠንጠረዥ ላይ ይለያል፡፡

   ሐ. ድንጋጌው ቀላልና ጽኑ እስራትን በአማራጭነት ባስቀመጠ ጊዜ ፍ/ቤት ወንጀል በቀላል እስራት ወይም  በጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን ይወስናል፡፡

   መ. በእርከኑ በተቀመጠው የቅጣት መነሻና መድረሻ መካከል ባለው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ መነሻ ቅጣት ይወስናል፡፡ ይሁንና ፍርድ ቤቱ የተቀበላቸው የቅጣት ማክበጃ ወይም ማቅለያ ምክንያቶች ካሉ በዚህ ድንጋጌ መሰረት መነሻ ቅጣቱን መወሰን ሳያስፈልግ ቅጣቱን ያከበዳል ወይም ያቃላል፡፡

   ሠ. ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ካሉ በዚህ መመሪያ መሰረት ቅጣቱን አክብዶ ቅጣቱ የሚደርስበትን እርከን ይወስናል፡፡

   ረ. ፍ.ቤቱ ተደራራቢ በሆኑ ወንጀሎች መነሻ ቅጣት ሲያሰላ የሚያገኘው የቅጣት መጠን በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ቅጣት ጣሪያ የሚደርስ ከሆነ እና የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ሲያዙ በመነሻ ቅጣት ተደርሶበት የነበረው ቅጣት ከቀለለ፣ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184(1) (ለ) መሰረት በሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎች በተወሰኑ ቅጣቶች ምክንያት እስከ አጠቃላዩ የእስራት ጣሪያ ድረስ ቅጣቱን በማክበድ ይወስናል፡፡

ሰ. ፍ/ቤቱ በተቀበላቸው ጠቅላላ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን በማስረጃ ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቂ ጊዜ ሰጥቶ ሊጣራ ይችላል፡፡

ሸ. ፍ/ቤቱ በተቀበላቸው ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች መሰረት የሚቀንሰውን እርከን በመለየት ቅጣቱን ይወስናል፡፡ ሆኖም ክርክር የተነሳባቸው የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በማስረጃ ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቂ ጊዜ ሰጥቶ ሊያጣራ ይችላል፡፡

ቀ. በወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል ከ ስድስት ወር ያልበለጠ ቀላል እስራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች ላይ የሚጣለው ቅጣት ጊዜ በዚህ መመሪያ ተያይዞ በሚገኘው የቅጣት እርከን ሠንጠረዥ(አባሪ-1) መሰረት በግዴት ስራ እንዲለወጥ ሊወስን ይችላል፡፡

በ. በቅጣት ማቅለያ ጊዜ የእስራት ቅጣትን ወደ መቀጮ መቀየር እንደሚቻል በህግ በተደነገገው መሰረት ወደ መቀጮ ሲቀየርም በዚህ መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡

ተ. የወንጀል ሕግ አንቀፅ 89፣ በተደነገገው መሰረት ከሶስት ወር የማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከ አንድ ሽህ ብር የማይበልጥ መቀጮ የሚያስቀጡ ወንጀሎች ላይ የሚጣለው ቅጣት ፣ በዚህ መመሪያ ተያይዞ በሚገኘው የቅጣት እርከን ሠንጠረዥ(አባሪ-1) መሰረት ማስጠንቀቂያ እና ተግሳፅ ሊወሰን ይችላል፡፡

2. የወንጀል ደረጃ ያልወጣላቸውን የወንጀል አይነቶችን በተመለከተ፡-

ሀ. የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በድንጋጌው በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት ሊያስቀጣ እንደሚችል የተደነገገ ከሆነ፣ ፍርድ ቤቱ በቀላል እስራት ወይም በጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን በቅድሚያ ይለያል፡፡

ለ. የወንጀሉ ከባድነትን በተመለከተ ‹ቀላል› ፣ ‹መካከለኛ› ፣ ወይም ‹ከባድ› በማለት ይለያል፡፡

ሐ. በዚህ መመሪያ በተመለከተው መሰረት መነሻ ቅጣቱን በመወሰን፣ በቅጣት እርከን ሠንጠረዥ የሚያርፍበትን የቅጣት እርከን ወይም የመቀጮ እርከን ይለያል፡፡

መ. ከዚህ በመቀጠል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከንዑስ አንቀጽ (ሠ-ቀ) በተመለከተው መሰረት ስሌቱን በመስራት ቅጣቱን ይወስናል፡፡

3. የወንጀል ደረጃ የወጣላቸው እና ያልወጣላቸው የወንጀል ዓይነቶች ተደራረበው ባጋጠሙ ጊዜ ለእያንዳንዱ ወንጀል በዚህ መመሪያ መሰረት የመነሻ ቅጣት ከተወሰነ በኋላ የሁለቱ ድምር የመነሻ ቅጣት ሆኖ ይወሰዳል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 120. ከዚህ መመሪያ ውጪ ቅጣት ሊወሰን የሚችልበት ስርዓት

1. ፍርድ ቤቱ የወንጀል አፈፃፀሙም ሆነ ባህርይው በዚህ መመሪያ ደረጃ በወጣላቸው ሊወከል የማይችል ሆኖ ባገኘው ጊዜ ወይም በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ቅጣቱን መወሰን የወንጀል ህጉን የቅጣት አላማ እና ግብ የማያሳካ ነው ብሎ ካመነ፣ መመሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ የማይችልበትን ምክንያት በዝርዝር በማስቀመጥ በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው በተለየ መልኩ ቅጣት ሊወስን ይችላል፡፡

2. ዳኞች ከመመሪያው ውጪ ቅጣትን ከወሠኑ ውሳኔው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲተላለፍ ግልጽ ትዕዛዝ ሊሰጡ ይገባል፡፡ የክልል ፍ/ቤቶችን በተመለከተ የውሳኔ ግልባጭ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በኩል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲላክ ማድረግ አለባቸው፡፡

3. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት መመሪያው ከሚያስቀምጠው በተለየ እርከን ላይ እንዲያርፍ በማድረግ የተሰጠውን ውሳኔ ግልባጭ ውሳኔ ከተሰጠበት ጀምሮ በ60 (በስልሳ) ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡

4. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከመመሪያው ውጭ የተወሰኑ የቅጣት ውሳኔዎችን ግልባጭ የሚቀበል እና የሚያደራጅ የስራ ክፍል ይኖረዋል ፡፡ ዝርዝሩ በሌላ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

### 121. የንብረት ግምት መወሰንን በተመለከተ

1. ወንጀሉ የተፈጸመው በውጭ ሀገር መገበያያ ገንዘብ ላይ ከሆነ የገንዘብ ምንዛሬ መጠን ወንጀሉ ሲፈፀም በነበረው የምንዛሬ ተመን መሰረት ይሆናል፡፡

2. በወንጀሉ የተወሰደው ንብረት በሚሆንበት ጊዜ የንብረቱን ግምት በተመለከተ ተከሳሹ ክርክር ካቀረበ እና የተከሳሹ ክርክር ተቀባይነት ቢያገኝ የቅጣት እርከኑን የሚቀየር ከሆነ እና በፍርድ ቤቱ እምነት በአቃቤ ህግ የቀረበው ግምት ምክንያታዊ ያልሆነ ነው ብሎ

ሲያምን የራሱን ግምት በማስቀመጥ ወይም በባለሙያ በማስገመት የወንጀል ደረጃውንና የቅጣት እርከኑን ይወስናል፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ ሁለት የተመለከተው ቢኖርም ተከራካሪ ወገኖች በግምቱ ላይ ክርክር ባያነሱም ፍ/ቤቱ የንብረቱን ግምት ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሊያጣራ ይችላል፡፡

4. ከንብረቱ ልዩ ባህሪ የተነሳ ግምቱን በገንዘብ መተመን ያልቻለ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በራሱ ተገቢ ነው ባለው መንገድ ቅጣቱን ሊወስን ይችላል፡፡

## 122. ስለቅጣት አስተያየት አቀራረብ

1. አቃቤ ሕግ፣ ጥፋተኞች ወይም ጠበቆቻቸው የቅጣት ውሳኔ አስተያየት በሚያቀርቡበት ጊዜ በዚህ መመሪያ መሰረት መሆን አለበት፡፡ ፍ/ቤቶችም በመመሪያው መሰረት የቅጣት አስተያየቶች መቅረባቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

2. በጠበቃ ለማይወከሉ ተከሳሾች በመመሪያው መሰረት የቅጣት አስተያየት ማቅረብ እንዳለባቸው ፍ/ቤቱ ሊገልጽላቸው ይችላል፡፡

## 123. ቅጣት እንዳይፈፀም ስለመገደብ

1. የቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል (የወን. ሕግ አን. 543(1)፣ 543 (2) እና 543(3)፣ ያለደረሰኝ ግብይት (የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ( አዋጅ ቁጥር 983/2008) አንቀጽ 120 (1)) እና የሚያዙበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ማውጣት (የወንጀል ሕግ አን. 693(1) በተመለከተ ቅጣትን የመገደብ አግባብነት የሚወሰነው በዚህ መመሪያ (አባሪ-3) በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሰረት ነው፡፡

2. ጥፋተኛ የተባለው ሰው በመስፈርቶቹ ተመዝኖ 60% እና ከዚያ በላይ የሚያገኝ ከሆነ ቅጣት የሚገደብለት ይሆናል፡፡

3. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንኡሳን ድንጋጌዎች የተመለከተው ቢኖርም፣ ፍ/ቤቱ በ አባሪ-3 የተዘረዘሩ መስፈርቶችን ተግባራዊ በማድረግ ውሳኔ መስጠት ተገቢ ሆኖ ካላገኘው፣ ምክንያቱን በዝርዝር በማስቀመጥ በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው በተለየ መልኩ ቅጣትን የመገደብ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ፣ ውሳኔው ከተሰጠበት ጀምሮ በ60 (በስልሳ) ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡

## 124. *የተሻረ መመሪያ*

የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን *መመሪያ* ቁጥር 2/2006 በዚህ *መመሪያ* ተሽሯል፡፡

## 125. *መመሪያው ስራ ላይ የሚውልበት ጊዜ*

ይህ *መመሪያ* ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ከ 15ኛው (አስራ አምስተኛው) ቀን ጀምሮ ስራ ላይ ይውላል፡፡

**አዲስ አበባ ፣ ሰኔ 26 ቀን 2017 ዓ.ም**

**ቴዎድሮስ ምህረት ከበደ**

**የኢ.ፌ.ድ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት**

## አባሪ-1

## ነፃነትን እና ሕይወትን የሚያሳጡ የቅጣት እርከኖች ሰንጠረዥ

| | | |
|---|---|---|
| እርከን 1 | ከ 1 ቀን - 3 ወር የግዴታ ስራ<br>ወይም<br>ተግሳፅ ፣ ማስጠንቀቂያ | እስከ 1000.00 ብር |
| እርከን 2 | ከ 10 ቀን - 6 ወር እስራት<br>ወይም<br>ከ 10 ቀን - 6 ወር የግዴታ ስራ | እስከ 2500.00 ብር |
| እርከን 3 | ከ 2 ወር - 8 ወር እስራት<br>ወይም<br>ከ 2 ወር - 6 ወር የግዴታ ስራ | እስከ 3000.00 ብር |
| እርከን 4 | ከ 4 ወር - 10 ወር እስራት | እስከ ብር 3500.00 |

| | | |
|---|---|---|
| እርከን 5 | ከ 6 ወር - 1 ዓመት እስራት | እስከ ብር 4500.00 |
| እርከን 6 | ከ 8 ወር - 1 ዓመት ከ 2 ወር እስራት | |
| እርከን 7 | ከ 1 ዓመት  - 1 ዓመት ከ 6 ወር እስራት | |
| እርከን 8 | ከ 1 ዓመት ከ 2 ወር - 1 ዓመት ከ 8 ወር እስራት | |
| እርከን 9 | ከ 1 ዓመት ከ 4 ወር - 1 ዓመት ከ 10 ወር እስራት | |
| እርከን 10 | ከ 1 ዓመት ከ 6 ወር - 2 ዓመት እስራት | |
| እርከን 11 | ከ 1 ዓመት ከ 8 ወር - 2 ዓመት ከ 2 ወር እስራት | |
| እርከን 12 | ከ 2 ዓመት - 2 ዓመት ከ 6 ወር እስራት | |
| እርከን 13 | ከ 2 ዓመት ከ 3 ወር - 2 ዓመት ከ 9 ወር እስራት | |
| እርከን 14 | ከ 2 ዓመት ከ 6 ወር - 3 ዓመት  እስራት | |
| እርከን 15 | ከ 2 ዓመት ከ 9 ወር - 3 ዓመት ከ 3 ወር  እስራት | |
| እርከን 16 | ከ 3 ዓመት - 3 ዓመት ከ 5 ወር  እስራት | ከዚህ በኋላ ያለው ፍ/ስልጣን በ 15% |

| | | |
|---|---|---|
| | | እንዲያድግ ተደርጓል |
| እርከን 17 | ከ 3 ዓመት ከ 3 ወር - 3 ዓመት ከ 9 ወር እስራት | |
| እርከን 18 | ከ 3 ዓመት ከ 6 ወር - 4 ዓመት እስራት | |
| እርከን 19 | ከ 3 ዓመት ከ 9 ወር- 4 ዓመት ከ 4 ወር እስራት | |
| እርከን 20 | ከ 4 ዓመት ከ 3 ወር - 4 ዓመት ከ 11 ወር እስራት | |
| እርከን 21 | ከ 4 ዓመት ከ 7 ወር - 5 ዓመት ከ 3 ወር እስራት | |
| እርከን 22 | ከ 4 ዓመት ከ 11 ወር- 5 ዓመት ከ 7 ወር እስራት | |
| እርከን 23 | ከ 5 ዓመት - 5 ዓመት ከ 9 ወር እስራት | |
| እርከን 24 | ከ 5 ዓመት ከ 5 ወር - 6 ዓመት ከ 3 ወር እስራት | |
| እርከን 25 | ከ 5 ዓመት ከ 10 ወር - 6 ዓመት ከ 9 ወር እስራት | |
| እርከን 26 | ከ 6 ዓመት ከ 4 ወር- 7 ዓመት ከ 7 ወር እስራት | |
| እርከን 27 | ከ 6 ዓመት ከ 9 ወር - 7 ዓመት ከ 9 ወር እስራት | |
| እርከን 28 | ከ 7 ዓመት ከ 2 ወር - 8 ዓመት ከ 3 ወር እስራት | |

| | | |
|---|---|---|
| እርከን 29 | ከ 7 ዓመት ከ 9 ወር - 8 ዓመት ከ 11 ወር እስራት | |
| እርከን 30 | ከ 8 ዓመት ከ 4 ወር - 9 ዓመት ከ 7 ወር እስራት | |
| እርከን 31 | ከ 9 ዓመት - 10 ዓመት ከ 4 ወር እስራት | |
| እርከን 32 | ከ 9 ዓመት ከ 8 ወር - 11 ዓመት ከ 1 ወር እስራት | |
| እርከን 33 | ከ 10 ዓመት ከ 5 ወር- 12 ዓመት እስራት | |
| እርከን 34 | ከ 11 ዓመት ከ 3 ወር - 13 ዓመት እስራት | |
| እርከን 35 | ከ 12 ዓመት - 13 ዓመት ከ 10 ወር እስራት | |
| እርከን 36 | ከ 13 ዓመት - 15 ዓመት እስራት | ከዚህ በኋላ ያለው ፍቅድ ስልጣን 2 ዓመት ነው፡፡ |
| እርከን 37 | ከ 14 ዓመት - 16 ዓመት እስራት | |
| እርከን 38 | ከ 15 ዓመት - 17 ዓመት እስራት | |
| እርከን 39 | ከ 16 ዓመት - 18 ዓመት እስራት | |
| እርከን 40 | ከ 17 ዓመት - 19 ዓመት እስራት | |

| | | |
|---|---|---|
| እርከን 41 | ከ 18 ዓመት - 20 ዓመት  እስራት | |
| እርከን 42 | ከ 19 ዓመት - 22 ዓመት እስራት | ፍቅድ ስልጣን 3 ዓመት ነው፡፡ |
| እርከን 43 | ከ 21 ዓመት - 25 ዓመት እስራት | ፍቅድ ስልጣን 4 ዓመት ነው፡፡ |
| እርከን 44 | ከ እድሜ ልክ እስራት - ሞት ቅጣት | |
| እርከን 45 | የሞት ቅጣት | |

## አባሪ-2

## የገንዘብ መቀጮ እርከኖች ሰንጠረዥ

| የመቀጮው እርከን | የገንዘብ መቀጮው ጣሪያ (በብር ) |
|---|---|
| እርከን 1 | እስከ 1,000.00 |

| | |
|---|---|
| እርከን 2 | እስከ 3,000.00 |
| እርከን 3 | እስከ 4,500.00 |
| እርከን 4 | እስከ 7,500.00 |
| እርከን 5 | እስከ 10,000.00 |
| እርከን 6 | እስከ 15,000.00 |
| እርከን 7 | እስከ 30,000.00 |
| እርከን 8 | እስከ 45,000.00 |
| እርከን 9 | እስከ 60,000.00 |
| እርከን 10 | እስከ 75,000.00 |
| እርከን 11 | እስከ 100,000.00 |
| እርከን 12 | እስከ 150,000.00 |
| እርከን 13 | እስከ 187,500.00 |
| እርከን 14 | እስከ 200,000.00 |
| እርከን 15 | እስከ 300,000.00 |

| | |
|---|---|
| እርከን 16 | እስከ 375,000.00 |
| እርከን 17 | እስከ 450,000.00 |
| እርከን 18 | እስከ 525,000.00 |
| እርከን 19 | እስከ 600,000.00 |
| እርከን 20 | እስከ 750,000.00 |
| እርከን 21 | እስከ 1,500,000.00 |
| እርከን 22 | እስከ 3,000,000.00 |
| እርከን 23 | ከ 3,000,000.00 በላይ |

## አባሪ-3

## የእስር ቅጣትን በገደብ የማቆየት ውሳኔ አሰጣጥ ሰንጠረዥ

| ተራ ቁጥር | ቅጣት ለመገደብ ታሳቢ የሆነው ምክንያት | ለ ምክንያቱ የሚያዘው ነጥብ | ጥፋተኛ የተባለው ሰው ያገኘው ነጥብ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የቤተሰብ አስተዳዳሪነት | ብቸኛ የቤተሰብ አስተዳዳሪ | ከ 10 እስከ 20 ነጥብ | | |
| | | ብቸኛ ያልሆነ የቤተሰብ አስተዳዳሪ | እስከ 10 ነጥብ | | |
| 2 | የጤና ሁኔታ | ከባድ ሕመሞች | ከ10 እስከ 20 ነጥብ | | |
| | | ከባድ ያልሆኑ ነገር ግን የሕክምና ክትትል የሚያስፈልጋቸው፡፡ | እስከ 10 ነጥብ | | |
| 3 | ከተበዳይ ጋር መታረቅ፣መካስ | ከተበዳይ ጋር የታረቀ ወይም የካሰ | 35 ነጥብ | | |
| | | ከተበዳይ ጋር ለመታረቅ ወይም ለመካስ ጥረት ያደረገ | እስከ 10 ነጥብ | | |
| | | ከተበዳይ ጋር ያልታረቀ፣ ለመታረቅም ጥረት ያላደረገ | 0 ነጥብ | | |
| 4 | የወንጀል ድርጊት መፈፀሙን ማመን | የወንጀል ድርጊቱን መፈፀሙን ያመነ | 10 ነጥብ | | |
| 5 | ሌሎች ምክንያቶች [1] | ምክንያቱ ይጠቀስ | ከ 1- 15 ነጥብ | | |

[1] ጥፋተኛው ወንጀሉን እንዲፈፅም ምክንያት የሆነው ነገር፣ የተከሳሽ እድሜ፣ የስራ ሁኔታ፣ በቀድም ማህበራዊ አስተዋፅኦ ወ.ዘ.ተ ታሳቢ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | | **አጠቃላይ ድምር** | 100 ነጥቦች | | |